


## የእውነት ዋጋ

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

3

## ረመዷንን ጠርጥሮ - ምርጫን በጓሮ



ሁሴን ከድር

12

## ፍሬንድ ዘመኑ የኤፍ.ኤም ነው!

(ካለፈው የቀጠለ)



በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)

6

# ፍትህ

ቅፅ 5 ቁጥር 192 አርብ ሰኔ 8 2004 ዓ.ም www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia ዋጋ 7.00 ብር

## የጠፋው ትውልድ እና የታህሪር ናፍቆት - ፪

5




## በትላንትናው ምሽት መገናኛ አካባቢ ከሕገ-ወጥ ንግድ ጋር በተያያዘ ነጋዴዎችና ፖሊሶች ተጋጩ

### - የአንድ ሰው ሕይወት አልፏል ተባለ

15

## ሁለት ጋዜጣ አዟሪዎች ‹‹ፍትህ ጋዜጣ ሕገ-ወጥ ነው እንዳትሸጡ›› ተብለን ነበር አሉ

‹‹ጋዜጣው የተያዘው ሕጋዊ ነው፣ አይደለም በሚል ሳይሆን በእግረኛ መንገድ ላይ ተዘርግቶ ስለተገኘ ነው››

ወ/ት መብርሀት ገ/ሚካኤል የፍትሕ ጽ/ቤት ኃላፊ

15

## መኢአድ በሰሜን ጐንደር የሚገኙ ሁለት አመራሮቹ የደረሱበት አለማወቁን ገለፀ

15

-አንደኛው በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ታስሮ ይገኛል

## የአቶ ኦልባና ሌሊሳን መደብደብ ማረሚያ ቤቱ አላውቅም አለ

15

## በማረሚያ ቤት የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ከትናንት ጀምሮ የረሃብ አድማ እያደረጉ እንደሚገኙ ተገለፀ

15

## በሀዋሳ ከተማ ጉዳይ ላይ የቀረበው ሰነድ ተቃውሞ እንደገጠመው ተገለጸ

15

## ከስራ የታገዱ መምህራን የይቅርታ ደብዳቤ እንዲያስገቡ መጠየቃቸውን ገለፁ

15

## ለአቶ አስገደ ገ/ሰላሴ 12 ሺህ ብር ተዋጣ

በጋህዲ ቁጥር ሶስት መፅሀፋቸው የስም ማጥፋት ክስ ተመስረቶባቸው ፍርድ ቤቱ እንዲከላከሉ የወሰነባቸው አቶ አስግደ ገ/ስላሴ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ለማጓጓዝ እስከ ትላንትና ድረስ አስራ ሁለት ሺህ ብር እንደተዋጣላቸው ታውቋል።

ከተዋጣው እስራ ሁለት ሺህ ብር ውስጥ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም 3 ሺህ ብር ያዋጡ ሲሆን ፍትህ ጋዜጣ 8ሺህ ብር ስታወጣ አንዲት ወጣት ደግሞ 1ሺህ ብር ያዋጣች መሆኑ ታወቋል። አቶ አስግደ በአጠቃላይ የሚያስፈልጋቸው 30 ሺህ ብር እንደሆነ ባለፈው ሳምንት መዘገባችን ይታወሳል።

# ኢትዮጵያውያኑ ስራ-አጥ ወጣቶች ወደ ዓመፅ ያመራሉን?



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

እንደሌሎቹ አቻ የአፍሪካ ደሀ ሀገራት ሁሉ ኢትዮጵያም በንፅፅር ብዙ ወጣቶች ያሉባት ሀገር እየሆነች መጥታለች። በተለይም በከተማ የሚኖሩ ወጣቶች ቁጥር ከሌሎች በዕድሜ እርከን ክፋይ ውስጥ ከሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች አንፃር ያላቸው የቁጥር መጠን እጅግ ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያ የወጣትነት ዕርከንን በምትበይንበት ከ15 እስከ 29 ያለውን የዕድሜ ክልል ተንተርሶ በቀደመው ዓመት የወጣው የስታስቲክስ ባለስልጣን አንድ ሪፖርት እንደሚለው በከተሞች ያለው የወጣቶች ቁጥር ወደ 40% ይጠጋል። “Analytical Report: on the 2010 urban Employment unemployment survey” በሚል ርዕስ የወጣው የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጥናት፤ የከተማ ስራ አጥ ወጣቶችን ቁጥር 24.5% ሲያደርገው፣ ሌሎች ተቋማትና ፀሐፊዎች ወደ 40% ያስጠጉታል። ካላቸው ከፍተኛ ቁጥር አንፃር ወጣቶች በዚህ ልክ ስራ አጥ መሆናቸው የስርዓቱ የፖሊሲ ውድቀት መሆኑን የሚከራከሩ ፀሐፊዎች አሉ። ሹመቴ ግዛው የተባሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጂኦግራፊ ትምህርት ክፍል የሦስተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ አጥኚ እንደሚከራከሩት ያለፉት አስርት ዓመታት የልማት ፖሊሲ ተሞክሮዎች ክሽፈትን የሚያስረዳው ለወጣቶች የስራ ዕድል ሊሰጥ ይቻል የነበረበት በከተሞች ያለው የኢንዱስትሪ ክፍለ-ኢኮኖሚ አለማደግ ነው። ፀሐፊው “A glimpse at urban youth unemployment in Ethiopia” በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚጠቅሱት ከዚህ ውድቀት መነሾ የወጣቶች በከፍተኛ መጠን ስራ አጥ መሆን የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተሞች መለዮ ሆኗል። ይህን ከፍተኛ ስራ አጥነት በሀገሪቱ ከተሞች በንፅፅር ለማየት የሞከሩት ሌላኛው ለጤናህ እጅጉ የተባሉ ፀሐፊ በበኩላቸው በሌሎች ሀገራት የተለመዱ ወደ ማይመስሉ መላምቶች ያመራሉ። ከተሞች በከተማነት ሊያስይሟቸው የሚችሉ የማህበራዊ፣ የፖለቲካ እና የንግድ ተቋማትን የበለጠ እያስፋፉ በሄዱ ቁጥር ከሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች በተሻለ ሁኔታ ለኗሪዎቻቸው የስራ ዕድሎችን እያበዙ ይሄዳሉ። ተመራማሪው “Characteristics and determinants of youth unemployment in Ethiopia›› በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው እንደሚያወሱት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ያለው የወጣት ስራ-አጥ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል። ብዙ ስራ-አጥ ወጣቶችን በመያዝ በከተማነት ባህሪያቸው በአንፃራዊነት ከሌሎች ክልሎች የተሻሉ የሆኑት አዲስ አበባ እና ድሬደዋ ቀዳሚውን ደረጃ ይይዛሉ። አጥኚው በሱማሌ ክልል ላለው ስራ አጥነት የክልሉን ሰላም አልባነት በምክንያትነት ሲያነሱ፤ ለአዲስ አበባ እና ለድሬደዋ ከተሞች በብዙ ሌሎች ፀሐፊዎች በዋነኝነት ሲጠቀስ የማይስተዋለውን ከገጠር-ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን ይጠቅሳሉ።

### የሥራ-አጥ ወጣቶች ሀገር

በከተሞች በሚኖሩ ስራ-አጥ ወጣቶች ላይ የሚፅፉ አጥኚዎች በቀዳሚ ምክንያትነት የሚያነሷቸው የኢኮኖሚውን ሥራ የመፍጠር አቅም፣ የህዝብ ቁጥር መብዛት፣ የትምህርት ስርዓቱ ከነባራዊ አውድ ጋር አለመገናዘብ እና ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰቶችን ቢሆንም በመጀመሪያው ምክንያት ላይ ከመስማማታቸው በተፃራሪ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው የዜጎች ፍልሰት ለከተማ ወጣቶች ስራ-አጥነት አባባሽ ነው በሚለው ላይ አይስማሙም። በአንድ ሀገር ውስጥ ያለ ስራ አጥነት በወጣቶች ላይ በተለየ መልኩ እየናረ ከመጣ የኢኮኖሚውን ብቃት ጥያቄ ውስጥ እየከተተው ይመጣል። ጌትነት ሀይሌ የተባሉ ኢኮኖሚስት እንደሚናገሩት የወጣቶች ስራ አጥነት መብዛት ኢኮኖሚው ያለውን አጠቃላይ የሰው ሃይል ፍላጐት /Aggregate demand/ መቀዛቀዝ ያሳያል። እንዲህ ዓይነት ሀገራዊ የፍላጎት መቀዛቀዝ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የስራ እድሎች ብቻ እንዲኖሩ ስለሚያደርግ ወጣቶቹ ከትውልድ አቻዎቻቸው ጋር ከሚኖራቸው ፉክክር የበለጠ፣ የተሻለ የስራ ልምድ ካላቸው፤ ከነርሱ በዕድሜ ከሚበልጡት ጋር ለመፎካከር ይገደዳሉ። ኢኮኖሚስቱ “The incidence of youth unemployment in urban Ethiopia” በሚል ርዕስ ባሳተሙት ጥናታዊ ፅሁፍ እንደሚሞግቱት አሁን በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለው የስራ አጥ ቁጥር መናር ከኢኮኖሚው እድገት ጋር በቀጥታ ይዛመዳል። የሀገሪቱ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ሲያድግ የስራ አጡ ቁጥር ሲቀንስ፤ የኢኮኖሚው ድቀት እንዲሁ ቁጥሩን ከፍ ያደርገዋል። በቁጥሩ ላይ መስማማት ባይኖርም የኢትዮጵያ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት እያደገ ከዚህ በግልባጩ የከተማ ወጣቶች ስራ አጥነትም እንዲሁ እየጨመረ ከመጣ የችግሩ መነሻ የሚሆነው መዋቅራዊ ነው ይላሉ የዌስት ሚኒስተር ዩኒቨርስቲው ተመራማሪ ጌትነት ኃይሌ። ብርሃኑ ዴኑ፣ አብርሃም ተከስተ እና ሃናናህ ቫን ዴር ዴጂል የተባሉ አጥኚዎች በሌላ በኩል የስራ-አጥነቱን ቁጥር ከኢኮኖሚው ዕድገት ጋር በማያያዝ እንደሚደመድሙት አለ የሚባለው የኢኮኖሚ እድገት እጅግ የሚዋዥቅ በመሆኑ እና ዕድገቱ ተገማች ሊሆን ባለመቻሉ የተነሳ የወጣቶቹ ስራ አጥነት በሚታየው መንገድ ሊንር ችሏል። ጌትነት ሃይሌ እና ለጤናህ እጅጉ በበኩላቸው የሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ለስራ አጥነት አስተዋፅኦ እንዳለው ይከራከራሉ። የሁለቱ አጥኚዎች መከራከሪያ ግልፅ ነው። ኢህአዴግ እ.ኤ.አ. በ2015ዓ.ም እንዲከወኑ የሚጠበቁትን የሚሊንየም የልማት ግቦች በማስላት በከፍተኛ ሁኔታ ትምህርትን ለማስፋፋት እየጣረ ቢሆንም በትምህርት ስርዓቱ ጥራት ላይ የሚወቅሱት ተቋማትና ፀሐፊዎች ቁጥራቸው ይበዛል። ይህ ጥራትን ለብዛት ሲባል የመጨፍለቅ የስርዓቱ አካሄድ የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታ ከሚፈልጋቸው ክሂላዊ ልቀቶች እና የቁጥር ፍላጐት ጋር አለመዛመዱ የተማሩ ስራ አጥ የከተማ ወጣቶችን አብዝቷል። እነ ብርሃኑ ዴኑ በበኩላቸው በሀገሪቱ ያለው የተማረ ዜጋ ቁጥር አነስተኛ መሆን ስራ አጥ ከሆኑት ወጣቶች መሀከል የተሻለ ትምህርት ያላቸው በንፅፅር ከሌሎች ያነሰ ድርሻ እንዲኖራቸው ቢያስችልም ኢኮኖሚያዊ ስርዓቱ ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ወጣቶቹን ሊያካትት ካልቻለ ሁኔታው የከፋ ሊሆን እንደሚችል ያስጠነቅቃሉ።

ኢህአዴግ ወጣቶችን በተመለከተ ባወጣቸው ፖሊሲዎች ለከተማ ነዋሪዎች ስራ-አጥነት አብዝቶ የሚያነሳው ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ቢሆንም በጉዳዩ ላይ የፃፉ ምሁራን ይህን የፓርቲውን መከራከሪያ ያብጠለጥሉታል። እነ ብርሃኑ ዴኑ “Characteristics and determinants of youth unemployment, underemployment and inadequate employment in Ethiopia” በሚለው ጥናታዊ ስራቸው ከገጠር ወደ ከተማ የሚካሄደው የዜጎች ፍልሰት ፓርቲው በሚያነሳበት ልክ ላለመሆኑ እንደመሞገቻ የገጠሩን የመሬት ስሪት ያነሳሉ። እንደ አጥኚዎቹ ክርክር በገጠር ያሉት ነዋሪዎች በመሬታቸው ላይ የተረጋጋ የባለቤትነት ስሜት ስለማይሰማቸው አልፎም ይዞታቸውን ለቀው በከተሞች በቋሚነት ለመኖር ቢወስኑ የመሬት ባለቤትነታቸው ሊነጠቅ የሚችልበት እድል መኖሩ የፍልሰቱን ቁጥር አሳንሶታል። ከነዚህ ፀሐፊዎች በተዛመደ መልኩ ፊሊፕ ክሪሽናን “Family background, education and employment in urban Ethiopia” በሚለው ፅሁፋቸው በኢትዮጵያ ያለው ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት አንፃር እጅግ አነስተኛ መሆኑ በከተሞች ለሚታየው ከፍተኛ የወጣቶች ስራ-አጥነት ቁጥር በምክንያትነት እንዲቀርብ አያስችልም ሲሉ ይሟገታሉ።

### ሀገር እየደማች ነው!

የስራ አጥነት ጥያቄ በአንድ ዘርፍ ያሉ ምሁራን ጭብጥ ብቻ ከመሆን ዘሏል። የማህበር-ኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ክስረቶችን ለማስከተል የሚያስችል የመሆኑ ጉዳይ የፖለቲካ ስርዓታት በጥንቃቄ የሚመለከቱት እንዲሆን እንዳስገደደ ብዙ ተንታኞች ይስማማሉ። በጉዳዩ ላይ የሚፅፉት እንደሚሉት ስራ አጥነት በተለይም በከተማ ወጣቶች አካባቢ መከሰት ግዙፍ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ቀውሶችን ያስከትላል። ሁነቱን ያጠኑ ኢኮኖሚስቶች ለመከራከሪያነት የሚያቀርቡት፣ ሥራ-አጥ ዜጐች ወደ ስራ ባለመሰማራታቸው ሀገራቱ ያገኙ የነበሩትን የሀገራዊ ምርት ጭማሮዎች ማጣት ላይ ነው። ከዚህ ጭብጥ በተጨማሪ የስራ-አጦች መብዛት መንግስታቱ ሊሰበስቡ ይችሉ የነበሩትን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ያሳጣቸውዋል። እነዚህ ስራ-አጥ ወጣቶች አልፎ አልፎ እንደሚስተዋለው አነስተኛ ገቢ ለማግኘት ሲሉ የሚገቡባቸው ስራዎች ከሰለጠኑበት ክሂል ያነሰ የሚጠይቅ መሆኑ፣ አቅማቸውን በሚገባ እንዲጠቀሙ የማያስችላቸው ከመሆኑ መነሾነት አጠቃላይ ኢኮኖሚው ከሚኖረው በውስጡ ያሉ ተለዋጮችን በተሳለጠ መንገድ ያለመጠቀም ተፅዕኖ ያመጣል። ጆሴፍ ስቲግሊትዝ “Employment, social justice and societal well-being” በሚል ርዕስ በጉዳዩ ላይ ሩሲያን በማሳያነት ጠቅሶ በሚያወሳበት ስራው እንደሚለው ይህን መሰል ክስተት በሀገራት ውስጥ ሲፈጠር ማህበረሰቡ በድህነት አዙሪት ውስጥ ይሽከረከራል።

ሌሎች ተቋማት እና ምሁራን በሌላ ጫፍ ያለውን ማህበረሰባዊ ክስረት ሲተነትኑ፣ ስራ-አጥነት በግለሰቡ ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት፣ ማህበረሰቡን ሊያፈራርሱ እስከሚችሉ ያሉ ሁነቶችን ይጠቅሳሉ። የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን “Meeting the challenges of unemployment and poverty in Africa” በሚል ርዕስ ከጥቂት ዓመታት በፊት ባወጣው ጥናት፤ ስራ አጥነት አንድን ግለሰብ ከጤና መቃወስ እስከ ጥልቅ ሱሰኝነት ያሉ መዘዞችን ሊያመጣበት እንደሚችል ይተነትናል። ጌትነት ኃይሌ የተባሉት የነገረ-ሀብት አጥኚ፤ የሥራ-አጥነት ጊዜያት እየተራዘሙ ሲሄዱ፣ ዜጎች ቤተሰብ ለመመስረት እየተቸገሩ ይመጣሉ፤ ይህም የሚገመቱና የማይገመቱ ማህበራዊ ቀውሶችን ያስከትላሉ ሲሉ ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው ያወሳሉ። አንዳንድ ከሰሃራ በታች ያሉ ሀገራት ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን በወጣት ጥፋተኝነት፣ በኤች አይ ቪ ኤድስ መበራከት፣ በዕፅ ተጠቃሚነት እና በስራ-አጥነት መሀከል ተጣምሮሻዊ ቀጥተኛ ዝምድና እንዳለ ይከራከራሉ። ከስራ-አጥነት የሚነሱት እነዚህ ሁነቶችም በተራዛሚው ሀገራዊ ዕሴቶችን በማውደም ማህበረሰቡን ወደ ቀውስ ይወስዱታል።

### ወጣቶቹ ያምፃሉ?

ጀርመናዊው የማህበረሰብ ሳይንስ ባለሙያ ገንናር ሂንሾን እ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ አጋማሽ እርሱ ጥናት ባካሄደባቸው ሀገራት እየተፈጠረ የነበረውን የወጣቶች ቁጥር መበራከት “youth bulge” የሚል ስያሜ ሰጠው። ወጣቶች ከፖለቲካዊ ዓመፅ ጋር ያላቸውን ጉዳይ በመፈተሽ ቀዳሚ የሆነው አሜሪካዊው የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪ ጃክ ጎልድስቶን የሂንሾንን ሃሳብ በነባራዊ ጭብጦች አጋዥነት በጥልቀት ለማብራራት ሞክሯል። ጎልድስቶን “Revolution and rebellion in the Early modern world” በሚለው ስራው ወጣቶች እና አብዮት ያላቸውን ዝምድና በመመርመር የገንናር ሂንሾን ሃቲት ወደመሬት ሊያወርደው ሞክሯል። ከጎልድስቶን በዘለለ ሄነሪክ ኡርዳል፣ ፖል ኮሊየር፣ ኒኮላስ ሳምባኒስ እና ሄለን ዋሬ በወጣትነት እና በፖለቲካዊ ዐመፆች መሀከል ያሉ ዝምድናዎችን በጥልቀት በመመርመር ቀዳሚዎች ናቸው።

በነዚህ ሁለት ጭብጦች ላይ የፃፉት መምህራን ፖለቲካዊ ዐመፅ ለሚለው ሀሳብ ደም ከሚያፋስሱ ግጭቶች እስከ ሰላማዊ አብዮት እና ማህበረሰባዊ ስርዓት መናጋትን የሚጨምር ፍቺ ይሰጡታል። በእነ ፖል ኮሊየር የሚቀነቀነው ሃቲት ከፍተኛ አትኩሮት የሚሰጠው ማዕከላዊ መንግስቱ ላይ የሚያምፁ ታጣቂ ቡድኖች እና የሀገሪቱ ስራ-አጥ ወጣቶች አማፂዎቹን መቼ ሊቀላቀሏቸው እንደሚችሉ በመተንተን ነው። ፕ/ር ፕል ኮሊየር ከሃንኪ ሆፍለር ጋር በሰሩት “Greed and Grievance in civil war” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው፤ አማፂ ቡድኖች ያሉበት የፖለቲካ ስርዓት ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ስራ-አጥ ወጣቶች ባሉበት ማህበረሰብ ውስጥ መነሳት ከጀመረ ለአማፂዎቹ ወጣቶቹን ወደዚህ እንቅስቃሴ ማካተት ከባድ አይሆንም። እንደ ፀሐፊዎቹ መከራከሪያ ወጣቶቹ በስራ አጥነት ለረዥም ጊዜ መግፋት ከሚፈጥርባቸው የመደበት ህይወት አልፎም ለስራ-አጥነታቸው መንግስትን ተጠያቂ ማድረጋቸው ስርዓቱን ወደሚጥል ዓመፅ እንዲያማትሩ ይገፋቸዋል። ኒኮላስ ሳምቢያንስ “A review of recent advances and future directions in the quantitative literature on civil war” በሚለው ስራቸው ግራ-ዘመሙን ‹‹የአንፃሮ-ድህነት›› ኃልዮትን (Relative deprivation theory) በመጠቀም እንደሚያወሱት ከኢኮኖሚው ድቀት የሚነሳው ስራ-አጥነት እና የገቢ ኢ-እኩልነት ከወጣቶች መብዛት ጋር ተዛምዶ ሲከሰት ፖለቲካዊ ዓመፅን ቀላል ያደርገዋል የሚለው አንዱ ሲሆን፤ ሌላኛው የዚህ ሀልዮት ትንታኔ የሚያርፈው ወጣቶቹ መንግስት ይከውንልናል ብለው የሚጠብቁት የሥራ እድል ከገቢያቸው አንፃር ሲታይ የሚኖረው ያልተጠበቀ አሉታዊ ውጤት ሌላኛው ወጣቶችን ለአመፅ ቅርብ ከሚያደርጋቸው ገፊ ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ነው። ሳምቢያንስ፣ ስራ-አጥ እንዲሆኑ የተገደዱት ወጣቶችም ማዕከላዊ መንግስቱን በመጣል ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቻቸውን ማስከበር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል ሲሉ ይከራከራሉ። ከዚህ የሳምቢያንስ መከራከሪያ ጋር በተቀራረበ መንገድ የፃፉት እነ ኮሊየር ወጣቶቹ ወደዚህ ሊያመሩ የሚችሉት ባለማመፃቸው የሚያጧቸው ነገሮች በማመፃቸው የኢኮኖሚያዊ ዕጦታቸውን ምንጭ ማውደምን ጨምሮ ከሚያገኟቸው ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ዋጋ እንዳለው ወጣቶች ያምናሉ የሚል የኢኮኖሚክስ ዕሴቶችን የሚንተራስ መከራከሪያ ነው።

እነዚህ ሀቲቶችን በመዋስ የእስያ እና ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራትን ያጠኑት ሄነሪክ ኡሪዳል በጉዳዩ ላይ ጥቂት መላምቶችን ወደ እነጎልድስቶን መከራከሪያዎች ውስጥ ቀላቅለዋል። ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል አንፃር ወጣቶች በቁጥር እየበዙ ሲመጡ ፖለቲካዊ ዓመፅ የሚከሰትበት እድል እየሰፋ ይመጣል ከሚለው ቀዳሚ ሙግታቸው በተጨማሪ የወጣቶች የኢኮኖሚ መገለል እና የከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት ከፖለቲካዊ ዓመፅ ጋር ያለውን ትስስሮሽ ተንትነዋል። የኢኮኖሚያዊ መገለል የሚገለጥበት አንደኛው መልክ በስራ ላይ ያሉ ዜጎች በገቢያቸው ምን ያህል ሰዎችን ያስተዳድራሉ? የሚለው ነው። የኢኮኖሚው ዕድገት እየተቀዛቀዘ መምጣት ስራ-አጥ ዜጎችን እያበዛ ይመጣል። ኡርዳል እነዚህ ስራ-አጥ ዜጎች በሌሎች የቤተሰብ አባሎቻቸው ላይ የኢኮኖሚ ጥገኞች መሆን ለፖለቲካዊ ተቃውሞ የተመቻቹ ያደርጋቸዋል ሲሉ “A clash of generations? Youth bulges and political violence” በሚለው ፅሁፋቸው ይናገራሉ። እነ ብርሃኑ ዴኑ ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው በየዓመቱ ሁለት ሚሊየን ስራ ፈላጊ ወጣቶች ወደ ገበያው እየመጡ መሆናቸውን ከመጥቀሳቸው በዘለለ ከ100 ኢትዮጵያውያን 93 የሚሆኑት በሌሎች ላይ የኢኮኖሚ ጥገኞች መሆናቸውን ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪ እድሜያቸው ከ15-24 የሆኑት የሀገሪቱ ወጣቶች የስራ-አጥነት መጠን በየዓመቱ በ7% ይጨምራል። እነዚህ ቁጥራዊ ዕውነቶች የኡርዳልን የተጠቀሰውን መላምት የኢትዮጵያም ዕውነት የሚያደርገው ይመስላል። ሌላኛው የኡርዳል መላምት የትምህርት ስርጭት መስፋፋትን ከፖለቲካዊ ዓመፅ ጋር የሚያያይዘው ነው። መንግስታት የወጣቶችን በቁጥር እየበዙ መሄድ ማህበራዊ ቀውሶችን ወደማምጣት እንዳይሻገር የከፍተኛ ትምህርትን በስፋት ለማዳረስ ይሞክራሉ። በእነዚህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚያልፉ ወጣቶች ወደ ስራ ፍለጋ ሲመጡ በክሂላቸው ልክ የስራ ዕድሎችን እንደሚያገኙ መጠበቃቸው ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የኢኮኖሚው የሰራተኛ ኃይል ፍላጎት ጋር የማይዛመድ ከሆነ ሁኔታዎች መልካቸውን መቀየር ይጀምራሉ የሚሉት ኖርዌጂያዊው ፀሐፊ ይህን ተከትሎ የሚመጣውን ሁነት ‹‹እጅግ አደገኛ›› ሲሉ ይጠሩታል። “Urban youth bulges and social disorder: An empirical study of Asian and sub-Saharan African cities” በሚል ርዕስ ከሌላ አጋራቸው ክርስቲያን ሀልሼር ጋር በሰሩት ጥናት ይህን ጉዳይ ሲያብራሩ፤ ባለፉት መቶ ዓመታት ፖለቲካዊ ዓመፆችን የመሩት የተማሩ ወጣቶች መሆናቸውን በማስታወስ፣ ስራ አጥነቱ የተማሩ ከተሜ ወጣቶች አካባቢ እየጨመረ ከመጣ ፖለቲካዊ ስርዓቱን የሚያናጋ ዓመፅ እጅግ ቅርብ ይሆናል ሲሉ ያወሳሉ። ከዚህ የኡርዳል ሙግት ጋር የሚዛመዱ ክርክሮቻቸውን የሚያቀርቡት ማካርታን ሃማፍሬይስ እና ጀርሚ ዊንስተን የወጣቶች በፖለቲካዊ ስርዓት ተደማጭ መሆን ያለመቻል ለሀሳቡ መከራከሪያ ተጨማሪ ተለዋጭ መሆን እንዳለበት ይጠቅሳሉ። ፀሐፊዎቹ “Who fights? The determinants of participation in civil war” በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚተነትኑት ከተሜ ወጣቶች ወደ ፖለቲካዊ ስርዓቱ ለመቀላቀል እና ትውልዳዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሰማት ከተከለከሉ ወደ ተቃውሞ የማምራት ዕድላቸው ይሰፋል። ፀሐፊዎቹ በአፍሪካ ውስጥ የተደረጉትን የአመፅ እንቅስቃሴዎች በማጥናት ደረስንበት እንደሚሉት መደምደሚያ በማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ተሳትፎ አድርገው የማያውቁ ወጣቶች፤ ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀር በሦስት ዕጥፍ ፖለቲካዊ ዓመፆችን የመቀስቀስ ዕድል አላቸው።

ይህን መሰል ከስራ-አጥነት የሚነሳውን የወጣቶችን ፖለቲካዊ ዓመፅ ለማርገብ አምባገነን መንግስታት ከሚወስዷቸው እርምጃዎች ቀዳሚው ስደትን ማበረታታት ነው። ይህን የመንግስታቱን አካሄድ ‹‹ማስተንፈሻ መንገድ›› /Safety valve/ ብለው የሚጠቅሱት ሄለን ዋሬ “Demography, migration and conflict in the pacific” በሚለው ፅሁፋቸው ደሃ ሀገራት በወጣቶች ከሚመራ የፖለቲካ ዓመፅ ነፃ መሆን ከወጣቶቹ የስደት መጠን ጋር እንደሚያያዝ ያወሳሉ። ዊልያም ደብሰን የተባለ የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጠኛም፣ የአረቡን ዓለም አብዮት ካጠና በኋላ “Dictatorship for Dummies” በሚለው የጋዜጣው መጣጥፍ ይህን ጉዳይ ያነሳል። ቀሪ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች ከወደቁት አቻዎቻቸው መማር አለባቸው ካላቸው ሰባት ነገሮች አንደኛው ‹‹‹ለወጣቶቻችሁ ፓስፖርት አድሏቸው›› የሚል ነው። ‹‹በአምባገነናዊነታችሁ የተነሳ ለሁሉም ወጣቶች የስራ እድል መስጠት ስለማይቻላችሁ ስደትን አበረታቱ›› የሚለው ደብሰን ‹‹እነዚህ ስራ-አጥ ወጣቶች የራሳቸውን እና የቤተሰባቸውን የድህነት ጥልቀት በሚገነዘቡበት ወቅት ስርዓታችሁ ላይ መከራ መጥራታችሁ አይቀርምና›› ሲል ፅፏል። የኢትዮጵያውያንም ስደት ይህን መልክ እንደሚይዝ የሚናገሩት እነ አብርሃም ተከስተ፤ ስራ ፍለጋ ሀገራቸውን ለቀው ከሄዱት ዜጎች መሀከል 94% በመቶ የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ15-29 በሆነ እርከን ውስጥ የሚያርፉ መሆናቸውን ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው ይጠቁማሉ።

እነዚህን ሀሳባዊ ሙግቶች በኢትዮጵያ አውድ ሊመረምር የደፈረ ፀሐፊ ገና ወደ አደባባይ አልመጣም። በግርድፉም ቢሆን ይህን የሞከሩት አፍቃሬ ኢህአዴግ በሆነው አይጋ-ፎረም ድረ-ገጽ ላይ የፃፉት ፀጋዬ ተገኑ የተባሉ ፀሐፊ ሲሆኑ መከራከሪያዎቻቸው እርስ በእርስ የሚጣረሱ ይመስላሉ። “Revisiting youth bulge countries, Deprivation Hypothesis and opportunity perspective” በሚል ርዕስ ፀሐፊው በድረ-ገጹ ባሳተሙት ፅሁፍ፣ ግብፅ እና ቱኒዚያ እያንዳንዳቸው ከኢትዮጵያ አርባ በመቶው ያነሰ 34.1% እና 30.7% የሚሆን የስራ አጥ-ቁጥር ቢኖራቸውም ኢህአዴግ እንደግብ እከውነዋለሁ ከሚለው የትራንስፎርሜሽን እቅድ አንፃር ወጣቶቹ ያምፃሉ ብሎ መጠበቅ የተጋነነ አተናተን እንደሚመስላቸው ተናግረዋል። እርሳቸው ይሄን ቢሉም፣ ሊዩኔል ባህነር የተባሉ ፀሐፊ “The effects of ‘youth bulge’ on civil conflicts” በሚለው ፅሁፋቸው ይህን ጭብጥ አንስተው ‹‹ወጣቶቹ ሌላ ምርጫ ከሌላቸው እና ከስደት ከታቃቡ ወደ ፖለቲካዊ አመፅ ያጋድላሉ›› ሲሉ የሚከራከሩበት ኃይለ-ሀሳብ ኢትዮጵያዊም ጭብጥ የሚያጣ አይመስልም።

# የእውነት ዋጋ



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

ለአገርና ለወገን እቆረቆራለሁ፤ ለአገርና ለወገን እቆማለሁ፤ በቃልም ሆነ በተግባር ገለልተኛ ተመልካች አልሆንም ብሎ በቁርጥ የተነሣ ሰው ጨርቄን ማቄን፣ ስሜን አጠፋችሁብኝ፤ ክብሬን አጎደፋችሁብኝ ብሎ ሲበሳጭና ከዚያም አልፎ ወደፍርድ ቤት ሲሄድ ያሳዝናል፤ ዱሮውኑ በአገርና ሕዝብ ጉዳይ ውስጥ ሲገባ ዘጠና ሚልዮን ሕዝብ ተሰብስቦ ያጨበጭብልኛል ብሎ ከሆነ ቂል ነው፤ ጥሩ ኑሮ በጥሩ ደመወዝ እየኖረ ደመወዙን ከሚከፍለው ሕዝብ መሀከል በእሱ ሥራ የማይደሰት ሊኖር እንደሚችልና ወቀሳም ሆነ ነቀፌታ ሊሰነዘርበት እንደሚችል ያልተገነዘበ ሰው በንግድ ቢሰማራ ይሻለዋል፤ (እዚያም ቢሆን በሱ ዋጋ ካልገዛችሁኝ ብሎ ሱቁን ዘግቶ ቢቀመጥ ትርፉ ችጋር ነው፤) ወፍራም እንጀራ ብቻ አይቶ በሕዝብ ጉዳይ ውስጥ በመንግሥት ሠራተኛነትም ሆኖ በፖለቲካ ጥልቅ ብሎ ገብቶ አትንኩኝ አርፌ ልብላ የሚል ጮሌ ወይም ጮሌ-መሳይ ቂል እዬዬ ቢል ሰሚ ሊያገኝ አይገባም፤ የአገርና የሕዝብ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሰው ለቤተዘመዶቹ፣ ለቤተሰቡና ለልጆቹ ማሰብ ያለበት ገና ሳይነከርበት ነው፤ ሊያስመሰግናቸውና ሊያስከብራቸው የተሰማራ መሆን እንዳለበት የሚወስነው እሱ ራሱ ብቻ ነው፤ ሥራዬን በአደባባይ አትናገሩብኝ ሚስቴንና ልጆቼን ታስቀይሙብኛላችሁ ማለት ሞኝነት ነው፡፡

የመንግሥት ጉልበተኛም ሆነ ተስፈኛ ጉልበተኛ ሥልጣኑን ዱላ አድርጎ ሲጠቀምበት ከኖረ በኋላ ሥልጣን የሕዝብ አደራ እንጂ ዱላ አይደለም ሲሉት ረስቶት ወደቆየው ሕግ ልሸጎጥና የሙጢኝ ልበል ቢል ሕጉም ሊጠየፈው ይገባል፤ የሰዎች መብቶች ሲረገጡ ሳይሰቀጥጠው የኖረ ሰው ወቀሳንና ነቀፌታን መቀበል ተስኖት ስሜን አጎደፋችሁት ቢል አንዱን የመብት ጎን አላየውም፤ መብት በግልባጩ ግዴታ ወይም ኃላፊነት አለው፤ በአገርና በሕዝብ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሁሉ መብት አለው፤ ነገር ግን ከዚህ መብት ኃላፊነት የሚመነጭ መሆኑንም መረዳት ያሻል፤ ሕግ ንጽሕናን እንጂ ጉድፍን ጠባቂ ሊሆን አይችልም፤ ሊሆንም አይገባም፡፡

አገሩና ወገኑ በትክክለኛ መንገድ እንዲጓዙለት፣ እንዲለሙና እንዲበለፅጉለት፣ እንዲበረቱና እንዲጠነክሩለት የሚጥር እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ነው፤ የሚያውቀውን ለማሳወቅና እስከዛሬ ለአገሩና ለወገኑ የታገለበትን ትክክለኛ ዓላማ ለማስረዳት እየጣረ ነው፤ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ስሞችን ይጠራል፤ የሚወደሰውን ያወድሳል፤ የሚነቀፉትንም ይነቅፋል፤ በአንድ ወቅት የሚመሰገኑትም ሆኑ የሚወቀሱት በአንድ ላይ ለአገራቸውና ለወገናቸው የተሰለፉ ነበሩ፤ ዛሬ የተለያየ አስተሳሰብና የተለያየ እምነት ቢኖራቸውም ያንን አንድ አድርጎ የጠመዳቸውን ዓላማና በኋላ የተለያዩበትን ምክንያት ዘርዝሮ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስቀረት ትልቅ ኃላፊነትን መሸከም ነው፤ አቶ አስገደ ይህንን ኃላፊነት በፈቃደኛነት ወስዶአል፤ በሀሳብ የሚለዩትም ሆኑ የሚስማሙት ሊረዱት ይገባቸዋል፤ በሀሳብ የሚስማሙት መረጃና ማስረጃ በማሰባሰብ ሊረዱትና ሥራውን በጣም ፍሬያማ ሊያደርጉት ይገባል፤ በሀሳብ የማይስማሙት ደግሞ የራሳቸውን እይታና አመለካከት ከማስረጃ ጋር የያዘ ጽሑፍ ቢያቀርቡ እውነቱን ይክቡት ነበር፤ አንድ ሰው ብቻውን ቤት ዘግቶ ከመላእክት ጋር እየተነጋገረ ዜና መዋዕል የሚጽፍበት ዘመን አለፈ፤ አይመለስም፡፡

አቶ አስገደ የሚጽፈው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ለትግል ስለመሰለፋቸው፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የመጨረሻውን መስዋእት ከፍለው በዱር በገደሉ የቀሩ ስለመኖራቸው፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆን የአካል ክፍላቸውን ገብረው በችግር የሚኖሩ ስለመሆናቸው፣ እነዚህ ሁሉ ያሳለፉትን የትግል ታሪክ ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ነው፤ ከዚህ የበለጠ ክቡር ሥራ ምን አለ? የሞቱትን በክብር ለማስታወስ፣ የተጎዱትን ለማመስገን፣ ያጠፉትን ለመውቀስና ለማስተካከል ሲሆን፣ የአሁኑና የወደፊቱ ትውልድ ሰዎች የተሰዉበት ዓላማ ጠርቶ እንዲታየው ለማድረግ ነው፤ ይህንን አንድ ሰው በራሱ ላይ የጫነውን ማኅበራዊ ግዴታ እንዳይወጣው እንቅፋት መሆን አገርንና ወገንን መበደል ይሆናል፡፡

በእኔ አስተሳሰብ አቶ አስገደ የሁላችንም ድጋፍ ሊኖረው ይገባል፤ ምስክሮችን ከያሉበት ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ተረዳድተን ብንከፍልለት የኃላፊነታችንን ድርሻ የምንወጣ ይመስለኛል፤ የምሰብከው በተግባር የፈጸምሁትን ነው፤ ለእውነት መቆማችንን ለማስመከር ዋጋ መክፈል ከአለብን ወደኋላ ልንል አንችልም፤ አቶ አስገደ በትግራይ የተካሄደውን ትግል የኢትዮጵያዊነት መሠረትና መልክ የኢትዮጵያ ሕዝብ በትክክል እንዲገነዘበው ይጥራል፤ ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ፤ በትግራይ የተጀመረውን የትግል ዓላማ በትክክል ስለሚያውቀው እንዴት እንደተለወጠና አጓጉል እየሆነ እንደሄደ ሲናገር የማይወዱለት አሉ፤ በበኩሌ የእነሱንም መብት አከብራለሁ፤ የእነሱ መብት የሚሆነው የራሳቸውን በኩል በሙሉ ነፃነት መናገር እንጂ አቶ አስገደን ማፈን ወይም ማሳፈን አይደለም፡፡

በእኔ አመለካከት በአለፉት ሃያ አንድ ዓመታት የወያኔ/ኢህአዴግ አገዛዝ ውስጥ አንዳንዴ ቢሰናከልም ትልቁና ዋናው ጥቅም የጽሕፈት እገዳው መነሣት ነው፤ ይህ ነፃነት ሲጠፋ ጥፋቱ ሁሉ ሙሉ ይሆናል፡፡

---

# ጠላታችን ማነው?

ዓለማየሁ ገላጋይ

ሮማዊው የታሪክ ሰው Tranquillus suetonius (75-150)ዓ.ም “Lives of the twelve Caesars” የሚል መጽሐፍ አለው፡፡ የአሥራ ሁለት ቄሳሮችን ስንክሳር ያካተተበት ሥራው ነው፡፡ ከእነዚህ ቄሳሮች መካከል ‹‹እብዱ›› በሚል ተቀጥላ የሚጠራው ካሊጉላን (Caligula) ነው፡፡ በእርግጥም አንዳንድ የቄሳሩ ተግባሮች ጤነኞች የሚያከናውኗቸው አይደሉም፡፡ ለምሳሌ መኳንንቱና ሹማምንቱ እንዲሁም መሳፍንቱ በተገኙበት አዳራሽ ውስጥ ሚስቱ ቄሶኒያ (Caesonia) እርቃነ-ሥጋዋን እንድትመጣ ያዝዛታል፡፡ ልብሷን ጥላ እራቁቷን ስትመጣ የአዳራሹን ሁናቴ ይቃኛል፡፡ ከዚህ የሚያገኘውን ትርፍ እራሱ ካሊጉላ ይወቀው፡፡ ሌላም የእብድ መዝናኛ አለው፡፡ በመኳንንቱ ፊት መኳንንቱ እርስ በእርስ ትግል እንዲገጥሙ ማዘዝ፡፡ አንዱ ይጥላል፣ ሌላው ይወድቃል፡፡ ካሊጉላ ይስቃል፡፡ ቄሳሩ ከሳቀ የተቀረው መኳንንት አያኮርፍም-አብሮ ያውካካል፡፡ ከዚህ ትዕይንት ካሊጉላ የሚያተርፈው መዝናናትን ብቻ አልነበረም፡፡ ፖለቲካዊ ረብጣም አለው፡፡ የወደቀው መኳንንት በጣለው መኳንንት ላይ ያቄማል፤ ጠላትነትም ያበቅላል፡፡ እርስ በእርስ ተፈላላጊ ይሆናሉ፡፡

ወደኛ አገር እንምጣ…

…ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ተክለማሪያም ‹‹ኦቶባዮግራፊ (የህይወቴ ታሪክ)›› የተሰኘ መጽሐፋቸው ላይ የሚያስተዋውቁን ልጅ ኢያሱም የካሊጉላ ከፊል መንፈስ ያረፈባቸው ናቸው፡፡ የተከበሩትን መኳንንቶች ለእረኝነት እንደወጣ ኩታራ ትግል ያጋጥሟቸዋል፡፡ ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹… ታዲያ ልጅ ኢያሱ ቀኛዝማች ወልደአማኑኤልንና ቀኛዝማች ፋሪስን አታገሏቸው፡፡ ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል በንቀት አስተያየት እያየ ተጋጠመ፡፡ (ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል በራስ መኮንን ቤት ጉልበታምነቱ የታወቀ ነው፡፡) ቀኛዝማች ፋሪስ ጣለ፣ ልጅ ኢያሱ እያጨበጨቡ ደስታቸውን ገለጡ፡፡ እኛ ግን ዐፈርን፡፡ ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል ተገረመና እንደገና ታገሉ፡፡ ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል ጣለ፡፡››

በፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ግምጋሜ ልጅ ኢያሱ ለመቦረቅ ያመጡት የልጅነት ፍላጐት እንጂ የመኳንንቱን ትግል መግጠም በፖለቲካ ትርፍነት አይተውት አልነበረም፡፡ ይሁንና ለታዛቢዎቹ ለእነፊታውራሪ ተክለሐዋርያት ትግሉ ከግለሰቦች አልፎ ብሔርና ሃይማኖት ተኮር ሆኖ ተተርጉሞላቸዋል፡፡ በቅንፍ ውስጥ ይሄንን ትርጓሜ ጣል ያደርጋሉ፡፡ ‹‹በልባችን ውስጥ የሚታገሉት ወልደአማኑኤልና ፋሪስ አይደሉም ሸዋና ወሎ፣ ክርስቲያንና እስላም ናቸው (አልን)›› ይላሉ፡፡ የዚያ ወቅት ፖለቲካ ይሄው ነበር፡፡ ከሸዋ ወገን እነደጃዝማች ተፈሪ (ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ)፣ ከወሎ እነራስ አሊ (ንጉስ ሚካኤል) የተፋጠጡበት፡፡ ትውልዳቸውንና ሃይማኖታቸውን የወከሉት ቀኛዝማቾች በግጥሚያው አንድ ለአንድ ባይወጡ ምን አይነት ቂም ውስጣቸው ይፈጠር ነበር? በእንዴት አይነት ሁኔታስ ወደበቀል ይለወጥ ነበር?

አብዛኛው መንግሥት የራሱን ፖለቲካዊ ሁኔታና ሥልጣን የሚያስጠብቀው ትኩረት የሰጠባቸውን ‹‹ቀኛዝማች ወልደአማኑኤል እና ቀኛዝማች ፋሪስ›› በጠላትነት አኳኩኖ በማታገል ነው፡፡ ለምሳሌ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን የነበሩ ትግል ገጣሚዎች ‹‹በተወላጅነት›› እና ‹‹በትምህርት›› ሥልጣን የያዙ ሁለት ቡድኖች ነበሩ፡፡ የእነዚህ ቡድኖች ጠላትነት በአፄ ኃይለሥላሴ የሥልጣን ማስጠበቅ ፖለቲካዊ ፍላጐት የተፈበረከ ቢሆንም ደርግ እስኪመጣ ድረስ እንደተናነቁ ሥራ መሥራት ተስኗቸው ቆይተዋል፡፡ አንዴ አንዱ ሲጥል አፄ ኃይለሥላሴ እንደልጅ እያሱ ያለ ግን ስውር ጭብጨባ በማካሄድ ደስታቸውን ሲገልጡ፤ ሌላ ጊዜ ሌላው ሲጥል እንዲሁ ሲደረግ በመካከል ዋነኛው የንጉሱ ሥልጣን ከመካከላቸው የሚማትረው ሳይኖር ለረጅም ጊዜ ቆይቷል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ባህሩ ዘውዴ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹የአብዛኛዎቹ ሚኒስትሮች የመደብ ጀርባም በንጉሰ ነገሥቱ ፊት ነፃ አቋም ለመውሰድ የሚያደፋፍር አልነበረም፡፡ ብዙዎቹ የመሣፍንት ወገን ባለመሆናቸውና ሹመቱና ክብሩንም በቀጥታ ከንጉሠ ነገሥቱ ያገኙ በመሆናቸው ታማኝነታቸው የተረጋገጠ ነበር፡፡ በዚህም አኳኋን ንጉሠ-ነገሥቱ ሚኒስትሮቹን የመሣፍንቱን ኃይል ለመቋቋም አይነተኛ መሣሪያው አድርጓቸው ነበር፡፡ የድህረ 1933 የኢትዮጵያ ፖለቲካ አንዱ ገፅታ ይህ በመኳንንቱና በመሣፍንቱ መካከል ይካሄድ የነበረው ስውር ትግል ነበር ማለት

> ያታገለንን ትተን የታገለንን አልጠላንም? ከመታገላችን የሚያተርፈውን ‹‹የፖለቲካ ቁማርተኛ›› አልፈን የኛ ብጤ ሰለባውን ጠላት አላደረግንም? ለመሆኑ ጠላታችን ማነው?

ይቻላል፡፡›› (‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ…›› ገፅ 213)

በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በጠላትነት ትግሉን የገጠሙት ከመኳንንቱ ወገን ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ ሲሆኑ ከሚኒስትሮች ወገን ደግሞ የእርሻ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር የሆኑት መኮንን ኃብተወልድ ናቸው፡፡ ሁለቱም በሥራቸው የስለላ ቡድን በማቋቋም አንዱ የሌላውን ድክመት ሲያነፈንፍ ይውልና ያድር ነበር፡፡

በደርግ ዘመን ‹‹ቀኛዝማች ወልደአማኑኤልም ሆነ ቀኛዝማች ፋሪስ›› እራሱ ደርግ ነበር፡፡ ለጠላት ሌላ ጠላት ፈጥሮ ከማታገል ይልቅ አድሀሪ፣ በዝባዥ፣ ከላሽ፣ ቀልባሽ፣ ገንጣይ፣ አስገንጣይ… የሚለውን እራሱ እጅጌውን ሰብስቦ ይገጥማል፡፡ ከጣለ በኋላ በአዋጅ ይፎክራል፡፡ የሚወረሰውን እራሱ ይወርሳል፣ የሚገደለውን እራሱ ይገድላል፣ የሚሾመውን እራሱ ይሾማል…፡፡ በሽኩቻ ጠላት በጠላት እስኪጣፋ አይጠብቅም፣ ትዕግሥት የለውም፡፡ ዘው ብሎ እራሱ አጣጥሞ ቁልጭ ለማለት ይፈጥናል፡፡

ወደዚህ ዘመን እንምጣ…

…ከሁሉም ዘመን እጅግ የከፋው የዚህ ወቅት ሽኩቻ ነው፡፡ ያለማጋነን ህዝቡ እንዳለ ‹‹ቀኛዝማች ወልደአማኑኤሎችንና፣ ቀኛዝማች ፋሪሶችን›› እንዲሆን ተጥሯል፡፡ በብሔር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በክልል አስተዳደር፣ በፖለቲካ… እየተናነቀ ሙሉ ትኩረቱን አጠገቡ ያለ ወገኑ ላይ እንዲያደርግ እየተሴረ ነው፡፡ በገዢዎች የተመደበለትን ተጋጣሚ የመጣል ባዕድ ትልም ግቡ አድርጐ እንዲቀርና ወደላይ እንዳያማትር በዕለት ተዕለት ሽኩቻ እርስ በእርሱ እንዲጠላለፍ ተደርጓል፡፡ ከበድ ያሉትን አገር አቀፍ ጉዳዮች ትተን በህግ፣ በፖሊሲና በደንብ እየታከኩ የሚጠሩትን የእርስ-በርስ ጠላትነቶች እንመልከት፡፡

የልማት ተነሺ በመሆናችን ስንት የቀበሌ ነገሥታት እያጣደፉና እያከፉፉ እንድንጠላቸው አደረጉን? መኖሪያችንን በላያችን ላይ ለማፍረስ ሲቋምጥና ሲቁነጠነጥ በማየት ስንት አፍራሽ ግብረኃይል ላይ ቂም ያዝን? ስለመፈናቀሉ በመደስኮር በቁስላችን እንጨት እየሰደደ ስንቱ ጠላታችን ሆነ? በቤት ግምት ወሽመጣችንን ከቆረጠ ስንት ባለስልጣን ጋር ተቂያቂያምን? ያልተገባ፣ የተጋነነ የቤት ግምት የወሰደ ስንት ጐረቤት ታዘብን?…

….ደግሞ በተከራይ አከራይ ያልተብላላ ደንብ ስንቱ ተባላ? ስንቱስ ስንት የዘለአለም ባላጋራ አፈራ? ምን ያህሉስ ለመጋደል ተፈላለገ? እኔ እንኳን ሦስት አሰቃቂ የተከራይ አከራዮች ጭፍጭፍ አጋጥሞኛል፡፡ ሃያ ሁለት አካባቢ ገብርኤል ሆስፒታል መስመር፣ አትክልት ተራ እና ካሳንቺስ፡፡ ካልወረስክ መንግሥት ይወርሰዋል የተባለ ተከራይ ምርጫ በማጣት ከአከራዩ ጋር ጥርስ ከተናከሰ በኋላ እንደገና መልስለት በሚል የመንግሥት ትዕዛዝ ነው እንደጐሣ ወረራ በገጀራ ሲጨፋጨፉ የታዩት፡፡

….እናስ? ልጅ ኢያሱ ያታገሏቸውን ቀኛዝማች ወልደአማኑኤልንና ቀኛዝማች ፋሪስን አልሆንም? ያታገለንን ትተን የታገለንን አልጠላንም? ከመታገላችን የሚያተርፈውን ‹‹የፖለቲካ ቁማርተኛ›› አልፈን የኛ ብጤ ሰለባውን ጠላት አላደረግንም? ለመሆኑ ጠላታችን ማነው?

# የአልበሽርን ለፍርድ መቅረብ እንደግፋለን!

ቀጣዩን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ ማላዊ ለማዘጋጀት ኃላፊነቱን ወስዳ የነበረ ቢሆንም በዘር ማጥፋትና በሰው ልጆች ላይ በሚፈፀም ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት /ICC/ የሚፈለጉትን የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ኦማር ሀሰን አልበሽርን ይዛ የምታስረክብ መሆኗን በመግለጿ ስብሰባው ወደ አዲስ አበባ እንዲዘዋወር መደረጉ አሳሳቢ ጉዳይ ነው።

አፍሪካውያን ቅኝ ገዢዎቻቸውን ለመጣል ረጅም ርቀት በመጓዝ ደም አፋሳሽ በሆነ ጦርነት ውስጥ አልፈዋል። ይሄንን በድል ቢወጡትም በውጪ ወራሪዎች እግር የተተኩት መሪዎቻቸው ግን ስልጣንን መከታ በማድረግ የቀድሞውን ምሬት መልሰው ሲፈጥሩባቸው እዚህም እዚያም የተስተዋለ እና እየተስተዋለ ያለ ሀቅ ነው።

ምንም ፋይዳ ያለው ነገር ለአህጉሪቱ ዜጎች አልሰራም በተባለው በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቦታ የአፍሪካ ህብረት ቢተካም ለአህጉሪቱ ህዝቦች ጥቅም መስራት ከሚጠበቅበት አንፃር እዚህ ግባ የሚባል ስራ ሲሰራ አልታየም። ዛሬም መንግስታዊ ግፍ፣ በደልና ሰቆቃ የአህጉሪቷ መገለጫዎች ሲሆኑ፤ ከዚህም አልፎ አምባገነን መሪዎች በሙስና ሲዘፈቁ እና የዜጎቻቸውን መብቶች ሲደፈጥጡ ህብረቱ አይቶ እንዳላየ መሆንን መርጧል። በዚህና በሌሎች ተያያዥ ምክንያቶች የተነሳ የአፍሪካ ህብረት የነፃ ህዝቦች የትብብር ምልክት ከመሆን ይልቅ የመሪዎች ንብረት የሚመስልበት ገፅታው ጎልቶ ሲወጣ ችሏል።

የህብረቱ አባል ሀገራት መሪዎች በሚመሩት ህዝብ ላይ እንዳሻቸው የሰብዓዊ መብትን እየረገጡ፣ የፖለቲካ ጥያቄዎችን በሀይል እየጨፈለቁ እና በጠራራ ፀሀይ የምርጫ ድምፅ ሲያጭበረብሩ ትንፋሹ የማይሰማው ህብረቱ ዛሬ ደግሞ የለየለት አምባገነን ከመሆንም አልፎ በራሱ ሀገር ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈፅሞ በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ክስ የተመሰረተበትን መሪ ለመከላከል ሲል ብቻ ስብሰባው ወደ ሌላ ሦስተኛ ሀገር እንዲዞር በሱዳን መንግስት ሲጠየቅ የኢትዮጵያ መንግስት ፍቃደኝነቱን በመግለፁ አዲስ አበባ ላይ እንዲሆን ተስማምቷል።

በአፍሪካ ደረጃ እንኳን ከ30 በላይ ሀገራት የዓለም አቀፍ ወንጀል ችሎትን በፊርማቸው ሲያፀድቁ ኢትዮጵያን ጨምሮ ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት ብቻ ተለይተው አለመስማማታቸው ጥያቄን ያጭራል። ፍትህ የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ውል ያልፈረመበትን ምክንያት ግልፅ እንዲያደርግ ትጠይቃለች። ምንም እንኳን አፈፃፀሙ ላይ እንከን እንደማያጣው የሚታማ ቢሆንም፤ ሌሎች ሰብዓዊ መብቶችን የሚመለከቱ ቁጥራቸው የበዛ ሰነዶችን በመፈረም የሰነዶቹን ዕሴቶች የህገ-መንግስቱ አካል ያደረገው የኢትዮጵያ መንግስት ይህንን ሰነድ ላለመፈረም ያገደውን ችግር በአደባባይ ሊገልፅ ይገባዋል።

በፍትህ እምነት መንግስት ይህን ተቋም ከሌሎቹ አንፃር በተለየ ሁኔታ ቅቡልነት የነፈገበትን ምክንያትም ሆነ ከተቋሙ ጋር ለመተባበር ያልፈቀደበትን ምክንያት ለዜጎቹ ሊያስረዳ ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘው ፍርድ ቤት / ችሎት/ በዘር ማጥፋት ለሚፈለግ መሪ ሲባል ስብሰባው እንዲዞር ሲወሰን ኢትዮጵያ መተባበሯ ለዓለም አቀፍ ወንጀለኞች የተደረገ የፖለቲካ ድጋፍ ማሳያ እንዳይባል የተደረገ ጥንቃቄ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ማሳወቅ የግድ ይላል። ለዚህም የሚመለከተው የሚኒስትር መስሪያ ቤት ምላሹን እንዲሰጥ ፍትህ አጥብቃ ትጠይቃለች።

በአጠቃላይ ፍትህ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ በአለም አቀፉ ፍርድ ቤት የእስር ዋራንት የተቆጠረባቸውን የሱዳኑን ፕሬዚዳንት ኦመር ሀሰን አልበሽርን ለፍርድ ቤቱ አሳልፎ በመስጠት ለህግ የበላይነት እና በሰው ልጆች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመቃወም ያለውን ቁርጠኝነት እንዲያሳይ ትጠይቃለች። የፕሬዚዳንቱንም ለፍርድ መቅረብ ትደግፋለች።

## አስተያየት

# የአቶ አሥራት ጣሴ የሴራ ፖለቲካ

ታምራት ታረቀኝ

በቅድሚያ ለፍትሕ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልና ለጋዜጣው አንባቢያን የከበረ ሰላምታዬን አቀርባለሁ። የጠፋሁት ሰው ዛሬ ብቅ ለማለት ምክንያት የሆነኝ ግንቦት 24/2004 ዓ.ም. የተነበበው የአቶ አስራት ጣሴ ጽሑፍ ነው። አቶ አሥራት ለመጻፍ ምክንያት የሆናቸው ፕ/ር መስፍን ‹‹ተቀናቃኝ ቡድኖችና ፖለቲካ›› በሚል ርዕስ ግንቦት 10/2004 ዓ.ም. በፍትህ ጋዜጣ ያስነበቡት ጽሑፍ እንደሆነ ገልጸው ‹‹ዓላማዬ ስለአንድነት ፓርቲ የማውቀውን ጥቂት እውነታዎች ለአንባቢያን ለማጋራት ነው›› ቢሉም ጽሁፉ ግን እዚህና እዚያ እየረገጠ ብዙ ጉዳዮችን የነካካ፣ ከእውነት የተቃረነ አንብበው እንደተናደዱ የጻፉት ነው የሚመስለው። ሌላ ካልሆነ በስተቀር የፕ/ር ጽሁፍ አቶ አሥራትን ለይቶ የሚያናድድ አልነበረም።

አንድነትን ከጥንስሱ አንስቶ ለእነ ዶ/ር ነጋሶና አቶ ስዬ ተላልፎ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ የነበረውን የቀን ተቀን ሂደት ለሚያውቅ እንደኔ ላለ ሰው የአቶ አሥራትን ጽሑፍ አንብቦ በዝምታ ለማለፍ ህሊናው የማይፈቅድ በመሆኑ ነው ወደ ራቅኳት ፍትሕ ብቅ ማለቴ። ቢሆንም ስለአንድነት የማውቀውን ሁሉ ለመናገር አልሞክርም፤ በጋዜጣ ተጽፎ አያልቅምና። ስለፕ/ር መስፍን ያሉትም ከእውነታው ተቃራኒ መሆኑን ለመመስከር አልዳዳም። ፕ/ር ተግባራቸው ስለሚያረጋግጥ። ስለቅንጅት የነካኩትንም አልነካውም ብዙ የተባለበትና የተጻፈበት ስለሆነ። አቶ አሥራት አንድነት ውስጥ የፈጸሙትን ሴራም አልዘረዝርም፣ የዛሬ ጉዳዬ አይደለምና። ስለሆነም በዚህች ጽሑፍ የማነሳው አዛብተው ባቀረቡዋቸውና ዋሽተው በገለጹዋቸው ጉዳዮች ውስጥ የሚታየውን ሴራ ይሆናል። አቶ አሥራት ጣሴ ‹‹በፖለቲካ ትግል ውስጥ ቁም ነገሩ አሸናፊ ሆኖ መገኘቱ በመሆኑ የፖለቲካ ሰው ይህን ውጤት ለማግኘት በማንኛውም ዘዴ (ውሸት ጭካኔ ወዘተ) መጠቀም አለበት›› የሚለውን የሚኪያቬሊ መርህ ተግባራዊ ካደረጉ የሀገራችን ፖለቲከኞች አንዱ ናቸው። ለዚህ ደግሞ የራሳቸው ጽሑፍ በቂ ማስረጃ ነው።

**አምስት ሰዎችን የያዘ ኮሚቴ ግንቦት 1/2001 ዓ.ም. ለብ/ም/ቤቱ ስላቀረበው ሪፖርት፡-**

አቶ አሥራት የጻፉት የሆነውን ሳይሆን እሳቸው እንዲሆን ይፈልጉት የነበረውንና ያልተሳካውን ነው። የሆነው ግን እንዲህ ነበር። የፓርቲውን ችግር በውይይት ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች በሥራ አስፈፃሚው በተለይ በአቶ አሥራት እምቢተኝነት ሲከሽፍ በብሔራዊ ምክር ቤቱ በኩል ለመሞከር በርካታ የም/ቤት አባላት የተሣተፉበትና በሶስት ሰዎች የተፈረመ (አንዱ ፈራሚ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም ናቸው) ችግሮችንና መፍትሄዎቻቸውን ያመላከተ ጽሑፍ ሚያዝያ 03/2001 ዓ.ም. ለምክር ቤቱ ቀረበ። ምክር ቤቱ በቀረበለት ጽሑፍ ላይ እንዳይወያይ የተለያዩ ሰበቦች እየፈጠሩ ከተከራከሩት አንዱ አቶ አስራት ነበሩ። ይህ አልሳካ ሲል ማንበብ ስላለብን ዛሬ ልንወያይበት አይገባም አሉ። ይሄኛው በአብላጫ ድምጽ አሸንፎ ስብሰባው በማግስቱ እሁድ ሶስት ሰዓት እንዲቀጥል ስምምነት ላይ ተደረሰ።

ምክር ቤቱ እሁድ ሚያዚያ 4/2001 ዓ.ም. ባካሄደው ውይይት የቀረበውን ጽሑፍ መርምሮና ከፓርቲው እንቅስቃሴ ጋር አገናዝቦ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብለት አምስት አባላት ያሉት ኮሚቴ አቋቋመ። የኮሚቴው አባላትም ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ፣ አቶ አክሉ ግርግሬ፣ አቶ ሙሉጌታ ወንድምአገኝ፣ አቶ እንዳልካቸው ሞላ እና አቶ ድንቁ ነበሩ።

ይህ ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራ በጀመረበት ወቅት አቶ አስራት ጣሴ ሚያዚያ 13/2001 ዓ.ም. ከአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ጋር በአደረጉት ቃለ ምልልስ ‹‹ውይይት ላለማድረግ ወስነናል። አንዳንዴ ፖለቲካዊ ውሳኔ ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ። ደንብን የጠበቀ አሰራር የት ያደርሰናል የሚለው አሳሳቢ ሆኖብናል›› በማለት በእሳት ላይ ቤንዚን ጨመሩ።

የኮሚቴው ሰብሳቢ ሆነው የተሰየሙት አቶ አክሉ ግርግሬ ኮሚቴው ስራውን እንደጀመረ ወደ አሜሪካ ሲሄዱ ቀሪዎቹ የኮሚቴ አባላት ከተሰጣቸው ጊዜ አሳልፈው ግንቦት 1 ቀን 2001 ዓ.ም. ሪፖርታቸውን ለምክር ቤቱ በንባብ አቀረቡ። ሥራ አስፈፃሚን ለመከላከል የቀረበ ለመፍትሄ የሚያግዝ ሳይሆን ችግር የሚያባብስ ሪፖርት የሚል ተቃውሞ ገጠመው። ሪፖርቱ ተባዝቶ ለምክር ቤቱ አባላት እንዲሰጥና ስብሰባው ግንቦት 8/2001 እንዲሆንም ተወሰነ። በግንቦት 8/2001ዓ.ም ስብሰባ እነ አቶ አሥራት የኮሚቴው ሪፖርት እንዲጸድቅ አጥብቀው ቢከራከሩም ምክር ቤቱ በሪፖርቱ ላይ የቀረበውን ተቃውሞ በማጤን ሁለቱን ሰነዶች (ከምክር ቤቱ አባላት የቀረበውንና የኮሚቴውን ሪፖርት) ጎን ለጎን እያመሳከረ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ መወሰንን ምርጫው አደረገ። በዚህ ሁኔታ ውይይቱ ሙሉ ቀን ተካሂዶ ባለማለቁ በይደር ተቀጠረ። በማግስቱ ገና ከጅምሩ ስብሰባው ውጥረት የነገሰበት ሆነ። የውይይቱ መንፈስ ያላማራቸው ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም የመናገር እድል ጠይቀው ሲፈቀድላቸው ‹‹ተጨንቄአለሁ፤ ዓላማ ያለን ከሆንን እዚህ ቦታ የተሰባሰብነው የሰውም የሰነድም ማስረጃ ሲቀርብ እናጣራ፣ እንይ፣ እናረጋግጥ፤ መፍራት የለብንም። ተሳስቻለሁ የሚል ካለ ይቅርታ ማድረግ ነው። አሁን ግን ብዙ የመካካድ የመካሰስ ነገር አለ። ዓላማችን አንድ ካልሆነ እንድንነታረክ የሚያደርገን ምንድን ነው? አንድ ግለሰብ ካጠፋ ተነግሮት መታረም፣ አሰራሩ ያልተስተካከለ ከሆነ ማረም፣ የአሰራር ብልሹነት ነው እናርመው እናስተካክለው ብለን በዚህ እንኳን መስማማት የማንችል ሰዎች ምን እንሰራለን? ዳኝነት በሌለበት የምንጨቃጨቅ ከሆነ በዚህ አጀንዳ ለውጤት አንደርስም። እኔ ሀሳብ ስጥ የምትሉኝ ከሆነ አንዱ በዚህ ሌላው በዛ ተናዷል። ስለዚህ እናቁመውና ሶስት አራት እየሆንን እንወያይ። በፀሎት እንጀምር ለማለት አስቤ በጎ መንፈሥ አልነበረም አልገፋፋኝም። እናቁመው እየተፈላለግን እንነጋገር። ከአንድ ሳምንት በኋላ በጥሩ መንፈስ እንነጋገርበት፤ አሁን ያለው መንፈስ ወደ መጥፎ ስሜት እያመራን ነው።›› በማለት ጭንቀታቸውን ተናገሩ። ይህ ሀሳብ ደጋፊ የማግኘቱን ያህል ተቃዋሚም ስላላጣ ድምጽ ተሰጥቶ ውድቅ ሆነ። ውይይቱም ቀጥሎ ሃያ ሁለት የሚደርሱ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ከምሽቱ 12 ሰዓት ተጠናቀቀ። ብዙዎች ውይይቱ በዚህ መልክ በመጠናቀቁ ተደሰቱ። የምክር ቤቱን ውሳኔዎች ስራ አስፈፃሚው ተግባራዊ ያደርጋል ብለው በማመንም የፓርቲውን ችግር ይፈታል የሚል እምነት አሳደሩ። አቶ አሥራትን ጨምሮ ጥቂቶች ግን ደስተኛ አልነበሩም። እናም በተካኑበት የሴራ አሰራር ውሳኔው ተግባራዊ እንዳይሆን ውሳኔ የተላለፈበት ቃለ ጉባኤም እንዳይጸድቅ አደረጉ። ይህ አድራጎታቸውም የአንድነትን ችግር ለአደባባይ አበቃው።

**የእርቀ ሠላም ድርድር ተካሂዶ የስምምነት ሰነድም ተዘጋጅቶ ያለመታደል ሆኖ ውጤታማ ሳንሆን ቀረን።**

ድርድሩም ሰነዱም እውነት ነው። ውጤታማ ያልሆነው ግን ባለመታደል ሳይሆን በአቶ አስራት ሴራ ነው። ነገሩ እንዲህ ነው። በአቶ ይልማ ይፍሩ አገናኝነት እኔና አቶ ይልቃል ጌትነት (አሁን የሠማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር) ከአቶ አንዱዓለም አራጌ ጋር (በወቅቱ የአንድነት ዋና ጸሐፊ ነበር) ባምቢስ ከአንድ ቡና ቤት ተገናኝተን ተነጋገርን። በእኛ በኩል አቶ ሰዒድ አብራሂምንና አቶ ስለሺ ፈይሳን ጨምረን በእሱ በኩል ደግሞ ወ/ሮ ላቀችና አቶ ተመስገን ዘውዴን ጨምሮ በአቶ ይልማ አማካኝነት ግንኙነታችን እንዲቀጥል ሁለታችንም ውክልና የሌለን በመሆኑ የምንነጋገረው በራስ ተነሳሽነት እንደሆነ አንድ ውጤት ላይ ስንደርስ ሁለታችንም ውሳኔ ሰጪ ለሆኑት አካላት እንደምናቀርብ እስከዚያ ድረስ ግን ምስጢራዊነቱ እንዲጠበቅ ንግግራችን በቃለ ጉባዔም ሆነ በማስታወሻ እንዳይመዘገብ ተስማማን።

ከብዙ ጥረት በኋላ አንድ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሁለቱም ወገን ቀረበ። የእነ አቶ አሥራት ወገን ሰነዱን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ዶ/ር ኃይሉን፣ አቶ አሥራትንና አቶ አንዱዓለምን የያዘ ኮሚቴ አቋቋመ። ከጅምሩ የተለየ ሀሳብ ያላቸውን አባላት በዐይናቸው ለማየት የሚጠሉትና ከማንም ጋር አንወያይም ብለው ያወጁት፤ የሚጀመሩ ውይይቶችንም በተለያየ ሴራ የሚያከሽፉት አቶ አሥራት ጣሴ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሌላኛው ወገን ቀርቶ ሶስቱ የኮሚቴ አባላት እንኳን በአንድ ድምጽ ሊስማሙበት ያልቻሉትን ጽሑፍ አዘጋጅተው ለሥራ አስፈፃሚያቸው አቀረቡ። ሥራ አስፈጻሚው ደግሞ የኮሚቴው አባላት ተግባብታችሁ ያላመጣችሁትን ሰነድ አላይም በማለት ውሳኔ ሳይሰጥ ቀረ። ከዚህ በኋላ ሂደቱን ለማስቀጠል የተደረጉ ጥረቶች ሁሉ በአቶ አሥራት ጣሴ ግንባር ቀደም ተከላካይነት ሳይሳኩ ቀሩ።

**‹‹በአንድ አጋጣሚ ሥልጣን ቢያገኙና ወታደር ቢያዙ፣ በሀሳብ የሚለዩዎትን እና የማይደግፍዎትን ሰው ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ሳስብ በጣም ይዘገንነኛል››**

ኧረ! ወዴት ወዴት! የማንን ተግባር ለማን? ይሄ ራሳቸውን ጸሐፊውን ነው የሚመለከተው። ማስረጃ ራሳቸው በአንደበታቸው ሚያዝያ 13/2004 ዓ.ም. በአውራምባ ጋዜጣ አማካኝነት ‹‹አንወያይም የፖለቲካ ውሳኔ እንወስናለን›› ሲሉ ተናግረዋል። የፖለቲካ ውሳኔ ምን እንደሆነ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ግልጽ ነው። አቶ አሥራት ከመሰሎቻቸው ጋር ሆነው በሀሳብ የተለዩትን ከፓርቲው እንዲባረሩ አድርገዋል። እሰሩልን በማለት ለፖሊስ በተደጋጋሚ አመልክተዋል። በፓርቲው ጽ/ቤት ግቢ ውስጥ አባላትን በአባላት አስደብድበው ደም እንዲፈስ አድርገዋል። ምርጫ አዋኪ በማለት አባላትን ከሰው 11 ሰዎችን ለስድስት ቀን አሳስረዋል። በሀሳብ የተለዩ አባላትን ድንጋይ ወርዋሪና ሁከት ፈጣሪ ብለው ከሰው ፍርድ ቤት አቁመዋል። በግንቦት ሰባት አባልነት የሚጠረጠሩ በማለት የአባላትን ህልውና ለአደጋ አጋልጠዋል። ‹‹ባእድ አካላት››፣ ‹‹ሰርጎ ገብ እና ‹‹የብርቱካን ወንበር ጠባቂዎች›› ወዘተ እያሉ በመፈረጅ በአባላት መካከል አለመተማመን እንዲሰፍን አድርገዋል። ያሉበት የስልጣን ደረጃ የሚመኙትን ለመፈጸም የማያስችል መሆኑ በጀ እንጂ እንደ አቶ

ወደ ገፅ 11 ዞሯል »

ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

የአሳታሚው አድራሻ
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

ሥራ አስኪያጅ
ማስተዋል ብርሃኑ

ዋና አዘጋጅ
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

አዘጋጆች
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ኤልያስ ገብሩ

ሪፖርተሮች
ሰውዓለም ታዬ
ሚካኤል ዲኖ

አምደኞች
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ
አለማየሁ ገላጋይ
ብርሀኑ ደቦጭ
ኤፍሬም ስዩም
እንዳለጌታ ከበደ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ታዲዮስ ታንቱ

ግራፊክስ ዲዛይን
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

የሽያጭ ሰራተኞች
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

አታሚ
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ፡- አራዳ
ቀበሌ፡- 17
የቤት፡- 984

# የጠፋው ትውልድ እና የታህሪር ናፍቆት-፪



ተመስገን ደሳለኝ

ማን ይፈራል ሞት
ማን ይፈራል
ለእናት ሀገር ሲባል...

(ይህንን መዝሙር ያደመጥኩት በዘንድሮ አመት የግንቦት ሃያ ዋዜማ ላይ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በ1985 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተደርጎ የነበረ የተቃውሞ ሠልፍ ብሎ እንድንመለከተው ከጋበዘን ፕሮግራም ላይ ነው ። የኢቲቪ ዓላማ ‹‹ኢህአዴግ ያሸነፈው ደርግን ብቻ ሳይሆን ስልጣን ከያዘ በኋላ ይነሱ የነበሩ ተቃውሞዎችንም ነው›› የሚል መልዕክት ማስተላለፍ ነው)

በእርግጥ ዛሬ የነበረው አፈና እና እስር በዛን ወቅትም ነበረ፡፡ ነገር ግን እንዲህ እንደዛሬው ለተቃውሞ አደባባይ መውጣት ቀርቶ ገዥውን ፓርቲ ድምፅን ከፍ አድርጎ ማማት የሚያስፈራበት ደረጃ ላይ ገና አልተደረሰም፡፡ የምዕራባውያኖችም አድናቆት በህወሓት አመራር ቆሌ ላይ ያረፈበት በመሆኑ በበረኸኞቹ ባለስልጣናት ላይ ‹‹ሆደ ሰፊነት›› የሚስተዋልባቸው ጊዜያት ይበዛሉ፡፡ ለዚህም ይመስለኛል በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ የተሸለሙ ግዙፍ ሠልፎች ላይ ሳይቀር ‹‹ማን ይፈራል ሞት ማን ይፈራል?››ን የመሳሰሉ ሀገራዊ እና ቀስቃሽ መዝሙሮችን በድፍረት እንሰማ የነበረው፡፡

## ‹‹We will be back soldiers››

‹‹እንመለሳለን! ወታደሮች›› የምትል ግጥም የት እንዳነበብኩ ትዝ አልልህ አለኝ፡፡ የግጥሟ ባለቤት ከቼ ጉቬራ ጋር በቦሊቪያ ጫካ የመጨረሻውን ጦርነት የተካፈለ አንድ ወታደር ነው፡፡ በዛ አሳዛኝ ጦርነት እነ ቼ አስራ ሰባት ሆነው ነበር በአሜሪካ ይደገፍ ከነበረው የቦሊቪያ መንግስት ወታደሮች ጋር የተፋለሙት፡፡ በዚህ የጀብደኞች ውጊያ የመጨረሻ ውጤትም ቼ ተማረከ፡፡ ይህ ገጣሚ ወታደርም እንደ እድል ሆኖ ከጦርነቱ ተረፈ፡፡ ከዚህ በኋላም ነው የተጀመረው ህዝባዊ አብዮት መቀጠሉ እንደማይቀር ሌሎች አጋሮቹን ሲያፅናና ‹‹እንመለሳለን! ወታደሮች›› ያላቸው-በግጥሙ፡፡ ...የያ ትውልድ ተጋሪው ነብይ መኮንንም ‹‹ እንመለሳለን! ጓዶች›› የምትል በእንግሊዝኛም በአማርኛም የተፃፈች ግጥም አለችው፡፡ ነብይ ይህችን ግጥም የገጠመው ጉራማይሌው ድርጅቱ ኢህአፓ እንዲህ ተበትኖ ይቀራል ብሎ ባለማሰቡ ተስፋ ሰንቆ ይሆን? ወይስ ስሙ ብቻ የቀረው ተወዳጁ ፓርቲ ተመልሶ መጥቶ ይህንን ትውልድ ያነቃቃል በሚል እሳቤ? ...እንጃ! መላ ምቱ ግን ሁለቱም ቢሆን እንኳ ያሳዝናል-ተስፋው መክኗልና፡፡

በእርግጥ ያ ትውልድ የጀመረውን ሳይጨርስ፣ መደማመጥና መቻቻል እንደ ሰማይ ርቆት እርስ በእርሱ ተላለቋል፡፡ ይሄ የሚካድ አይደለም፡፡ እንዲሁም የተሸነፈው የኢህፓ የከተማ አባልና የአሲምባ ታጋይ ‹‹ጓዶች እንመለሳለን›› አይነት መልእክቱን ትቶ፣ ወጥቶ ከቀረ ከ30 አመት በላይ ሆኖታል፡፡ በዚህ በእኛ ዘመን አንድ እንኳ የተመለሰ አላየንም፡፡ ‹‹... We will be back comrades›› ከተሰኘችው የመፅናኛ ግጥም በቀር፡፡

በግልባጩ ደግሞ ከያ ትውልድ ስደትን የወረሱ ኢትዮጵያውያን ብዛታቸው ሺህ ምን ተሺ ደርሷል፡፡ ባለፈው ሳምንትም በይደር ያቆየነው ይህንኑ አጀንዳ ነው፡፡ የደቡብ ሱዳን ኑሮን ስለመረጡና በታህሪር ናፍቆት ስለተቃጠሉ ኢትዮጵያውያን፡፡

...በአስር ክልል የተዋቀረችው እምቦቀቅላዋ ደቡብ ሱዳን የኢትዮጵያውያኖችን አይን በእጀጉ እየሳበች ነው፡፡ ከአራት አመት በፊት በመንግስት በተደረገ ቆጠራ የደቡብ ሱዳን ህዝብ 8.26 ሚሊዮን እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የቆዳ ስፋቷ 644,629 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ይደርሳል፡፡ ከሀገሪቱ ገቢ 98% የሚሆነው ከነዳጅ ዘይት የሚገኝ ነው፡፡ የማዕከላዊ ኢኳቴሪያ ስቴት የሀገሪቱ ዋና ከተማ ‹‹ጁባ›› የምትገኝበት ክልል ነው፡፡ በጁባ ለዛሬው የደቡብ ሱዳን የነፃነት ጥያቄ መልስ የሰጠው የኤስ.ፒ.ኤል.ኤ (SPLA) ድርጅት መስራች እና ሊቀመንበር የነበረው የጆን ጋራንግ መካነ መቃብር በብቸኛው አደባባይ ይገኛል፡፡ ጋራንግ ለነፃነት ትግል ወደ ጫካ ከመግባቱ በፊት በሱዳን ጦር ሠራዊት ውስጥ እስከ ኮሎኔል ማዕረግ ድረስ የደረሰ ሲሆን፣ ‹‹ሉዋ ስቴት›› ከተሰኘው የአሜሪካ ዩኒቨርስቲም ፒ.ኤች.ዲውን ያገኘ ወታደር ነበር፡፡

የሆነ ሆኖ እንደሀገር ከቆመች ገና ሁለት አመት ያልሞላት የደቡብ ሱዳን ዋና ከተማ በኢትዮጵያውያን ስደተኞች አይን የምትሞላ እየሆነች ነው፡፡ ከ6 ሺህ የማያንሱ ኢትዮጵያውያኖች በቅጥሯ ከሀገራቸው ማግኘት ያልቻሉትን ‹‹ዳቦ ፍለጋ›› እንደተሰባሰቡ ይነገራል፡፡ The Citizen, The Juba Post, South Sudan Today, New Times, Daily Monitor የተሰኙ ጋዜጦች በግል አሳታሚዎች የሚንቀሳቀሱባት ጁባ ለኢትዮጵያውያን ስደተኞች ብቻ ሳይሆን ለፕሬስ ነፃነት መከበርም ተስፋ ያላት ትመስላለች፡፡ በቴሌኮም ዘርፍ የተሰማሩ አራት ድርጅቶችም ፈጣን አገልግሎት ሰጪዎች ናቸው፡፡ ሌላው በደቡብ ሱዳን አስገራሚ ነገር የምናገኘው በመካላከያ ሰራዊቷ ውስጥ ነው፡፡ በትግሉ ዘመን ሽምቅ ተዋጊ የነበሩት ታጋዮች ከነፃነት በኋላ የደቡብ ሱዳን ብሄራዊ ሰራዊት ተደርገዋል፡፡ በአለማችንም ከየትኛውም ሀገር የበለጠ የጄኔራል ማዕረግ ያላቸው አዛዦች በዚሁ ሰራዊት ውስጥ ነው የሚገኙት፡፡ አስገራሚውም ነገር ይህ ነው፤ ምክንያቱም ጦርነቱ ካበቃ በኋላ አንጋፋ ታጋዮች በሙሉ ጄነራሎች እንዲሆኑ የተደረገበትን ወታደሪዊ ኮሜዲ እንመለከታለንና፡፡ በዚህም ምክንያት የጄኔራሎቹ ቁጥር ከአምስት መቶ በላይ ሊሆን ቻለና በብዛታቸው ከአለማችን ሀገራት ቀዳሚ ሆኑ፡፡ በእርግጥ የጄነራል ማዕረግን እንደ ‹‹ሬሽን›› በማደል ደቡብ ሱዳን የመጀመሪያዋ ሀገር አይደለችም፡፡ የኢህአዴግ ኢትዮጵያ ትቀድማታለች፡፡

ከዚህ ባሻገር ደቡብ ሱዳን ዛሬም ቢሆን መረጋጋት የተሳናት ሀገር ናት፤ ይህ ግን ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን የሚያስጋ አይደለም፡፡ የእነሡ ስጋት በሀገራቸው ከእነቤተሰቦቻቸው በረሃብ ማለቃቸው ብቻ ነው፡፡

በደቡብ ሱዳን ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚያስችል መልኩ ኢትዮጵያውያኖች የሚገኙት የ250 ሺህ ሰው መኖሪያ በሆነው ጁባ ነው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት የተሰማሩበት የስራ መስክ በአገልግሎት ዘርፍ ወይም በጉልበት ስራ ላይ ነው፡፡ በሆቴል፣ በካፍቴሪያ፣ በፀጉር ቤት እና በሹፍርና ሙያ ላይ ሲሆን፣ ጥቂቱ ደግሞ በሱዳናውያን ‹‹ቦዳ ቦዳ›› እየተባለ በሚጠራው የሞተር ሳይክል የታክሲ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

በሀገሪቱ ከኢትዮጵያውያን በተጨማሪም ኤርትራዊያን፣ ዩጋንዳውያን እና ኬንያውያን በብዛት ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን የእነዚህ አገር ዜጎች በአብዛኛው የተሰማሩበት የስራ መስከ እንደ ኢትዮጵያውያኖች በዝቅተኛ (በጉልበት) ስራ አይደለም፡፡ ጠንካራ ካፒታል በሚጠይቁ የንግድ ስራዎች ጭምርም ነው፡፡ በተለይ ኤርትራውያኖቹ በዚህ በኩል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የደቡብ ሱዳንን የውሃ ፋብሪካ፣ የሀገር አቋራጭ ትራንስፖርት፣ የኮንስትራክሽን እና የመድሀኒት ማምረቻዎችን ተቆጣጥረውታል፡፡ ሌላው ቀርቶ ጁባ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ የሚያስኬደውን መንገድ እየሰራ ያለው ተቋራጭ ድርጅት ንብረትነቱ የኤርትራዊያን ነው፡፡ ስለኤርትራውያኖች ጥንካሬ እና መረዳዳት በጁባ ለተገኘው ተባባሪ ዘጋቢያችን አስተያየቱን የገለፀው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ‹‹ኤርትራውያኖቹ እንደ ግለሰብ ሳይሆን እንደ መንግስት ነው እርስ በእርስ የሚተባበሩት፡፡ አንድ ኤርትራዊ ወደ ጁባ ሲመጣ ባዶ እጁን ቢሆንም ከሶስት ወር በላይ ግን ተቀጥሮ ሲሰራ አይታይም፡፡ ምክንያቱም የሀገሩ ሰዎች መነሻ ካፒታልን ጨምሮ ለንግድ ስራ የሚያስፈልገውን በሙሉ በብድር ያሟሉለታል፡፡ እኛ ጋር ግን ይህ የለም፡፡ በተጨማሪም ከአዲስ አበባ የሚመጡ ስደተኞች ስራ የመናቅና የስንፍና ባህሪ አለባቸው›› ብሏል፡፡

ከዚህ ሌላ በወሲብ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሴት ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ሀገራት ሴቶች በብዛታቸው ይልቃሉ፡፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያኖች ከሀገራቸው ሲነሱ በጉዟቸው ላይ የደላላ ጣልቃ ገብነት ከሌለ ከስድስት ሺህ እስከ ሰባት ሺህ ብር ድረስ ወጪ አድርገው ነው ወደ ሚጓጉሏት ጁባ የሚደርሱት፡፡ ነገር ግን በጉዞአቸው ላይ ደላላ ስለገባበት ብቻ እስከ 56 ሺህ ብር ድርስ አውጥተው የመጡ የደቡብ ኢትዮጵያ ተወላጆች እንዳሉ ለዘጋቢያችን አስተያየት የሰጠው ስደተኛ አረጋግጧል፡፡

የከተማው ሺሻ እና ጫት ቤት በሙሉ የተያዘው በኢትዮጵያውያን እንስቶች ነው፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያውያኖች በየደረሱበት ሀገር መዋረዳቸውን እና መናቃቸውን የሚያሳየን በእንዲህ አይነት ስራዎች ጭምር መሰማራታቸው ነው፡፡ ለነገሩ ሀገራቸውም ቢሆኑ ይህ ውርደትና ንቀት የሚቀርላቸው አይመስለኝም፡፡ ወደ ስደት ሲሄዱም ይኸው ነው የሚያጋጥማቸው፡፡ ከነተረቱስ ‹‹ባለቤቱ የናቀውን አሞሌ...›› አይደል የሚባለው፡፡ ሳይጠቀስ የማይታለፈውን እና ሀገራዊ ክብራችንን ውርድት ላይ የሚጥል አንድ አሳዛኝ ነገር ልጨምርላችሁ፡፡ አዲስ አበባ የሚገኘው የደቡብ ሱዳን ኢምባሲ ወደ ሀገራቸው መግባት የሚፈልገውን ኢትዮጵያዊ ልክ እንደ ሰሜን አሜሪካ እና የአውሮፓ ሀገራት ሁሉ የባንክ ሂሳብ መግለጫ (Bank Statement) የሚጠይቁበት መስፈርት ነው፡፡ ልብ በሉ ነፃነቷን ካገኘች እንኳ ገና ሶስት አመት ያልደፈነች ሀገር ናት ዛሬ ኢትዮጵያዊ ወደሀገሬ ሲጋባ ወጪና ገቢውን የሚያሳይ የባንክ ሰነድ ካላቀረበ አንዴ ሀገሬ ከገባ በኋላ እዚሁ ጠፍቶ ሊቀር ስለሚችል በባንክ በቂ ተቀማጭ ገንዘብ ወይም ንብረት እንዳለው አረጋግጬ ነው ቪዛ የምሰጠው ነው እያለች ያለችው፡፡ መቼም ለአንድ ኩሩ ኢትዮጵያዊ ከዚህ በላይ ውርድት የትም የለ፡፡ እንዲሁም በሱዳናውያን ዘንድ ‹‹ኢትዮጵያውያኖች ችግር የማይችሉ እና ሱሰኞች ተደርገው ይወሰዳሉ›› ተብሎ በራሳቸው በስደተኞቹ የሚነገረው ሌላው አሸማቃቂ ነገር ነው፡፡ እዚህ ጋር የሚነሳው ጥያቄ ‹‹እናስ! መፍትሄው ምንድር ነው?›› የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ምንአልባት በቀላሉ ‹‹የዚህ መፍትሄ ስደት ሳይሆን ለችጋርና ለውርደት የዳረገህን መንግስትህን በታህሪራውያን አይነት ሰላማዊ አብዮት ከስልጣኑ ማባረር›› የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያምም ‹‹ስደትን የኢትዮጵያውያን ባህል ያደረጉት አገዛዞች ናቸው›› ያሉበትንም አውደ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ እናም እህቶቻችን በዚህ መሰል አዋራጅ ህይወት ውስጥ እንዲያዘግሙ ያስገደዳቸውን ስርአት መታገስ እንዴት ትክክል እንደማይሆን ብዙ አይገባኝም፡፡

## የታህሪር ናፍቆት

የቱኒዚያውያንን ዳና ተከትለው የተጓዙ ግብፃውያን ታህሪር በተሰኘው በታላቁ አደባባያቸው ተሰባስበው ሲያበቁ ለ30 ዓመት ያህል ጨፍልቆ በገዛቸው የሙባረክ መንግስት ላይ ጮኹ፤ በጣም ጮኹ፡፡ ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ይከበሩ ዘንድ ጮኹ፡፡ አስከትለውም በይስሙላ ምርጫ መታለል በቃን ሲሉ ከፒራሚዶቻቸው ርዝመት ልቆ በሚሰማ ድምፅ ጮኹ፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ ጩኸት በግብፅ ሰማይ ስር ውሎ ቢያድርም የሙባረክ ቤተ መንግስት ጆሮውን ሊሰጠው አልወደደም፡፡ የታህሪር ጎበዛዝትም በጩኸታቸው ቀጠሉ፡፡ ...እነሆ መጮኹ በጀመሩም በ18ኛው ቀን በዚህ ዘመን የሙባረክ መንግስት በጩኸት የፈረሰ ሁለተኛው አምባገነን መንግስት ሆነና አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ተገለጠ፡፡ የግብፅ ህዝብም በነፃነት ደስታ ተሳከረ፡፡ የታህሪር ናፍቆት ማለትም ይህ ነው-ሌላ አይደለም፡፡

አሁን ጥያቄው ‹‹ኢትዮጵያውያኖችስ ታህሪርን ይናፍቃሉን?›› የሚል ነው፡፡ በግሌ ‹‹በእርግጠኝነት ናፍቀዋል›› ከሚሉት ወገን እሰለፋለሁ፡፡ ለዚህም እውነት ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከኑሮ ውድነት እስከ ሃይማኖት ጣልቃ ገብነት ድረስ ያለው መንግስታዊ ምክንያቶች የብዙዎችን ቀልብ ወደ አብዮት አደባባይ ለመሳቡ በቂ ማረጋገጫ አይሆኑም የሚል ማን አለ? ከሃያ አንድ አመት በላይ የአንድ ፓርቲ እና የአንድ ሰው አምባገነናዊ አገዛዝም እንዲሁ ለታህሪር ናፍቆት ቀልብ ለመስጠት በቂ ነው፡፡

በእርግጥ እዚህ ጋር ሌላም ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ‹‹ታህሪርን የናፈቀው ለውጥ ፈላጊው ብቻ ነውን?›› የሚል፡፡ ‹‹አይደለም!›› ብሎ መከራከርም ይቻላል፡፡ አቶ መለስና ፓርቲያቸውም ታህሪርን ለመናፈቃቸው ጥቆምታዎችን እያየን ነውና፡፡ ለዚህ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሚቀርቡ ትንተናዎች ጆሮ ብንሰጥ ወደ እውነታው ይገፉናል፡፡ በቅርቡ በኢትዮጵያ ተካሂዶ በነበረው የ “World Economic Forum” ስብሰባ ላይ ተገኝቶ የነበረው ጋዜጠኛ ሪቻርድ ዳውደን ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ጋር ቃለ መጠይቅ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ ይህ ጋዜጠኛም ከቃለ መጠይቁ በኋላ በፃፈው ኮመንተሪ ላይ መለስም ታህሪርን ለመናፈቃቸው የተለያዩ ማሳያዎችን ጠቅሶ አቅርቧል፡፡ “The Arab spring was watched closely by Ethiopians and it appears Meles senses it is coming” (ኢትዮጵያውያኖች የአረብ አብዮትን በንቃት ተመልክተውታል እናም ይህ አይነቱ ነገር እንደሚፈጠር መለስም ገብቶአቸዋል) ሲል ለሰአታት ሁለቱ ብቻ የቀዩበትን አጋጣሚ ተጠቅሞ የደረሰበትን መላምታ አስቀምጧል፡፡

ምናአልባት ብዙዎቻችን ‹‹መለስ ስለምን የህዝቡን ማመፅ ይናፍቃሉ?›› ብለን የዳወደንን መላምት ላንቀበል እንችል ይሆናል፡፡ ሆኖም መላምቱ ስጋና ደም ሊለብስ የሚችልበት እድል ሰፊ ለመሆኑ ምክንያት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በቀላሉም ከዚህ ቀደም ዊክሊክስ የተባለው ድህረ ገፅ የአሜሪካንን ገበና በገለጠበት ጊዜ ‹‹በአዲስ አበባ ከተማ በተለያየ ቦታ ፈንጅ የሚፈነዳው በራሱ በመንግስት ነው›› ሲሉ የአሜሪካው አምባሳደር ወደ ሀገራቸው ማስተላለፋቸውን አስነብቦናል፡፡ ይህንን ሴራ ታህሪርን ከመናፈቅም በላይ አድርገን ‹‹መንግስታዊ ሽብርተኝነት›› ልንለው እንችላለን፡፡ ከዚህ ሌላም ዛሬም ድረስ የቀድሞ ቅንጅት መሪዎች በድህረ ምርጫ የተከሰተውን የሰኔ አንድንም ሆነ የጥቅምት 22ቱን ‹‹የጎዳና ላይ ነውጥ›› ሆን ብሎ የፈጠረው ኢህአዴግ ነው ሲሉ የሚከራከሩበትን አንኳ ስንመዘው ‹‹ኢህአዴግ በህዝቡ ላይ የተፈጠረውን መነቃቃት ለመደምሰስና የቅንጅት መሪዎችን እስር ቤት አስገብቶ፣ ተቃዋሚዎችን በመረጠውና ከጎናቸው በቆመው ህዝብ ላይ ፍርሃትን ለማንገስ በራሱ ሰዎች የፈጠረው አመፅ ነው›› የሚል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ከተስማማን የአረብ ሀገራት አብዮትን ተከትሎ በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ምልክት እየታየ መሆኑ ላይ መስማማታችን አይቀሬ ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱን መላምቶች ካሰናሰልን ደግሞ መለስ እንደ ድህረ ምርጫ 97 አይነት እርምጃ ለመውሰድ ከህዝቡ ቀድመው ቢዘጋጁ የሚደንቅ አይሆንም ማለት ነው፡፡

በአናቱም የስነ ልቦና ባለሙያዎች ‹‹ብዙውን ጊዜ አምባገነኖች አደጋ ይከሰታል ብለው ከጠረጠሩ አደጋው እነርሱ ባላሰቡበት እና ለቁጥጥር አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ከሚከሰት በፈለጉትና በቀላሉ ሊቆጣጠሩት በሚችሉት ወቅት ሆን ብለው እንዲከሰት ያደርጋሉ›› የሚለው ትንተናቸውን ስንደምረው ምንአልባት መለስ ሳያስቡት ህዝባቸው አብዮት አደባባይን ከሚያጥለቀልቅ ባሰቡት እና አመቺ ነው ባሉት ጊዜ፣ በቀላሉ ሊቀለበስ የሚችል አብዮት እንዲነሳ አድርገው የሀይል እርምጃ በመውሰድ ለተወሰኑ አመታት ዝም-ጭጭ ማድረግ ይፈልጋሉ የሚል ሆኖ ብናገኘው አሁንም በጨለማ ውስጥ ጥቁሯን ድመት የመፈለግ አይነት ድካም አድርገን መውሰድ የለብንም፡፡ ጆን ክላውድ የተባለ ፀሀፊ ‹‹The Psychology of dictatorship: Why Gaddafi Clings to Power›› በሚል ርዕስ ባሰፈረው ፁሁፍ ‹‹Dictators may fight to the end because they don’t understanding that any end is possible›› (አምባገነኖች እስከ መጨረሻው ድረስ የሚዋጉት መጨረሻ የሚባል ነገርን ስለማይረዱት ነው) ማለቱን ጠቅሶም መከራከር ይቻላል፡፡ መቼም ራሳቸው አቶ መለስ ዳውደን ስለጋዳፊ አወዳደቅ በጠየቃቸው ጊዜ “He was a malign influence on the area. His departure was less benign than we had hoped.” (ሰውየው በአካባቢው ላይ የፈጠረው ተፅእኖ ክፉ ቢሆንም ውድቀቱ ያሰብነውን ያህል በጎ አይደለም) ሲሉ በአብዮት የሚመጣ መልካም ለውጥ አለመኖሩን በገደምዳሜ ለማስተላለፍ የፈለጉበት አንጓም ሲፈረካከስ በአረብ አብዮት ስጋት ከሰላማዊ እንቅልፍ መፋታታቸውን ይጠቁማል፡፡

በእርግጥ በሀገራችን ያለው ስርአት ዘውግ ተኮር በመሆኑ የሚነሳው አብዮት ከግብፃውያን የታህሪር ጀግኖች በተለየ መልኩ የሚታይ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ግብፆች ወደ ታህሪር ሲያቀኑ የሃይማኖትም ሆነ የብሔር ልዩነት አልፈጠሩም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሁልጊዜም ራሳቸውን ‹‹የዴሞክራሲ ጠበቃ›› አድርገው የሚቆጥሩት ምዕራባውያኖች ጣልቃ ገብተው ይረዱናል የሚል ተስፋም ሰንቀው አይደለም፡፡ ይህ እንደማይሆን አስቀድመው አውቀዋልና፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ግን የዚህን ግልባጭ ነው የምናገኘው፡፡ ዛሬም አሜሪካንን ተስፋ ያደረጉ ፖለቲከኞቻችን ብዙ ናቸው፡፡ አስማማው ኃይሉ የተባሉ የቀድሞ የኢህአፓ ታጋይ ‹‹ከደንቢያ-ጎንደር እስከ ዋሽንግተን ዲሲ›› በሚል ርዕስ ታሪካዊ ልቦለድ ብለው በፃፉት መጽሐፍ ላይ ምዕራባውያንን መተማመን ጉም የመዝገን ያህል መሆኑን ለመግለፅ እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል፡-

‹‹በአፍሪካ ቀንድ ኃያል ነው ሲባል የኖረውን የደርግን መንግስት የደመሰሱ የሻዕቢያና የሕወሓት ድርጅቶች ተቀምጠው፣ ግንባር

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

# ፍሬንድ ዘመኑ የኤፍ ኤም ነው!



በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)

## (ካለፈው የቀጠለ)

ባለፈው ሳምንት በዚህ ርዕስ አንድ መጣጥፍ ፅፌያለሁ፡፡ በዚያ ጽሁፌ አሁን ያሉት የኤፍ.ኤም የራዲዮ ጣቢያዎች ስለሚያስተላልፏቸው ያልተገቡ ፕሮግራሞች አንስቼ፣ ለእንደዚያ ያሉ መጥፎ ፕሮግራሞች የእኛንና የልጆቻችንን ጊዜ የሸለማቸው ማነው? የሚል ጥያቄ አንስቼ ነበር፡፡ መልሴም “ጊዜያችንን ቀምተው ለነዚህ የኤፍ ኤም ፕሮግራሞች የሸለሙብን አንደኛ መንግሥት፣ ሁለተኛ የኤፍ.ኤም ባለቤቶች“ ሶስተኛ ደግሞ የሙያው ብቃት የሌላቸው “ጋዜጠኞች” ናቸው የሚል ነበር፡፡ መንግሥትና የኤፍ. ኤም ባለቤቶች ከችግሩ ጋር እንዴት እንደሚቆራኙ ባለፈው አብራርቻለሁ:: የዚህ ሳምንት ቀጠሮዬ ስለ “ጋዜጠኞች” ድርሻ ለማብራራት ነው፡፡

የጋዜጠኝነት ሙያ ትልቅ ሙያ ነው፡፡ ትልቅ ሙያ ደግሞ ትልቅ ሰብእናን ይጠይቃል፡፡ የሰብእና ትልቅነት የተፈጥሮ ባህርይና የእውቀት ቅንጅት ነው፤ ሁለቱ ካልተደጋገፉ ትልቅ ሰብእና አይገኝም፡፡ በትምህርትም ሆነ በህይወት ልምድ ያካበተውን እውቀት ለሰዎች ጠቃሚ በሆነ መንገድ ለመተርጐም የማይችል ሰብእና የጋዜጠኝነትን ሙያ ሊሸከም አይችልም፡፡ ጋዜጠኛ ሙያውን ደፍሮ ሳይሆን አውቆ የተቀላቀለ፤ እውቀቱም ለሰዎች ሁለንተናዊ ነፃነት እስከበጀ ድረስ ከመጠቀም የማይቦዝን መሆን አለበት፡፡ ዋናው ደግሞ የሙያውን ስነ ምግባር ለመሸከም ቀልቡ የፈቀደ ብቻ ሳይሆን፣ ልቦናው የፀና መሆን ያሻዋል፡፡ እውቀቱ ወይ የልብ ጽናቱ ሲጐድል ለዚህ ጽሁፍ መነሻ እንደሆኑኝ አይነት የኤፍ.ኤም ፕሮግራሞችን እንሰማለን፤ የሚያዳምጣቸውም ይኖራል፡፡

መቼም ስለመጥፎ የኤፍም.ኤም ፕሮግራሞች ሲነሳ “ታዲያስ አዲስን” የሚስተካከል የለም፡፡ “ታዲያስ አዲስ” በ‹‹ሸገር ኤፍ.ኤም››የሚተላለፍ መጥፎ ፕሮግራም ነው በእኔ ዕይታ፡፡ ይህ የኤፍ.ኤም. ጣቢያ እንደ “ሸገር ካፌ” እና “የሳምንቱ እንግዳ” አይነት ጥሩ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፡፡ “ታዲያስ አዲስንም” ያስተላልፋል፡፡ ማዘጋጀትና ማስተላለፍ ለየቅል ናቸው፡፡ “ታዲያስ አዲስ” ይተላለፋል እንጂ አይዘጋጅም፡፡

“ታዲያስ አዲስ” ስለቋንቋ አጠቃቀም አይጨነቅም፡፡ ኢትዮጵያዊው ባህልና ወግ ቁብ አይሰጠውም፡፡ የጋዜጠኝነት ስነምግባር ሲያልፍ አይነካውም፡፡

ምሳሌ አንድ

ከአመት በፊት ነው፡፡ ያልተዘጋጀው “ታዲያስ አዲስ” ይተላለፋል፡፡ “ጋዜጠኛው” በየማስታወቂያው መሀል “ልደት በነፃ” እያለ ይጮሃል፡፡ አነጋገሩን ላዳመጠ “እንኳን ደስ አላችሁ” ለማለት ሳይሆን፣ የልደት ኬክ እና ስጦታ ያዘጋጀ ነው የሚመስለው፡፡ አንዲት ልጅ ደወለች፡፡ “ሀሎ” አለችው፤ ድምጽዋ ደስ ይላል፡፡ “ማን ልበል” አላት፤ ድምጹ ከመጠን ያለፍ ፈንጠዝያ ይደመጥበታል:: በወጉ “ሀሎ” ሳይላት የማንነት ጥያቄ ያቀረበላት ልጅ በተቆራረጠ ድምጽ “ቤዛ እባላለሁ፤ አስራ አራት አመቴ ነው” አለችው፡፡

“ዛሬ ልደትሽ ነው” ጠየቃት፤ የጋዜጠኛ ሳይሆን የፖሊስ ቃና ባለው ቅላፄ፡፡

“አዎ” መለሰችለት፡፡

“ኦኬ ቤዛ የአስራ አራተኛ ዓመት ልደትሽን እያከበርሽ ነዋ ...[ሳቀ] ለመሆኑ ወደፊት ምን መሆን ትፈልጊያለሽ?” አሁንም ጠየቃት፡፡

“አስትሮኖት” በፍጥነት መለሰችለት፡፡ ቤዛ ሳታቅማማ ነው የመለሰችው፡፡ የአመላለስዋ ፍጥነት የቤዛ አስትሮኖት የመሆን ህልም አብሯት የከረመ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ለቤዛ “አስትሮኖት” መሆን እፈልጋለሁ ምላሽ የታዲስ አዲስ “ጋዜጠኛ” ምን ብሎ እንደመለሰላት ማንም ሊገምት አይችልም፡፡ በተለይ ከአንድ ጋዜጠኛ የሚጠበቀውን ከግምት ካስገባን የ“ጋዜጠኛውን”” መልስ ከማግኘት ቶምቦላ ሎተሪ ገዝቶ ማሸነፍ ይቀላል፡፡

“አልቀረብሽም” ነበር የ“ጋዜጠኛው” መልስ፡፡

የአስራ አራተኛ ዓመት ልደትዋን እያከበረች ያለችው ቤዛ፣ ያመነችው “ጋዜጠኛ” አሾፈባት፤ ተሳለቀባት፡፡ “ልደት በነፃ” ሲል አምናው ደወለችለት፡፡ ህልምዋን ነገረችው፡፡ የእንቡጥዋ እንቡጥ ህልም ላይ አላገጠበት፡፡ አዘንኩ፡፡ ቀና ብዬ የአስራ ሁለትና የዘጠኛ ዓመት ልጆቼን ተመለከትኩ፡፡ አልሰሙትም፡፡

“የቤዛ ቤተሰቦች ሰምተው ይሆን” እራሴን ጠየቅኩ፡፡ “ጋዜጠኛው” በዚህ አላበቃም፡፡

“ማታ ማታ እየወጣሽ ጨረቃና ኮከብ ታያለሽ” አላገጠ፡፡

“አዎ አያለሁ፡፡” ቤዛ በቅንነት መለሰችለት፡፡ አይ ልጅነት፡፡ ልጅነት እኮ ቅንነት ነው፡፡

“ደመና ሲሆንስ!” “ጋዜጠኛው” ተንከትክቶ ሳቀ፡፡ የሳቁ ምንጭ የቤዛ ትልቅ ህልም ይሁን የእሱ እውቀት ማጠር አልገባኝም፡፡ ለዚህ ጥያቄ ግን ቤዛ መልስ አልነበራትም፡፡ ዝም አለች፡፡ ከዚህ ጊዜ በሁዋላ ቤዛ ደግማስ ለሬዲዮ ፕሮግራም ስልክ ትደውል አትደውል አላውቅም፡፡ “ጋዜጠኛው” ግን ዛሬም ከአመት በሁዋላ አለ፡፡ በሳምንት አምስት ቀን በአድማጮቹ ላይ እያሾፉ እያላገጠ አለ፡፡ ያለ መታደል ሆኖ ለእኛም “ሀይ” የሚልልን አካል፣ ለእሱም “ሀይ የሚል ህሊና ሳንታደል ቀረን፡፡

ጋዜጠኝነት እኮ በጋዜጣ መፃፍ፣ በራዲዮና በቴሌቭዥን መናገር ብቻ አይደለም፡፡ ጋዜጠኝነት ተዘርዝሮ የማያልቅ ሀላፊነት ነው፡፡ “ጋዜጠኛው” ለቤዛ ሲናገር በሚሊየን ለሚቆጠር ህዝብ ነው የተናገረው፡፡ የምዕራቢውያንን ፕሮግራሞች ፈጥኖ የሚቀዳ “ጋዜጠኛ” እንደምን የሙያውን እውቀትና ስነ ምግባር አብሮ አይጨልፍም? ወይም ቁምነገርን አጥሎ የሚያስቀር መከረጃ አለ? አይገባኝም፡፡

ኤፍ.ኤም የምእራባውያኑን ቀልድና መዝናኛ እንዳለ ኮርጆ “እንቀልድ፤ እንዝናና” እያለ ያስቃየናል፡፡ ገመናችንን በአደባባይ ይበትንብናል፡፡ እንዴት ነው አንድ ባለምግብ ቤት ከማታውቀው ሰው ስልክ ተደውሎላት “ውሻ አርደሽ ምግብ ከሰራሽ ብዙ ገንዘብ ይከፈልሻል” ተብላ ስትፈተን ቀልድ ብለን የምንስቀው? ባለምግብ ቤትዋ በቀረበላት አማላይ ገንዘብ ተሸንፋ “እሺ ይሁን የውሻ ምግብ እሰራለሁ” ብትልስ? በርግጥ ለ“ጋዜጠኛው” ምንም አይደለም፡፡ ግን እዚያ ቤት ከዚህ በሁዋላ ገብቶ የሚመገብ አለ? ያንን ያልሰማ ካልሆነ በቀር፤ አይመስለኝም፡፡

ምእራባውያኑ የራሳቸው ባህል አላቸው፡፡ የሚያስቃቸው፣ የሚያዝናናቸው “ቀልድ” ብለው የሚቀበሉት ጉዳይ አለ፡፡ ባህላቸው የማይቀበለው ጉዳይም አለ፡፡ ልዩነቱ “እነሱ ባህላችን፣ አኗኗራችን ተናጋ” ሲሉ “እኮ ማን” የሚል አካል አላቸው፡፡ ከላይ በቤዛ እና ባለምግብ ቤትዋ የደረሰው አይነት በደል በአውሮፓ ወይም በአሜሪካ ቢደርስ፣ ጋዜጠኛው ሙያውን እስከ ዘለአለሙ ያጣል፤ ሬዲዮ ጣቢያውም ሊዘጋ ይችላል፡፡ እኛ ግን ባህላችን ሲናጋ፣ አኗኗራችን ሲሾፍበት “ሀይ” የሚልልን እስካሁን አልተገኘም፡፡

ምሳሌ ሁለት

አንድ ቀን ምሽት ላይ፣ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት በሁዋላ ነው፤ ትክክለኛው ሰአት ትዝ አይለኝም እኔና ቤተሰቤ (ባለቤቴና ሁለት ሴት ልጆቼ) ዘመድ ቤት አምሽተን ስንመለስ መኪና ውስጥ ራዲዮ ከፈትኩ፡፡ የፈረደበት ኤፍ.ኤም፤ ነበር መስመሬ፡፡ አንዲት ሴት “ጋዜጠኛ” ስለአንድ የወሲብ ንግድ ቤት ከአንድ ሰው ጋር ቃለ ምልልስ ታደርጋለች፡፡ ፕሮግራሙን ከመጀመሪያው ስላላዳመጥኩት የደረስኩበትን እነሆ፡፡

“እዚህ ቤት ማታ የሚመጡት ሴተኛ አዳሪዎች ናቸው፤ ማለቴ ሴቶቹ?” ጠየቀች “ጋዜጠኛዋ”

“ኖኖ! አንድም ሴተኛ አዳሪ የለም፡፡ ሰራተኞች ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ጥሩ ስራ አላቸው፡፡ ብትፈልጊ የኤን.ጂ.ኦ ሰራተኞችም አሉ፤”

“ቀንስ የሚመጡ ሴቶች?”

“ቀን የሚመጡት ተማሪዎች ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ የሚመጡት ሴቶች ብቻ አይደሉም፤ ወንዶችም ይመጣሉ፡፡”

“ማለት ወንድ ለመፈለግ የሚመጡ ሴቶች አሉ?” በመደነቅ ጠየቀች “ጋዜጠኛዋ”፡፡

“በሚገባ ይመጣሉ፤ እዚያ ለወንዶቹ ከፍለው ይጠቀማሉ፡፡” መለሰላት እኔና ባለቤቴ ደንግጠናል፡፡ ልጆቻችን የግል ጨዋታ ይዘዋል፡፡ ኤፍ.ኤም ቀጠለ፡፡ “ጋዜጠኛዋ” በርከት ያሉ ጥያቄዎችን አከታትላ ጠየቀች፡፡ ተጠያቂው መለሰላት፡፡

ቤቱ በሁለት የተከፈለ መሆኑንና አንደኛው “VIP” እንደሚባል፤ እዚያ ያሉትም ሴቶች ደንበኞቻቸው በጠየቁዋቸው አይነት ሁሉ ወሲብ እንደሚፈጽሙና ከታችኛው ‹ተራው› ቤት ጋ ሲነፃፀሩ ቆንጆዎች እንደሆኑ፤ የተራው ቤት ሴቶች ወሲብን የሚፈጽሙት እንደ “VIP”ው ደንበኞቻቸው በጠየቀው መንገድ ሁሉ ያለመሆኑን፣ ከሁሉም የሚገርመውና የሚሰቀጥጠው ግን በአንዱ ክፍል ውስጥ አስር ጥንዶች ያለምንም መጋረጃ ወሲብ እንደሚፈጽሙ የተናገረው ነው፡፡

“ጋዜጠኛዋ” የባለ ወሲብ ቤቱ ዋናው ገቢ ምን እንደሆነ ጠየቀች፡፡ ዋናው ገቢ በቤቱ ውስጥ ከሚሸጠው እጅግ ውድ የአልኮል መጠጥና የሀሺሽ ሺያጭ መሆኑን ገለፀላት፡፡ የቤቱ ደንበኞች ሀሺሽ እንደሚጠቀሙ በይፋ ነገራት፡፡

በቤቱ ውስጥ ወሲብ የሚሸጡና የሚገዙት ሰዎች መከላከያ /ጥንቃቄ/ ያደረጉ እንደሆነ ስትጠይቀው ገረመው “እዚህ የሚመጡት ሰዎች እኮ ጥንቃቄ ምናምን ለሚለው ደንታ የላቸውም፡፡ የሚገርምሽ አብዛኞቹ የቤቱን ዝና እየሰሙ አንዴ ለማየት ይመጣሉ፡፡ ከዚያ ግን በቃ ደንበኛ ሆነው ነው የሚቀሩት አላት”

በመጨረሻም “ጋዜጠኛዋ” በእንደዚህ አይነት ቦታ ሰዎች ሲዝናኑ ራሳቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው አስገንዝባ ፕሮግራምዋን ዘጋች፡፡ ጉዳዩን ከሀገርና ከባህል፣ ከልጆቻችን ስነምግባርና ተስፋ ጋር አላያያዘችውም፡፡ አንድ የስፖርት ጋዜጠኛ “የዛሬው ተሸናፊ ወደፊት ለማሸነፍ በርትቶ መለማመድ አለበት” ብሎ እንደሚዘጋው የእግር ኳስ ወሬ “ስንዝናና ጥንቃቄ እናድርግ” የሚል መቋዋጫ ጣል አድርጋ ሄደች፡፡ ያሳዝናል፡፡

ለመሆኑ የዚህ ፕሮግራም አላማ ምንድን ነው? የወሲብ ቤቱን ማስተዋወቅ ካልሆነ በቀር ፋይዳው ምንድን ነው? በእርግጥ ጥሩ ማስታወቂያ ነው፡፡ እኔና ባለቤቴን ጨምሮ እጅግ በርካታ ዜጎች መሀል አዲስ አበባ ላይ እንዲህ አይነት ወሲብ በጅምላ የሚሸጥበት ቤት መኖሩን አወቅን፤ መጥኔ ለኤፍ. ኤም፡፡ እኛስ በእድሜና በኑሮ ስለ ሰከንን ሰቀጠጠን፣ እንቅልፍ አልባ ለሊት አሳለፍን፡፡ በአፍላ እድሜ ላይ ያሉ፤ አዲስ ነገርን የመሞከር ተፈጥሮአዊ ፍላጎት በታወጀበት እድሜ ውስጥ ያሉትስ? እውን ለማየት አይጓጉም? እነዚህን “ጋዜጠኞች” አስቤ ነው ባለፈው “ልጆቻችንን በየት በኩል እናሳድግ፤ ኤፍ.ኤም ዱርዬ ሆነብን” ማለቴ፡፡

ከላይ የጠቀስኩዋቸውን አይነት የኤፍ. ኤም ፕሮግራሞችን መጥቀስ አይገድም፡፡ እነዚህን ፕሮግራሞች የሚያዘጋጁ “ጋዜጠኞች” ሙያው የሚጠይቀው እውቀት አላቸው፤ ሀላፊነትም ይሰማቸዋል ማለት አይቻልም፡፡ ደፋሮች ግን ናቸው፤ የትውልዱን ድፍረት ጠቅለው የወሰዱ ይመስል የማይደፍሩት የእውቀት መስክ፣ የህብረተሰብ ክፍል የለም፡፡ ሀገራችንን ነገ ስለሚረከቡ ልጆቻችን የሚቆጨው የኤፍ.ኤም ጣቢያ ባለቤት ካለ፣ የዜጎችን ሁለንተናዊ ጤንነት የሚያሳስበው መንግስት ካለ “ሀይ” ሊልልን ይገባል፡፡

# ሚስማሩን የሳተው የበድሉ ዋቅጅራ መዶሻ

ቀናው ገ/ስላሴ

ተመስገን ፍትህ ጋዜጣን ለሙግት የፈጠራት ሳትሆን አትቀርም፡፡ ይሄው ‘እንደየሩሳሌም’ አርብ አርብ ትሸበራልች - በሙግት፡፡ በየሳምንቱ ካለፈው ህትመት በመነሳት አንዱ የአንዱን ሀሳብ ሲሞግት፤ እያነሳ ሲጥል ላቅ ሲልም ሲወርፍ ማንበብ የተለመደ ሆኗል፡፡ ለነገሩ ፍትህ እራሷ ያለ ሙግት መች ትመጣና፡፡ ይሄው እኔም ማነህ ባለሳምንት ብየ መጥቻለሁ፡፡

ይህችው የሙግት እና የመረጃ ጋዜጣ በቅርቡ አዳዲስ አምደኞችን ይዛ ብቅ ማለት ጀምራልች፡፡ እሰየው የሚያስኝ ነው፡፡ ከአዳዲሶቹ ውስጥ ታዲያ በግጥም ፀሐፊነታቸው የምናውቃቸው በቁጥር ላቅ ይላሉ፡፡ ሰፋ ሰፋ ያሉ ገፆችን ይዘው ተደላድለዋል፡፡ ምን አልባት ብዙ ሰው ግጥም ስለማያነብ በጋዜጣ በኩል ሊደርሱት አስበው ይሆናል (ይቆየን)፡፡ አንዳንዶቹ ከገጣሚነት ወደ ጋዜጣ አርቲክል ፀሐፊነት ያደረጉት ሽግግር ያደናቀፋቸው ይመስላል፡፡ እዚህም እዚያም የሚረግጥ ያልሰከነ እና ለአቅመ-ንባብ ያልደረሰ ፁሑፍ ያስነብቡን ጀምረዋል፡፡ እናም ለሚመለከታቸው ሁሉ ግጥማቸው ላይ ቢበረቱ እንዴት መልካም ነው እላለሁ፡፡ ወደ ዋናው ጉዳዬ ልግባ፡፡

ባለፈው የግንቦት 24 የፍትህ ጋዜጣ እትም ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ “የሰው አዋዋሉ የቃል አገባቡ ነው ስድ የሚያሰኘው” በሚል ርዕስ በግንቦት 17 ፍትህ እትም መልካምሰው አባተ የተባሉ ፀሐፊ በዕውቀቱ ስዩም በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ያነሳውን ክርክር በመሞገት የፃፉትን እያጣጣሉ ‹‹በስድአደግ ቃላት የታጨቁ፣ መሆናቸውን ይህም ከዕውቀት ማነስ ፤ ብዙ ካለማንበብ፤ ያነበቡትንም በደንብ ካለመረዳት እና ሀሳብን በአግባቡ ካለማደራጀት የመጣ በሽታ ነው›› ሲሉ ወቅሰዋል፡፡ ወቀሳዬ ካለምንም ማስረጃ እና ዋቤ የመጣ አይደለም ሲሉም በመስኩ ሊቃውንት ካሏቸው የወሰዷትን ቀጭን ጥቅስ ከአንድ እድሜ ጠገብ መፅሐፍ ጎተት አድርገው ጠቅሰዋል፡፡ እናንተም አንብቡ ሲሉም መክረዋል፡፡

መቸም የመልካምሰውን ፁሑፍ በቅንነት ያነበበ እንደ በድሉ ዋቅጅራ እያጋነነ ‹‹በስድአደግ ቃላት የታጨቀ ነው›› እያለ አይገልፀውም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ለእኔ ከመልካምሰው ይልቅ ዶ/ር በድሉ የፃፉበት ቋንቋ በዚህ መልኩ ቢገለፅ የሚበዛበት አይመስለኝም፡፡ በወፍ በረር (scanning) እንኳ ቃላትን መርጠን እናውጣ ብንል በድሉ መልካምሰውን የወረፉበት ‹‹ስድአደግ ቃላት›› በቁጥር ቢያይሉ እንጅ አያንሱም፡፡ ሌላው የመልካምሰው ፁሑፍ ዋነኞቹ በጉዳዩ ላይ ሲፋለሙ የቆዩት በዕውቀቱ ስዩም እና አለማየሁ ገላጋይ ከተወራረፉበት በላይ ተጋኖ ‹‹በስድአደግነት›› መወቀሱ በራሱ አስገርሞኛል፡፡

የበድሉ ሙግት ግልፅ አይደለም፡፡ ፀሐፊውን የሚወቅሱበት መንገድም ወጥነት ይጎድለዋል፡፡ በእርግጥ ፁሑፋቸው 1ኛ በቃላት አጠቃቀም 2ኛ በሃሳብ አደረጃጀት እና ማስረጃ አቀራረብ በሚሉ በሁለት አበይት ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር ገልፀውልናል በቀጥታም ባይሆን፡፡

ይሁን ብለን እነዚህን ተከትለን እንሂድ፡፡ የቃላት አጠቃቀም የሚለውን ጫፍ ይዘን “የሰው አዋዋሉ የቃል አገባቡ ነው ስድ የሚያሰኘው” የሚለውንም ርዕስ አይተን ስለ ፀሐፊው (መልካምሰው) ተገቢ ያልሆነ የቃላት አመራረጥ እና አገባብ ሊነግሩን ነው ስንል ሽተት ብለው ፀሐፊው በዕውቀቱን የሞገተበትን ፍሬሀሳብ ትክክል አይደለም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ ፀሐፊው ሀሳባቸውን ባግባቡ ያለማደራጀት እና ማስረጃ ያለማቅረብ ችግር እንዳለባቸው በመጠቃቀስ ሊሞግቱ ይሞክሩና አሁንም ሽተት ብለው መልካምሰው የበዕውቀቱን ሀሳብ ስላለማክበራቸው በጋራ እናውግዝ የሚል ድምፀት ያለው ሀሳብ ይዘው ከተፍ ይላሉ፡፡ ወረድ ብለው ደግሞ ስለ አካዳሚያዊ የምርምር ፁሑፍ አፃፃፍ ለማስተማር ይዳዳቸዋል፡፡ አረ እንዲያውም የተሰጣቸውን ሰፊ ገፅ ግማሽ አካል ያለበሱት በዚሁ የምርምር ፁሑፍ አፃፃፍ ዙሪያ ለማስተማር በመሞከር ነው፡፡ ለጋዜጣ የተፃፈ ባይሆን ኖሮ እንታገሰው ነበር፡፡ እስኪ አንዳዶቹን በማንሳት የግሌን አስተያየት ለመስጠት ልሞክር፡፡

ዶ/ር በድሉ ‹‹ስድአደግ›› ሲሉ ፈረጀው እየለቀሙ ያወጧቸውን የመልካምሰውን አገላለፆች ‹‹ስድአደግ›› ስለመሆናቸው ለማስረዳት የሞከሩበት መንገድ በግሌ መሰረታዊ ስህተት ያለባቸው ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡

መልካምሰው “የበዕውቀቱ ስዩም የታሪክ ቤተ-ሙከራ ቫይረስ” ብለው በርዕስነት የተጠቀሙትን አገላለፅ በመጥቀስ በዕውቀቱ ከሚለው ስም በስተቀር የተቀሩት ቃላት ያለቦታቸው የገቡ ናቸው-‹‹ስድአደጎች›› ይሉናል በድሉ፡፡ ከዚያም ‹‹ቫይረስ›› የሚለው ቃል አገባብ ትክክለኛ እና ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ መሰረት ያደረገ ነው የምንለው ለምሳሌ እኔ “ሰውየው የኤችአይቪ ቫይረስ ተገኘበት” ብየ ብፅፍ ነበር ሲሉም ምሳሌ ያስከትላሉ ልክ ‹ቫይረስ› የሚለው ቃል በሌላ አውድ (context) ገላጭ ሆኖ መግባት እንደሌለበት ሁሉ፡፡

ሙግቱ ‹ቫይረስ› የሚለው ቃል ያለ ትክክለኛ ተዛምዶው በመግባቱ (ከስድአደግ የወጣ) ‹‹ስድአደግ ቃል ሆኗል›› ከሆነ በድሉ እራሳቸው ‹‹ስድአደግ›› የሚለውን ቃል ያለቦታው እና ያለተዛምዶው ነው የደነጎሩት ብሎ መከራከር ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ‘ስድአደግ ሰው’ ሲባል እንጅ ‘ስድአደግ ቃል’ ሲባል ሰምተን ስለማናውቅ፡፡ በአማርኛ የቋንቋ አጠቃቀም ወይንም የቃላት ተዛምዶ ውስጥም ይህንን አላየንም፡፡ ምንአልባት በገጣሚነቴ ቃላትን የመፍጠር እና እንዳሻኝ የመጠቀም መብት (poetic license) አለኝ ካላሉ በስተቀር፡፡ ክፋቱ ግጥም አይደለም የፃፉልን፡፡

ከላይ እሳቸው ‹ቫይረስ› በሚለው ቃል ዓረፍተነገር ባዋቀሩበት መንገድ “ሰውየው ስድአደግ በመሆኑ ፀያፍ ቃላትን ይጠቀማል” ብየ ብፅፍ ስድአደግ የሚለው ቃል አገባብ ትክክለኛ እና የተፈለገውን ሐሳብ መሰረት ያደረገ ነው ብየ ልከራከር ነው ማለት ነው፡፡ ወደ ተመሳሳይ ስህተት ላመራ፡፡

ይህንን መሳ ምሳሌ የማቀርበው የበድሉ መከራከሪያ ከምር ቃላት አመራረጥ እና አገባብን መሰረት ያደረገ መስሎኝ ነበር፡፡ ግን ወረድ ብለው ከተነሱበት ዋነኛ ሀሳብ ይወጡና ፍሬ ሀሳቡ ላይ በመለጠፍ “በዕውቀቱ በፁሑፉ የታሪክ ቤተሙከራ አላቆመም…” ሲሉ ለቃላት ተገቢ አጠቃቀም ዘብ ከመቆም ወጥተው ለበዕውቀቱ ሀሳብ ዘብ ይቆማሉ፡፡ በተደጋጋሚም ወጥነት የሌለው ትንተና እየሰጡ ደግመው ደጋግመው ስህተት ውስጥ ሲወድቁ የምናገኝበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ በቃላት አመራረጥ እና አጠቃቀማቸው ጭምር፡፡

ለፁሑፋቸው መግቢያ የተጠቀሙበት የፀሐፊውን፤-

“በዕውቀቱ የአለማየሁን ሀሳብ ለመሞገት ተፈጥሯዊ አቋሙን ትቶ አንድ እግሩን አላልቶ አንድ እግሩን አጠንክሮ በአንድ ጎኑ በመቆም ጋሻውን ወድሯል የአለማየሁን ጎራዴ ለመመከት”

የሚለውን በውብ አገላለፅ የተከሸነ ሙግት “የቃላት አመራረጡ እና አሰዳደሩ ለአንባቢ እውቀትን ሳይሆን አንባጓሮን ነው የሚነግሩት” ይሉናል፡፡ መቸም አንድ ድንቅ ገጣሚ እና የቋንቋ መምህር የቃላት ጦርነትን ፤ በቃላት የመከላከል እና የማጥቃት ፍልሚያን እንዲህ እንደ መልካምሰው አድርጎ መግለፅ ምን ያህል አንባቢን እንደሚስብ ይዘነጋዋል ብየ አላስብም፡፡ ሌላው ዘለፋ ሊያስብል የማይችልን አገላለፅ ዘለፋ እያሉ ያላግባብ ቃል ያባክናሉ፡፡ “በዕውቀቱ የታሪክ እውቀቱ እንደስሙ ስላልሆነለት…” የሚለውን የመልካም ሰውን አገላለፅ በዕውቀቱን መዘለፍ ነው ይሉን እና እራሳቸው በተመሳሳይ አንቀፅ “መልካምሰው እንደስሙ መልካም ቃላትን አልተጠቀመም፡፡” ይሉናል፡፡

ከሁሉ የሚገርመው እኔም ጠንከር አድርጌ ልሞግተው የምፈልገው በድሉ እራሳቸውን እንደ ዓርአያ በማስቀመጥ አካዳሚያዊ አፃፃፍን እንድንከተል የመከሩበት በዩንቨርሲቲ ቆይታችን የምርምር ፁሑፍ አፃፃፍ (Research Writing) ክፍለጊዜን የሚያስታውሰንን የፁሑፋቸውን አካል ነው፡፡ ለጋዜጣ እየፃፉ መሆኑን ሁሉ ዘንግተው እንዲህ እንደኔ እያጣቀሳችሁ በትምህርተ ጥቅስ (“ ”) ውስጥ እያስቀመጣችሁ ካልፃፋችሁ ከምሁራዊ አቀራረብ የተፋታችሁ ጨዋዎች ናችሁ ይሉናል፡፡

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# ጥንቃቄና ትኩረት የጎደለው

# የታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ <<ገድለ መፈንቅለ መንግሥት>>

*ርዕስ፡- ገድለ መፈንቅለ መንግሥት በኢትዮጵያ 1953 ዓ.ም*
*አዘጋጅ፡- ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ*
*ገጽ፡- 235*
*ዋጋ፡- 80 ብር*
*የታተመበት ዘመን፡- 2004 ዓ.ም.*

የዛሬው መጽሐፍ ጸሐፊ ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ‹‹ቅስም የሰበረው ርምጃ›› (1985)፣ ‹‹አይ ምጽዋ››(1997ዓ.ም. የታተመ)ና ‹‹የአናብስት ምድር፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት የታሪክ ዘገባ (ከ1927-1983ዓ.ም.)››(የታተመው 1999ዓ.ም.) የተሰኙ ሦስት መጻሕፍትን በማዘጋጀት ይታወቃሉ፡፡ አይ ምጽዋ በተሰኘው መጽሐፋቸው (ገጽ XIII) መጽሐፉን ጽፌ የጨረስሁት በ1983 ዓ.ም. ነበር የሚሉን ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ በወቅቱ ያላሳተሙት በግል ሕይወታቸው ላይ አደጋ እንዳይደርስ በመፍራት እንደሆነ ይገልጹልናል፡፡ የዛሬው አስተያየቴ የሚያጠነጥንበት የታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ‹‹ገድለ መፈንቅለ መንግሥት በኢትዮጵያ 1953 ዓ.ም.››ም የመጽሐፉ ሥራ የተጀመረው ሰኔ 1981 ሲሆን የተጠናቀቀው ደግሞ ነሐሴ 2002 ዓ.ም. በመሆኑ 21 ዓመታት የፈጀ የ‹‹ምርምር›› ውጤት ነው ብለን እንድንጠብቅ ያስገድደናል፡፡

**ስለመፈንቅለ መንግሥቱ የተሠሩ ሥራዎች**

ከሃገር ውስጥ ፐ/ር ባህሩ ዘውዴ ከውጭ ዜጎች ክርስቶፎር ክላፋም፣ ሃሮልድ ማርከስ፣ ጆን ማርካኪስ እንዲሁም ማርጋሪት ፔርሃም በዘመናዊ ኢትዮጵያና አስተዳደሯ ዙሪያ ጽሑፎቻቸው ስለመፈንቅለ መንግሥቱ አስተያየት ቢሰጡም ከሁሉም የሰፋ ማብራሪያ ያቀረቡት ሪቻርድ ግሪንፊልድ እኤአ በ1965 Ethiopia: A New Political History›› (ከገጽ 337-452 ይሸፍናል) በሚል ያሳተሙት መጽሐፍ ነው፡፡ ግሪንፊልድ በወቅቱ በቀላሉ ሊገኝ የማይችለውን በነብርጋዲዬር ጀኔራል መንግሥቱ ላይ የተካሄደውን የፍርድ ሂደት ማግኘት መቻላቸው በእጅጉ ጠቅሟቸዋል፡፡ መፈንቅለ መንግሥቱ በተሞከረ ሰዓት በአዲስ አበባ መገኘታቸውም በጉዳዩ ሊሳተፉ ከቻሉ ሰዎች ባሻገር ንጉሡን ራሳቸው ስለጉዳዩ ማወያየት መቻላቸው ነገሩን በጥልቀት ለመመልከት ረድቷቸዋል፡፡ ካልታተሙት ግርማ ፀጋይ ለመጀመሪያ ድግሪ መመረቂያቸው ‹The Abortive Coup D' tat of December 1960› በሚል ያዘጋጁትና ተከስተ መላክነህ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ያዘጋጁት ‹The 1960 Coup D' tat in Ethiopia› (1990 እኤአ) ይጠቀሳሉ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ከተጻፉትም ሻለቃ ቃለክርስቶስ አባይ ስለ1953ቱ መፈንቅለ መንግስት ባጠቃላይና እና የይላቀ ኃይለማርያም ስለኮሎኔል ወርቅነህ የጻፉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አምና በኢጥምተ ስር በተዘጋጀው ውይይት ስለነዚሁ ሰዎች ‹‹ስማቸው እንዲጠራ አንፈልግም›› ዓይነት አስተያየት ለሚሰጡ ሰዎች የሚመች ባይሆንም፤ በዚሁ ዙሪያ ገና ጸሐፊዎቻቸው ለህትመት እያዘጋጇቸው ያሉ በረቂቅ ደረጃ የሚገኙና ወደፊት የህትመት ብርሃን ካዩ በጉዳዩ ዙሪያ የሚኖረንን ስብስብ ስለሚጨምሩልን ሁለት ሥራዎች ሰምቼያለሁ፡፡

**‹‹የታሪክ ዘገባ››፡- ማምለጫ?**


ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ከሦስተኛው መጽሐፋቸው (‹‹የአናብስት ምድር…››) ጀምሮ አቀራረባቸው ታሪክ መጻፍ ሳይሆን የታሪክ ዘገባ ማቅረብ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ የታሪክ ዘገባ እንደ ጽንሰ ሃሳብ ምንድን ነው? በመሰረቱ የታሪክ ዘገባ ስለአንድ ታሪካዊ ፋይዳ ያለው ምንጭ/መረጃ ግኝት የሚቀርብ የቅድሚያ ትንተና ዘገባ ነው፡፡ ይህ በተለምዶ ብዙ ጊዜ የሚደረገው የግኝቱ ባለቤት ወደፊት በሚያሳትሙት መጽሐፋቸው ሙሉ መረጃውን ከትንታኔ ጋር እንደሚያቀርቡ ታሳቢ በማድረግ ይሆናል፡፡ ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ ሥራቸው ‹የታሪክ ዘገባ› እንዲባል የፈለጉበትን ምክንያት ‹‹የአናብስት ምድር…›› በተሰኘ መጽሐፋቸው ሲገልጹ ‹‹የ17ቱ ዓመታት ከሰው ሕይወት አልፎ ከ33 ቢሊዮን ብር በላይ የባከነበት ጦርነት [በመካሄዱና] ይህን ግዙፍ ጉዳይ [መጽሐፋቸው የሚሸፍነው ከ1927-1983 በመሆኑ ይመስላል] በአንድ መለስተኛ መጽሐፍ ሙሉ ታሪክ መስራት የማይታሰብ በመሆኑ [እንደሆነና]… በታሪክ ዘገባ መልክ ቀንጨብጨብ›› አድርገው ወደአንድ መጽሐፍ በመጠቅለል ‹‹የአናብስት ምድር›› ብለው እንደሰየሙት ይነግሩናል (በተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ X)፡፡ የዛሬውንም መጽሐፍ የታሪክ ዘገባ ሲሉ በተመሳሳይ ምክንያት እንደሆነ እንድናስብ ብንገደድም፤ በእውነቱ ርዕሰ ጉዳዩ የሚሸፍነው ጊዜ በቀናት ቢበዛ በሳምንታት በመሆኑ ለዚያኛው መጽሐፍ የቀረበው ምክንያት ሊሠራ የሚችል አይሆንም፡፡ ስለዚህ ‹የታሪክ ዘገባ› የሚለው አቀራረብ ከታሪክ ጸሐፊ ፍዳ (የምንጭ ትንተናና ትርጉም በሚሰጥ መልኩ የተሟላ ትረካ ያለው ጽሁፍ ከመጻፍ) ለማምለጥ የሚደረግ ሙከራ እንዳይመስል እሰጋለሁ፡፡

**ሰነዶችን በመጽሐፍ መልክ የማተም ልምድ**

ለዚህ አስተያየቴ ማጠናከሪያ የሚሆነኝን በርካታ መከራከሪያ ማቅረብ ቢቻለኝም፤ መጽሐፉ ሰነዶችን ከማቅረብ የዘለለ ማድረግ አለመቻሉ ብቻ በቂ ነው፡፡ በመሰረቱ ሰነዶችን በመጽሐፍ መልክ ማተም ለታሪክ ዕውቀታችን ፋይዳው እጅግ የጎላ ነው፡፡ በእርግጥም የዚህ መጽሐፍ ዋና ፋይዳም ይሄው የመጀመሪያ ደረጃ ዋጋ ያላቸውን ሰነዶች በየቤታችን ሼልፍ ላይ እንድናገኘው ማስቻሉ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሥራዎችን አልፎ አልፎ ስናገኝ ደስታችን ከፍ ያለ ነው፡፡ ለምሳሌ የባላምባራስ ማህተመ ስላሴ ወ/መስቀል ‹‹ዝክረ ነገር››፣ የደጅአዝማች ከበደ ተሰማ ‹‹የታሪክ ማስታወሻ›› በተወሰነ ደረጃ፣ የፐ/ር ስቬን ሩቤንሰን ‹‹አክታ ኢትዮፒካ›› በሦስት ቅጽ (አጋር አርታኢያን አሉት)፣ የፐ/ር አሌሳንድሮ ትሪዩልዚና ተሰማ ታአ ‹‹የወለጋ የታሪክ ሰነዶች፡- ከ1880ዎቹ እስከ 1920ዎቹ (እ.ኢ.አ) ቅጽ 1›› ሌሎቹ ሲሆኑ፤ በአቶ ዓለሙ ኃይሌ የተዘጋጁትና በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን አሣታሚነት የታተሙት የአፄ ሠርጸ ድንግልና የአፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል ግዕዝና አማርኛ ትርጉም (1999ዓም) ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ በጳውሎስ ኞኞ ተሰባስበው በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት በ2003 መጨረሻ አካባቢ የታተሙት ‹‹አፄ ምንሊክ›› በአገር ውስጥና በውጪ የተጻጻፏቸውን ሰነዶች ያካተቱት ሁለት መጽሐፎችም ለአቀራረቡ የቅርብ ማሳያዎቻችን ናቸው፡፡

የዛሬው የታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ መጽሐፍም የተዘጋጀው ከመጀመሪያው ምዕራፍ (ከገጽ 1-22) እና ምዕራፍ 9 አንድ ገጽ እንደ መግቢያ(150) እና ከገጽ 171-180 በተለያዩ የክብርዘበኛ መኮንኖች ላይ ስለተካሄደው የፍርድ ሂደት በጭማቂ መልክ ከቀረበበት በስተቀር ሰነዶች ወይም የቃል መረጃዎች እንዳለ ራሳቸውን ችለው የምዕራፍነት ማዕረግ እየተሰጣቸው ነው፡፡ ስለዚህ የሰነዶች ዝርዝርም የመጽሐፍ ማውጫም ተለይቶ ሊኖረው የሚገባ አይመስልም፡፡ ልክ በስቬን ሩብነሰን እንደተዘጋጁት እንደአክታ ኢትዮፒካ ተከታታዮች የሰነድ ዝርዝር ብቻ ሆኖ ሰነዶቹ በተከፋፈሉበት ክፍል ተዘርዝሮ ቢቀመጥ በቂ ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ በታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ አቀራረብ ላይ የሚነሳው ትችት መጽሐፉ የሰነዶችን ስብስብ ያያዘ ብቻ መሆኑን በግልጽ ለማስቀመጥ አዘጋጁ ድፍረት ስላነሳቸው ነው፡፡ ይህን በማድረጋቸው ብቻ መመስገናቸው አይቀርምና፡፡ አዘጋጁ ይሄን በግልጽ ቢያስቀምጡ የሚነሳባቸውን ጥያቄ መሸሽ አይችሉም፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል አንዱ ይሄን ለማድረግ ወሰደ የተባለው ጊዜ ነው፡፡

ገድለ መፈንቅለ መንግሥት በጸሐፊው ፈጀ የተባለው 21 ዓመታት መሆኑ የጸሐፊውን ልፋት እንድናስብ ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የዝግጅቱ መራዘም ያስገኘው አስተዋጽኦ ሲለካ ግምገማው



**በብርሀኑ ደቦጭ**
**(የታሪክ ተመራማሪ)**

የሚያመለክተው ከንቱ ልፋት መሆኑን ነው፡፡ እንኳን ለሕዝብ የሚቀርብ ታሪክ ነክ ዝግጅት ቀርቶ ማንኛውም ደብዳቤ በቂ ጊዜ ሊሰጠው እንደሚገባ አልስትም፡፡ የማስረጃ ማሰባሰብ ሥራም ምን ያህል አታካችና አድካሚ እንደሆነም አልዘነጋም፡፡ ችግሩ ግን አዘጋጁ ሲጀመር ሰነዶቹን ከየት እንዳገኟቸው ባለመግለጻቸው ልፋታቸውን ለመረዳት የማያስችል ያደርገዋል፡፡ ይልቅስ በሌላኘው ‹‹የአናብስት ምድር›› በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ III ያንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት የትብብር ደብዳቤ በመጻፍና ዶክሜንት/ፋይል ያቀረቡልኝ በሚል የሚያመሰግኗቸው 14 ሰዎች አሉ፡፡ ዛሬ እየተነጋገርንበት ባለው መጽሐፍ የተካተቱትን ሰነዶችም ያገኙት በዚያን ጊዜ ነው ብለን ብናስብ እውነት ነው ሊባል ይችላል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የዛሬው መጽሐፍ ፈጀ የተባለውን ጊዜ የሚመጥን ዝግጅት አለማሳየቱን እንረዳለን፡፡ ከአንዳንድ መረጃዎች ተነስተን ማስረጃዎቹን ያገኙት ከ21 ዓመት በፊት ከሆነ ሰነዶቹን እንደየቀናቸው ቅደም ተከተል አስተካክሎ በማስቀመጥ ዛሬ ታትሞ ልናነበው የቻልነውን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ይሄን ያህል ጊዜ መውሰዱ አነጋጋሪ ይሆንብናል፡፡ የአገራችን አዘጋጆች ያለባቸውን የገንዘብ ችግር ሳንዘነጋ ከዚያ በመለስ ማለት ነው፡፡ አዘጋጁ ይሄን ያህል ጊዜም መውሰድ ከነበረባቸው ስለሰነዶቹ ገላጭ መረጃዎችን

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

# "የቃሊቲ ምስጢሮች" እና የታሪክ ተመራማሪው

**ከወሰንሰገድ ገ/ኪዳን**

**እንደመነሻ**

"… ፈትዬ እንዳልበላው እምቢ አለኝ እንዝርቱ
ለካ ከአናቱ ነው የቋንጣው ጥመቱ. . . . ."

አንዲት የወሎ ገበሬ ናት አሉ ይህንን ድንቅ ቅኔ የተቀኘችው፡፡ ቅኔውን የተቀኘችበት ዘመን በውል አይታወቅም፡፡ ብቻ ዱሮ ነው፡፡ ‹‹ዱሮ መቼ ነው?›› ግልፅ አይደለም፡፡ በደፈናው ግን ራቅ ባለ ዘመን የተነገረ ነው የሚለው የሚያስማማን ይመስለኛል፡፡ የሆነ ሆኖ ቅኔዋ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ እዚህ ዘመን ደረሰ፡፡ እኔም ቅኔዋን ለመዋስ ወደድኩ፡፡

የዚህችን ምስኪን ገበሬ ሥነ-ቃል ባስታወስኩ ቁጥር የትርጉሙ ጥልቀትና ምጥቀት ያስደምመኛል፡፡ እኔ ነኝ ያለ ሊቅ፣ እኔ ነኝ ያለ ምሁር፤

ብራና ሙሉ ቃላት ሰብስቦ ግጥም ቢደረድር የእሷን ሁለት መስመር ስንኝ የሚሞላ ሐቅ አይኖረውም ብዬ አስባለሁ፡- ካላጋነንኩ፡፡

እንዲህ የመጠቀና ጥልቅ አንደምታ ያለውን ምስጢር በሁለት ስንኝ ብቻ ቅልብጭ አድርጋ ለመግለፅ ብላ ፊደል የቆጠረች አይመስለኝም፡፡ አስኳላ መግባትም አላስፈለጋትም፡፡ ከየዕለቱ ኑሮዋ መሀል ነው ሐቂቋን እንደዘበት የመዘዘችው፡፡ በህይወት ዘመኗ ከገጠማት ተግዳሮት የገረማትን፣ የደነቃትን፣ ያስጨነቃትን . . . ወዘተ ሁነት ነው ፈልቅቃ ያጋለጠችው፡፡ ት/ቤቷ ኑሮ ነው ማለት ነው፡፡

እናም ስነ-ቃሏን ባሰብኩ ቁጥር ሴትነቷ ጎልቶ ይታየኛል፡፡ የዚያ ዘመን ሴት ልጅና እንዝርት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ መሆናቸውም ይታሠበኛል፡፡ ታዲያ የእንዝርት ቋንጣ ከአናት መሆኑ እንደምን ጠፋት? ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ እንደማይጠፋትም ይታሰበኛል፡፡ እንዲህ ከሆነ ዘንዳ ፈትላ እንኳ እንዳትበላ ያደረጋት ወይም ያስቸገራት ምኑ ነው? ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ አሁንም ሴትነቷ ይገዝፍብኛል፡፡ በሴትነቷ ሰበብ ከጨቅላነቷ ጀምሮ የተጫነባት የተዛባ እሳቤ ተደርድሮ ይከሠትልኛል፡፡

በመጀመሪያ ‹‹የሴት ልጅ ራሥ ወንድ ነው›› የሚለው አሥተምህሮ ደምቆ ይከሰትልኛል፡፡ ወንድ! ወንድ! … እያለ ይቀጥላል፡፡ ወንድሟ፣ ባሏ፣ የቀበሌው፣ የወረዳው ብሎም የአገሪቱ ራስ ሁሉ በወንድነቱ ይጫናታል፡፡ እንደፈቃዷ ሰርታ እንኳ እንዳትበላ ተብትቦ ይዟታል፡፡ በሕይወት ዘመኗ እንዲህ ያለውን መራር እውነት ያስተዋለችው ያቺ ሴት ናት "ለካ ከአናቱ ነው" ለማለት የተገደደችው፡፡ የዚህ ፅሁፍ ዋነኛ ፈትለ-ነገርም (theme) ይኸው ነው፡፡ ፡- "የአናት" ነገር፡፡

**"አናት?!"**

በአ/አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "አናት" ለሚለው ቃል የሚከተለውን ፍቺ ይሠጠዋል፡- (1) መሀል ራስ፣ ጭንቅላት (2) እንጥል፡፡

በዚህ መሰረት ለፅሁፌ አግባብነት የመጀመሪያውን ፍቺ ነው የበለጠ ተመራጭ ሆኖ ያገኘሁት፡፡ መሀል ራስ፣ ጭንቅላት የሚለውን፡፡ ትርጉሙን ትንሽ ፈታ፣ ትንሽ ለጠጥ እናድርገው ከተባለ ‹አናት› ማለት ‹‹የህሊና ቤት፣ የዕውቀት መከማቻ ማዕከል፣ የአስተውሎትና የማመዛዘኛ ማህደር… ወዘተ ነው›› ብንል ስህተት አይሆንም፡፡

ይህ የህሊና ቤት፣ ይህ የማስተዋልና የማመዛዘን ማዕከል ከተበላሸ የሰው ልጅ የቀና ህይወት ሊኖረው አይችልም፡፡ በሌላ አባባል የህሊና ጥመት ከተፈጠረ ወይም ህሊና ከጠመመ እጅግ በጣም ቀላሉ ነገር ከባድ፣ ከባዱ ነገር ውስብስብና አስቸጋሪ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ህሊናን መግራትና የጠመመን አመለካከት ማቃናት የግድ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ የዛሬው ፅሁፌም የመጀመሪያም የመጨረሻም ዓላማም ይኸው ነው፡፡ "የቃሊቲ ምስጢሮች" በሚል ርዕሥ ለህትመት ባበቃሁት መፅሐፍ ላይ የተሰነዘረው ቅጥ አምባሩ የጠፋበትን እና "ከአናቱ የተጣመመውን" ሂስ ተብዬ የተዛባ አመለካከት ማቃናት ነው፡፡

**ከአናቱ የተጣመመው ሂስ**

ከአናቱ የተጣመመው ሂስ ተብዬ ፅሁፍ ለአንባቢያን የቀረበው ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም ለህትመት በበቃው ፍትህ ጋዜጣ ላይ ነው፡፡ ፀሐፊው ለሂስ ተብዬው የተዛባ አመለካከቱ "የቃሊቲ ምስጢሮች - የረፈደባቸው ምስጢሮች?" የሚል ርዕስ ነው የሠጠው፡፡ ፀሐፊው ብርሃኑ ደቦጭ ይባላል፡፡ ፎቶውም ከፅሁፉ ራስጌ ተደንቅሯል፡፡ ከፎቶው ሥር የታሪክ ተመራማሪ መሆኑ ተገልጧል፡፡

የታሪክ ተመራማሪ ብርሃኑ ደቦጭ ዓላማው "የቃሊቲ ምስጢሮች" መፅሐፍ ላይ ሂሳዊ ዳሰሳ (ቅኝት) ማድረግ ይመስላል፡፡ ሂሳዊ ቅኝት እንዲመስልለትም የመፅሐፉን ርዕስ፣ የገፅ ብዛት፣ የታተመበትን ዘመንና የሚሸጥበትን ዋጋ ዘርዝሯል፡፡ ይሁን እንጂ ገና ከመነሻው አላማውን ስቶ ቁጭ ይላል፡፡ ይህንን አባባሌን ለማስረገጥ ደግሞ በሸውራራ ዕይታ የታጨቀውን የመጀመሪያውን አንቀፅ ብቻ ማጤን ይበቃል፡፡ ይህ ማለት ሂስ ተብዬው ፅሁፍ ከአናቱ ተበላሽቷል ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ነገር ከአናቱ ተበላሸ ማለት ደግሞ ለማንም ምንም ፋይዳ አይኖረውም፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ሐያሲው ብርሃኑ ደቦጭ (ፅሑፉ ሂስ ከተባለ) ለማለት የፈለገው ነገር ለራሱም የገባው አይመስልም፡፡ ምነው ቢሉ? አስቀድሞ የሠነዘረው ሃሳብ ከኋለኛው፣ የኋላ ኋላ የሚያነሣው ሃሳብ ደግሞ ከቀደመው ጋር ይጣረስበታል፡፡ በራሱ ሀሳብ ከራሱ ጋር ይጋጫል፡፡ ሌላም ሌላም ሌላም ማለት ይቻላል፡፡

ለማንኛውም የታሪክ ተመራማሪው ብርሀኑ ደቦጭ በ"የቃሊቲ ምስጢሮች" መፅሐፍ ላይ የሰነዘረው ሂስ ተብዬ አስተያየት ከአናቱ የተበላሸ መሆኑን ለማሳየት ከመጀመሪያው አንቀፅ አንስተን አስረጅ እየነቀስን እንመልከት፡፡ እነሆ፡-

"… ልክ እንደዚሁ በሀገር ውስጥም ጋዜጠኛ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን የቃሊቲ ምስጢሮች በሚል ርዕስ አዲስ መፅሐፍ ጀባ ብሎናል፡፡ <u>ይህ መፅሐፍ የገኘውን ቡድን የሚያስቀይም ባለመሆኑ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ፍቅር ከወዲሁ በማግኘት አሳይቷል …"</u> (ሠረዝ የኔ)

ያሳዝናል፤ አንድ ሃያሲ ለዚያውም የታሪክ ተመራማሪነትን ዕውቅና የደረበ ሰው አንድ መፅሐፍ እከሌን ያስቀይማል፣ እከሌን አያስቀይምም የማለት ድፍረት ማግኘቱ ነው የሚያሳዝነው፡፡ ኸረ ለመሆኑ አንድን መፅሐፍ፣ መፅሐፍ የሚያሰኘው ምንድነው? ገዥውን ፓርቲ ማስቀየም? አይመስለኝም፡፤ ተቃዋሚዎችን ማስደሰት ብቻ? ይኼም አይመስለኝም፡፡ እንዲህ አይነቱ ዕምነትና ዕውቀት ከየት የመጣ እንደሆነ ሊገባኝ አይችልም፡፡ እንዲገባኝም አልፈልግም፡፡ ቢሆንም እንዲህ አይነቱ እሳቤ የሚመነጨው ነገር ከአናቱ ሲበላሽ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

የዚህች ሀገር ችግር ደግሞ ይኼ ይመስለኛል፡፡ የገዢው ፓርቲም ሆነ የተቃዋሚዎች ፓርቲም ችግር ይኸው ይመስለኛል፡፡ ‹‹ከእኔ ጋር ካልሆንክ፣ እኔ የምለውን ካላመንክ፣ እኔ እንደማስበው ካላሰብክ ጠላት ነህ›› ብሎ መፈረጅ ነው ችግሩ፡፡ ገዢውም ፓርቲ ሆነ ተቃዋሚዎች እኔን ምሰል፤ በአንድ ግባ ነው ፈሊጣቸው፡፡ ይህንን ስል የሠካራሙ ሠውዬ ታሪክ ታወሠኝ፡፡

**ሰውዬው!**

ሰውዬው አንድ ቀን መጠጥ ቀማምሶ ወደ ቤቱ ሲያዘግም ማጅራት መቺዎች አቀመሱት፡፡ ከዚያ ቀን በኋላ ለብ ብሎትና አመሻሽቶ ወደ ቤቱ ሲገባ ድንጋይ ከእጆቹ የማይታጣ ሆነ፡፡

አንድ እኩለ ሌሊት እንዲሁ እየተወላገደ ወደ ቤቱ ሲሄድ ከፊት ለፊቱ አምስት ያህል ሰዎች ሲመጡ ተመለከተ፡፡ ጋቢ ትከሻቸው ላይ ጣል አድርገዋል፡፡ ነጠላ ደርበዋል፡፡ ሰዎቹ ከለቅሶ ቤት ነው የወጡት፡፡ ቢሆንም ሰካራሙ አላመናቸውም፡፡ "እያንዳንድሽ በአንድ ግቢ!" አለ ድንጋዩን አውጥቶ፡፡ ‹‹ምን ሆነህል?›› ቢሉት "የሆንኩትን እኔ አውቃለሁ፤ ሁልሽም በአንድ ገብተሽ ታልፊ እንደሆነ እለፊ!" ሲል ደነፋ፡፡ አምስቱ ሰዎች ለብ እንዳለው ገባቸው፡፡ በአንድ ተርታ ተሠልፈው አልፈውት ሄዱ፡፡ ዞሮ ቢያያቸው እነሱ ጉዞአቸውን ቀጥለዋል፡፡

የእኛ ሀገር ፖለቲካና ፖለቲከኞችም ችግር እንደሠካራሙ ያለ ነው፡፡ በአንድ ግባ ብቻ! እኔ ነኝ አዋቂ ብቻ! እኔን ተከተለኝ ብቻ! ታዲያ ውጤቱ ምን ይሆናል? እሳት በብቻ!"

**እኔን የገረመኝ**

እኔን የገረመኝ "የቃሊቲ ምስጢሮች" መፅሐፌን ለመተቸት የተነሣው የታሪክ ተመራማሪ ብርሃኑ ደቦጭ ከመነሻው መሳቱ፤ መሳሳቱ ብቻ አይደለም፡፡ ከትምህርቱ ዘርፍና (ከተመረቀበት) ከፀሐፊነቱ አንፃር ነገሮችን አለማየቱ ነው፡፡ እንደ ታሪክ ተመራማሪነቱና እንደ ፀሐፊነቱ ብዕሩን የሚያነሣው "ህዝብ የማወቅ መብት አለው!" የሚል ዕምነት አንግቦ ነው ብዬ እገምታለሁ፡፡ ይህ ማለት በጎውንም መጥፎውንም ካለአድልዎ ማሳየት ማለት ይመስለኛል፡፡ ብርሃኑ ይህንን ያጣዋል ብዬ አላምንም፡፡ አውቆ የተኛን እንዲሉ ካልሆነ በቀር፡፡

ከሁሉ በላይ የገረመኝ የሚከተሉት ሂስ ተብዬ የቃላት ጥርቅም ብቻ የሆኑ ገለፃዎች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው እነሆ፡- "የቃሊቲ ምስጢሮች ዓይነተኛ መረጃ የተቃዋሚ አመራሮች የሚረቡ እንዳልሆኑ ማጋለጥ ነው" ይላል ብርሃኑ፡፡ ይቀጥላል፡-

<u>"…ይሁንእንጂ ጋዜጠኞቻችን በተቃዋሚዎች በኩል ያለውን ድክመት ለመረዳትና ለመተንተን እስር ቤት ድረስ አብረው እስኪጓዙ መቆየት ነበረባቸው ወይ ተብሎ እንዲጠየቅ ያስገድዳል፡፡ የአገሬ ጋዜጠኞች ሲሆን ሲሆን ባሉ ተጨባጭ ነጥቦች ላይ ተመስርተው የፓርቲዎቹን ዕጣ ፈንታ ለመተንበይ የሚያስችል በቂ መረዳት ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡፡"</u> (ሠረዝ የኔ)

ድንቄም መረዳት! የታሪክ ተመራማሪው ብርሃኑ ደቦጭ መረዳት እንዲህ ከሆነ መማር አፈር በልቷል ማለት ነው፡፡ አንድ ጋዜጠኛ ያላየውን፣ ያልጨበጠውን፣ ያልዳሰሰውን፣ በእጁ ያልያዘውን መረጃ እንዴት ሊፅፍ እና ሊታመን እንደሚችል አይገባኝም፡፡ በሌላ መልኩ ጋዜጠኛ ነቢይ መሆን ነበረበት አይነት ተራ ሙግት ነው፡፡ ከቋቱ ጠብ የማይል ሙግት፡፡ ይኼንን እዚህ ላይ ልተወውና ብርሃኑ ደቦጭ አንጉል ወደሰነዘረው ሌላኛው ሃሳብ ልዝለቅ፡፡

በምርጫ 97 ሳቢያ የታሠሩት ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ከተፈቱ አምስት አመት አካባቢ እንደሆናቸው፣ በታሣሪዎቹ ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ደርዘን የሚሞሉ መፅሐፍት መታተማቸውን ያትታል፡፡ እንደእሱ አገላለፅ ተፈቺዎቹ "በመፅሀፍቶቻቸውና በተለያዩ ሚዲያዎች <u>ውስጠ ነገራቸው ሁሉ የአደባባይ ዕውቀት ሆኗል፡፡</u> ታዲያ አሁን ወሰንሰገድ መፅሐፉን የቃሊቲ ምስጢሮች አሰኝቶት ሲመጣ <u>ለእኛ እስካሁን ያላወቅነው ምን ነገር ይኖር ይሆን</u> እንድንል አድርጎናል… .›› ይለናል፡፡

በዚሁ አንቀፅ ሥር ጥቂት አረፍተ ነገሮችን ወረድ ብሎ ደግሞ ጥቂት ገፆችን ጠቅሶ መፅሐፉ አዲስ ነገር እንደያዘ ይመሰክራል፡፡ እዚያው በዛው ደግሞ የሚከተለውን ሀሳብ ይሠነዝራል፡፡

‹‹ይሁን እንጂ የምናወራው ስለአጠቃላይ መፅሐፉ ስለሆነ በዚህ መፅሐፍ የተካተቱትን ነገሮች <u>እንደግኝት ልንቆጥራቸው አንችልም፡፡ ምስጢርም አይደሉም</u>. . .››

የታሪክ ተመራማሪው ብርሃኑ ደቦጭ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# የጠቅላይ ሚኒስትሩ ዲሞክራሲና ልማት ጉራማይሌ



**በሙሉነህ አያሌው**

muleayalew@yahoo.com

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመሯት አገር በአብዛኛው የምትተዳደርበት የፖለቲካ ፍልስፍና ጠንካራ መሠረት የሌለውና ወጥነት የማይስተዋልበት መሆኑን ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ምሁራን ይገልፃሉ። ለዚህም የኢህአዴግ አመራሮች አገሪቷን ከተቆጣጠሩበት ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ እስከዛሬም ድረስ እያወጧቸው የሚገኙት የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በየወቅቱ የመቀያየርን ሁነት ምሁራኑ በአስረጅነት ያቀርባሉ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቅርቡ ከሪቻርድ ዳውደን ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ የዚህ የተንሻፈፈ ምልከታ ነፀብራቅ መሆኑንና የሰጡትን ምላሽ ከተለያዩ የሙግት ማዕዘኖች ማየት እንደሚቻል ቃለመጠይቁን የታዘቡ ተንታኞች ይናገራሉ።

ጠ/ሚኒስትር መለስ በቃለ መጠይቃቸው ላይ ‹‹በዲሞክራሲና በዕድገት መካከል ቀጥተኛ ተዛምዶ የለም። ዲሞክራሲ ብቻውን ሊቆም ይችላል። (There is no direct relationship between democracy and growth. Democracy can stand on its own) ››ብለዋል። በእርግጥ እርሳቸው እንደሚሉት ልማትና ዴሞክራሲ ተነጣጥለው መታየት ይችላሉን? ወይንስ የልማትና ዴሞክራሲ ፅንሰ ሀሳቦችን ለየብቻ ነጣጥሎ ማየት በአዲሱ የኢህአዴግ ፖለቲካ ፕሮግራም የራሱ ምልከታ ይኖረው ይሆን? የሚለውን በሚገባ መፈተሽ ተገቢ ይመስላል።

## ባህላዊ ዲሞክራሲ

በዘመናዊው የፖለቲካ ፍልስፍና አስተምህሮ አንድ የተረጋጋን ማህበረሰብ ለመመስረት ከሚያስፈልጉ ነገሮች መካከል የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዋነኛው መሆኑ ይገለፃል። ሳይመር ማርቲን ሊፕሴት የተባሉት እውቁ የፖለቲካ ሳይንስ ጠበብት ይህንን ሃሳብ ይበልጥ አጠንክረው ወደ አደባባይ ካወጡት ምሁራን መካከል በግንባር ቀደምትነት ስሙ ተጠቃሽ ነው። ሊፕሴት የዴሞክራሲን ምንነት እና አተገባበር ለመረዳት ከሚያግዙን መንገዶች መካከል ስርዓቱ በሌሎች አገራት ውስጥ የተጓዘባቸውን ተሞክሮዎች በንፅፅር ማቅረብ በትንሹ ሁነቱን ለመረዳት የተሻለና አስፈላጊ እንደሆነ አፅንኦት ሰጥቶ ይሞግታል። “Some social requisites of democracy, economic development and political legitimacy” በሚለው ፅሁፉ በአንድ አገር የዴሞክራሲ ስርዓትን በራሱ እንዲቆም ከሚያግዙት ነገሮች መካከል የሌሎች ደጋፊ ተቋማት በነጻነት መደራጀት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን ይገልጻል።

ሳይመር ሊፕሴት በሌላኛው “Political sociology” በሚለው ፅሁፉ የዲሞክራሲ ደጋፊ ከሚባሉት ተቋማት በተጨማሪም የማህበረሰቡ ነባር ወግና ባህል ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ሚና በሰፊው ለመዳሰስ ሞክሯል። በወቅቱ ባህል በዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ላይ ባለው ሚና ላይ ተነስቶ የነበረውን ንትርክ ለመቋጨት በሚል የጻፈው ሰፊ ጥናታዊ ጽሁፍ በዲሞክራሲ ስርዓት ላይ የሚነሱ ማህበራዊ ተግዳሮቶችን በሚገባ ለመፈተሽ አግዞታል። ከነዚህ ማህበራዊ ተቋማት መካከል በተለይ ሃይማኖት ህዝቡን አንድ ወጥ ወደሆነ የፖለቲካ ማህበረሰብ የመቀየር ብሎም የማስተሳሰር ትልቅ ተፅዕኖ እንደነበረው ይገልፃል።

ከሊፕሴት በተቃራኒው ሌላኛው የፖለቲካ ተንታኝ ኽርነስት ግሪፊትዝ ሃይማኖት ብቻውን አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብንና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መርህን ለዘላቂው ደግፎ ሊያስቀጥለው እንደማይችል የጀርመንን ተሞክሮ በምሳሌነት በመጥቀስ ከላይ የቀረበውን የሊፕሴት ሙግት መሰረተ ቢስ እንደሆነ ይከራከራል። ግሪፊትዝ በዋናነት በተሳተፈበትና ሌሎችም ተጠቃሽ ፀሐፊያን በጋራ ባሳተሙት “Capitalism, socialism and democracy” በሚለው መፅሐፍ ላይ ይህንን መከራከሪያ ሃሳብ በስፋት አብራርቶታል። በዚህ ንትርክ ላይ አንዳንዶቹ በአውሮፓ የነበረውን የጁዴይዝም-ክርስትና (Judeo-Christianity) ቅርስና አስተምህሮት ለዴሞክራሲ ግንባታ የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል ቢሉም ሌሎች በዚህ ኃሳብ ተቃርኖ ላይ የቆሙ ምሁራን በበኩላቸው ከኃይማኖት ይልቅ የኢኮኖሚ ተቋማት በተገቢው ሁናቴ ባለመጠናከራቸው ምክንያት አገራቱ ወደባሰ የፖለቲካ አዘቅት ይዟቸው ሊሄድ እንደሚችል ይሞግታሉ። ለዚህ በምሳሌነት ሊጠቀሱ ከሚችሉ አገራት መሃከል ጀርመን እና ጣሊያን መሆናቸውን እነዚህ ምሁራን ይገልፃሉ።

በሁለተኛው የአለም ጦርነት ዋዜማ አካባቢ በተከሰተው የኢኮኖሚ ድቀት ምክንያት በደረሰው ማህበረሰባዊ ቀውስ፣ በሃይማኖት መደላደል ላይ የተመሰረተውን ህዝብ በጦርነቱ ወቅት ከተነሱት የፋሽስትና የናዚ አምባገነን መንግስታት ጨቋኝ አገዛዝ እጅ ሊታደጋቸው እንዳልቻለ እነ ኮልማን ጨምረው ይሞግታሉ። ኮልማንም ይሁን ሌላኛው ምሁር ትሮው ከላይ በተጠቀሰው በጋራ ባሳተሙት መጽሐፋቸው ላይ የጀርመን ሃይማኖተኛ ህዝብ የአምባገነኑን የአዶልፍ ሒትለር መንግስትን ድጋፍ ከማሳጣት ይልቅ ለስርዓቱ መደላደል የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያደርግ እንደነበር ታሪክ ጠቅሰው ይከራከራሉ። በኢትዮጵያ ላይ የምርምር ስራዎቻቸውን ያቀረቡ ተንታኞች የኢትዮጵያ ኃይማኖታዊ ተቋማትም ይሁኑ የኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያለኢኮኖሚ መሠረት እና ህዝብ ተቀባይነት የሚፀናበት ምንም ህልውና ሊኖረው እንደማይችል ከአፄው ሥርዓት በአንዴ ወደ ደርግ ሥርዓት የተሸጋገረበት ፖለቲካ ዑደት በማሳያነት ጠቅሰው ይከራከራሉ።

## የዴሞክራሲ መሠረቶች

በአብዛኞቹ የፖለቲካ ተንታኞች ዘንድ ዴሞክራሲ የሚለው ፅንሰ ሀሳብ የተለያየ ትርጉም ቢሰጠውም የብዙዎቹን ንድፈ ሃሳባዊ ማጠንጠኛ ዞሮ ዞሮ ወደ አንድ ጥቅል ትርጉም ማቅረብ እንደሚቻል ምሁራን አፅንኦት ሰጥተው ይጠቅሳሉ። ጆሴፍ ሹንፒተር የተባለው ፀሐፊ የዲሞክራሲ ጥቅል ትርጉም ሁለት መታያዎች እንዳሉት ይገልጻል። የዴሞክራሲ መርህ በመሠረታዊነት ሁለት አላማዎች አሉት የሚለው ፀሐፊው በቅድሚያ የሚያወሳው መርሑ በሥርዓት ውስጥ የሚካሄድን የስልጣን ሽግግር ለማቀላጠፍ ህገ-መንግስታዊ ዋስትና ይሰጠዋል የሚለው ሲሆን ሁለተኛው የዲሞክራሲ አላማ በህዝብ ዘንድ ለሚነሱ የማይታረቁ አስተሳሰቦች የመጨረሻውን ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ሥርዓት የማስወሰን ሚና ይኖረዋል የሚለው ነው።

ከሹንፒተር ጠቅላይ ኃሳብ ጋር የሚስማማው ሌላኛው የጀርመን ሶሾሎጂስት ማክስ ዌበር ነው። ዌበር “Essay in sociology” በሚለው ፅሑፉ የሹንፒተር ንድፈ ኃሳብ በውስጡ የፖለቲካ ቀመር (Political formula)፣ መንበረ ሥልጣኑን ተቆጣጥረው ስለተቀመጡ ባለሥልጣናት፣ ከስልጣን ውጪ ያሉትና በህጋዊ መንገድ ከመንግስት በተቃርኖ የተሰለፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸው እርስ በርስ መስተጋብርን ጨምሮ በስራ ላይ ያለው የፖለቲካ ምህዳር ለጥምረታቸው ያበረከተው አዎንታዊ አስተዋፅኦ በአጠቃላይ ለዲሞክራሲ ምሉዕነት ከግምት ውስጥ መግባት እንደሚገባው ይሞግታሉ።

የፖለቲካ መጫወቻ ምህዳሮች መስተካከል አስፈላጊ ነው የሚባለው በዲሞክራሲ ሥርዓት ያስገኛቸዋል ተብሎ ለሚጠበቁ ሁለት መሰረታዊ ውጤቶች አንፃር መሆኑን ጃኖዊትስ እና ማርክስ “Competitive pressure and democratic consent” በሚለው ፅሁፋቸው ላይ ያብራሩታል። እነዚህ ፀሐፊያን እንደሚሉት ከሆነ የፖለቲካ ስርዓቱ ሰላማዊ ‹‹መጫወቻ›› ምህዳር ማዘጋጀት ከተሳነው ‹‹ውስጥ›› ባሉ ባለስልጣናት የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ‹‹ውጭ›› ካለው ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት እድላቸው የመነመነ ከመሆኑም በተጨማሪ በስልጣን ላይ ለተቀመጡ ግለሰቦችና አገዛዛቸው ማህበረሰቡ ህጋዊ እውቅና ስለሚነፍገው የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዳይገነባ ያደርገዋል የሚለው የመጀመሪያ ሲሆን በሁለተኝነት የተቀመጠው መከራከሪያ ደግሞ የፖለቲካው ጨዋታ ሌሎች ተወዳዳሪዎችን የሚያበረታታ ምህዳር መፍጠር ካልቻለና ለአንድ ፖለቲካ ቡድን ብቻ ወገንተኝነት ካሳየ ስርዓቱ ከዴሞክራሲያዊ ይልቅ ኃላፊነት የጎደለው መንግስት እንዲመሰረት ያደርገዋል የሚለው ነው። የኢህአዴግን መንግስት የእነዚህ ሁለት የስርዓት ሂደት ፍፃሜዎች ድምር ውጤት አድርገው ፀሐፊያኑ የሚወስዱት አሁን በስልጣን ላይ ያሉ የፓርቲው አመራሮች ያለምንም ተቀናቃኝ ለብቻቸው የመንግስትን ሥልጣን እንዳሻቸው በመቆጣጠር በፖሊሲ ማውጣት ላይ የህዝቡ ተሳትፎ እንዲቀንስ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ የዚህ አይነት አካሄድ በስተመጨረሻ አገሪቱ በአንድ ጥቅል ፓርቲ አገዛዝ ስር የመውደቅ እጣ ፈንታ ይገጥማታል ብለው ሲፈሩት የነበረው እውነት ሆኖ በማግኘታቸው እንደሆነ ይከራከራሉ።

## ዴሞክራሲ እና ኢኮኖሚ

በአንድ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ለተመሰረተ መንግስት ለህልውናው ወሳኝ ናቸው ከሚባሉት ነገሮች መካከል ዋነኛው የሚያስመዘግበው የኢኮኖሚ እድገትና ህዝቡ ለአገዛዙ የቸረው የ‹‹ስልጣን ህጋዊነት›› ተጠቃሽ ናቸው። ዴሞክራሲ ያለእነዚህ ተቋማት ተደጋጋፊ ጥምረት የትም ሊደርስ አይችልም የሚሉት እነዚህ ተንታኞች በተለይ የማህበረሰቡ የነፍስ ወከፍ የገቢ እድገት፣ የትምህርት ደረጃ፣ የከተሜነት መስፋፋት፣ የኢንዱስትሪ ተቋማት እመርታ ከዴሞክራሲ ግንባታ ተነጥለው መታየት እንደማይችሉ ዲሞክራሲና ኢኮኖሚን አጣምረው ያጠኑ ምሁራን ይጠቅሳሉ።

ዴቪድ አሽተን “An approach to the analysis of political system” በሚለው ፅሑፍ በአደጉ እና ገና በማደግ ላይ ባሉ አገራት መካከል ላለው የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ ልዩነት ምክንያት በኢኮኖሚው እድገት ያስመዘገቡት ውጤት መሆኑን ይገልፃሉ። አብዛኞቹ ምዕራባውያን አገራት ያስመዘገቡት የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ግንባታ ሳይፈርስ ለረጅም ጊዜ ተጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር ምክንያት የሆነው ፖለቲካውን ደግፈው የያዙት የኢኮኖሚ ተቋማት መሆናቸውን ሲገልፁ፣ የዚህ አይነት ተሞክሮዎች በተለይ ደሃ በሚባሉ የላቲን አሜሪካና የአፍሪካ አገራት በብዛት አይስተዋልም። እነዚህ ደሃ አገራት አስቀድመው ማጠንከር የሚገባቸውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ሳያጎለብቱ የዴሞክራሲ ስርዓትን እንገነባለን ማለታቸው ፈፅሞ የማይቻል መሆኑን ሮበርት ዳል “A preface to democratic theory” በሚለው ፅሁፋቸው ይገልፃሉ።

የሮበርት ዳልን ሀሳብ አጠንክረው ከፃፉት የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን መካከል ሌላው ተጠቃሽ ምሁር ሊይን ሽኖን ነው። ሽኖን የኢኮኖሚ እድገትን በንፅፅር የሚያስቀምጠው በፖለቲካ የ‹‹ራስ ገዝ አስተዳደር›› ከሚባለው ንድፈ ሐሳብ ጋር ነው። ሽኖን “Is level of government related to capacity for self-government?” በሚል ርዕስ አሜሪካ ጆርናል ላይ ባሳተመው ፅሁፍ ዜጎች የራስ ገዝ አስተዳደርን በሙሉ ፍቃድ መመስረት እስከቻሉ ድረስ በኢኮኖሚ ዘርፍ አመርቂ ውጤት የማያስመዘግቡበት አንዳችም ምክንያት ሊኖር እንደማይችል ይጠቅሳል። እንደ ተንታኞቹ ገለፃ ከሆነ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሃ አገራት ለኋላ ቀር የኢኮኖሚ እድገት መመዝገብ ምክንያቱ ማህበረሰቡ ገዢዎቹ በገነቡት የፖለቲካ ስርዓት ላይ መተማመኛ የማጣታቸው ሁነት መሆኑን አውስተው ለአንድ አገር ኢኮኖሚ መዳበር የተገነባው የዴሞክራሲ ስርዓት በማህበረሰቡ ዘንድ ባለው ተቀባይነትና ህጋዊነት ላይ እንደሚጸና ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው ላይ አብራርተዋል።

## ዴሞክራሲና ህጋዊነት

መንግስት በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው ተቀባይነት እንዲጨምር ከሚያግዙት ሁነቶች መካከል በኢኮኖሚው መስክ ያስመዘገባቸው ውጤታማ ተግባራቶች መሆናቸውን ተንታኞቹ ይገልፃሉ። የመንግስት ውጤታማ ኢኮኖሚ እድገት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመጣና ማህበረሰቡም የዚህ እድገት ተቋዳሽ መሆን እስከቻለ ድረስ አገዛዙ ያለው ህጋዊ ተቀባይነት ለረጅም ጊዜ በስልጣን እንዲቆይ እንደሚያስችለው እነዚህ ፀሐፊያን ይጠቅሳሉ።

የኢኮኖሚው እድገት፣ ለስልጣን ባለቤቶች ከሚቸራቸው ህጋዊ ተቀባይነት በተጨማሪም ለዴሞክራሲያዊ ግንባታ መረጋጋት የሚኖራቸው አስተዋፅኦ ቀጥተኛ ተዛማጅነት ይኖራቸዋል ይላሉ ተንታኞቹ። ከዚህ በተፃራሪው ኢትዮጵያን እያስተዳደሩ ያሉ መሪዎች የአገሪቷን የኢኮኖሚ እድገት አንድ ደረጃ ፈቅ ማድርግ ባለመቻላቸው የተነሳ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚገጥማቸውን ተቀባይነት እና ህጋዊነት የማጣት ስሜት ለመሸፈን ሲሉ አገሪቷንና ህዝቦቿን በአምባገነን አገዛዝ እንድትተዳደር ከማድረግ የዘለለ አማራጭ እንዳይኖራቸው እንዳደረጋቸው በአገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራኑ ይጠቅሳሉ። በእንደዚህ አይነት አኳኋን የሚጓዙ ደሃ አገራት በፖለቲካ መጻኢ እጣ ፈንታቸው መበታተን አልያም የማያባራ የእርስ በርስ ጦርነት ሊሆን እንደሚችል ምሁራኑ ይጠቅሳሉ።

ፕራናብ ባርዳን “Democracy and development: A complex relationship” በሚለው ፅሁፉ ዴሞክራሲ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሰረፀ ሊሰጣቸው የሚችላቸውን ሦስት መሰረታዊ ነጥቦችን ለመዳሰስ ሞክረዋል። አንደኛው ዴሞክራሲ ዜጐች ያላቸውን ሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ለማስጠበቅ የሚኖረው ዋስትና ሲሆን ሁለተኛው ህገ-መንግስቱ እና የፖለቲካው ጨዋታ በሚያጐናፅፋቸው መተማመኛዎች ምክንያት በገዢዎች ላይ የሚያሳርፈው የተጠያቂነት ስርዓት ነው። ሶስተኛውና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚቀርበው ዲሞክራሲ በተወሰነ የጊዜ ገደብ የፖለቲካ ስልጣንን ለተመረጠው አካል የሚሸጋገርበትን ስርዓት ማመቻቸት መቻሉ ነው። ባርዳን በትንሹ ዴሞክራሲ በእነዚህ ተቋማት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ የዜጎችን መሰረታዊ መብት በመጠበቁ ህብረተሰቡ ለአገር እድገት ማበርከት በሚገባው አስታዋፆኦ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ያግዘዋል ይላል። የባርዳንን ሀሳብ ይበልጥ አጠንክረው ካወጡት ሌሎች ፀሐፊያን መካከል ፔርሰን እና ታበሊን ተጠቃሽ ናቸው። እ.ኤ.አ በ2005 በጋራ ባሳተሙት ፅሁፍ ላይ ለዴሞክራሲያዊ እና አምባገነን መንግስታት መነሳት መሠረታዊ ምክንያቱ ከኢኮኖሚ እድገት አልያም ውድቀት ጋር በቀጥታ ሊነፃፀር እንደሚቻል ይጠቅሳሉ። “Democracy and development: Devil in the details” በሚለው ፅሁፋቸው በፖለቲካው መስክ የሚካሄደው ለውጥ በቀጥታ ከኢኮኖሚ ተቋማት ጋር የሚኖረውን ውጤት የተለያዩ የመንግስት ስርዓቶች ዋቢ በማድረግ ይሞግታሉ። የዴሞክራሲ መንግስታት ሥርዓት በዳበረባቸው አገራት የሚካሄድ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ በኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነትም ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ በአዎንታዊ ጐኑ የሚጠቀስ ነው ይላሉ።

የፖለቲካ ለውጦች ይዟቸው በሚመጣው አዳዲስ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ሳቢያ አንዱ በአንዱ ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ የጐላ እንዲሆን ያደርገዋል። አምባገነን መንግስታት የራሳቸውን ስልጣን መደላደል ለረጅም አመታት ለማቆየት ሲሉ የሚቆምሯቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ህግጋት ተቋማቱን ከማሽመድመድ በተጨማሪም በአገሪቷ ውስጥ ለሚነሱ ቀውሶች ተጠያቂ እንዲሆን ያደርጋቸዋል ይላሉ ፀሐፊዎቹ።

## ዴሞክራሲ እና የግጭት ፖለቲካ

በዴሞክራሲያዊ ስልጣን ሽግግር እና ኢኮኖሚ እድገት መካከል የሚኖሩ ተፃሮዎች እየሰፉ በመጡ ቁጥር በማህበረሰቡ ውስጥ ስለሚፈጠሩ ችግሮች ፖሊሲ አጥኚዎች ሁለት መሰረታዊ ትምህርቶችን ሊወስዱ ይገባል ይላሉ። ዳውንስ እና ብሩስ በጋራ ባሳተሙት “Development and democracy” በሚለው ፅሁፋቸው ከእነዚህ ሶስት መሰረታዊ ትምህርቶች መካከል በቀዳሚነት የሚጠቅሱት በማደግ ላይ ያሉ አገራት የሚያስመዘግቡት የኢኮኖሚ እድገት የዴሞክራሲን ባህል ግንባታ ቀስ በቀስ ያመጣዋል የሚለው የተዛባ አስተሳሰብ ነው። የዚህ ትንታኔ ሙግት የሚያርፈው ዜጎች የጠበቁት የኢኮኖሚ እድገት የጥቂቶች መጠቀሚያ ብቻ መሆን ሲጀምር ማህበረሰቡ በአምባገነን የአገዛዝ ሥርዓት የመውደቅ እጣ ፈንታ ይገጥመዋል የሚለው መከራከሪያ ነው። የመንግስት ሹማምንትና ወታደራዊው ክንፍ በተመዘገበው ውሱን የኢኮኖሚ እድገት ተጠቃሚ ሆኖ ሌላው ማህበረሰብ የጥቅም ተጋሪ መሆን ካልቻለ፣ ተጠቃሚዎቹ የያዙትን የተደላደለ መንበር ላለመልቀቅ ሲሉ ሥርዓቱን የበለጠ አምባገነንና ኢኮኖሚውን የጥቂቶች መጠቀሚያ ብቻ ያደርገዋል ይላሉ።

ሁለተኛው ምሁራን ፖሊሲ አውጪዎችን የሚመክሩት ከውጭ ለጋሽ አገራት ስለሚገኘው የገንዘብ እርዳታ እና አጠቃቀም ነው። ከአለም ባንክና የተለያዩ የገንዘብ ተቋማት ለደሃ አገራት የሚለግሷቸው ገንዘቦች መሠረት ልማቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ የተማረ የሰው ኃይልን ለማፍራት በቀጥታ መዋላቸው ማህበረሰቡን መካከለኛ ገቢ ወዳለው የእድገት ደረጃ ያሳድገዋል የሚለው ትንታኔ ፈፅሞ የማይሆን ነው ይላሉ።የእነዚህ ገንዘብ ምንጮች አጠቃቀም ትክክለኛውን ቁጥጥር እስካልተደረገባቸው ድረስ ለታቀደላቸው አላማ ከመዋል ይልቅ የመንግስትን ጡንቻ እንዲፈረጥምና አምባገነንነቱን ይበልጥ እንዲጠነክር እንደሚያደርገው ይከራከራሉ። ስለዚህም ገንዘብ በዴሞክራሲ ሥርዓት ካልተደገፈ የሚኖረው ማህበረሰባዊ ፋይዳ ምንም ነው ይላሉ ተንታኞች።

## ጠ/ሚንስትሩ ምን እያሉ ነው?

የልማትና የዴሞክራሲ ጥመርታ በይበልጥ የሚያስፈራቸው አምባገነን መንግስታትን እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ። እንደ ኢህአዴግ አይነት መንግስት የኢኮኖሚው እድገቱን ከዴሞክራሲ መርህ አንፃር ለይተው ማስቀመጥ የፈለጉበትን ምክንያት ኮለየር እና ሮኸር በሦስት ከፍለው ያስቀምጡታል። ሁለቱ አጥኚዎች “Democracy, Development and conflict” በሚለው ፅሁፋቸው ኢኮኖሚው እያደገ በመጣ ቁጥር ማህበረሰቡ የሚያነሷቸው የይገባኛል ጥያቄዎችም እየሰፉ እንደሚመጡ ይጠቁማሉ። የመጀመሪያው ገቢንና ተጠያቂነት ያነፃፀሩበት ሞዴል ነው። ኢኮኖሚው እየጎለበተ በመጣ ቁጥር ስለሚገኘው የገቢ መጠን ማህበረሰቡ የመጠየቅ ፍላጐቱ አብሮ በመጨመሩ ምክንያት ባለስልጣኖቹን ወደተጠያቂነት ደረጃ ያቀርባቸዋል። ይህ ደግሞ ለአምባገነን መንግስታት የሚዋጥ ባለመሆኑ ለግጭት መነሳት መንስኤ ይሆናል። ሁለተኛው የኢኮኖሚ እድገትን ተጠቅመው መበልፀግ የሚፈልጉ ባለስልጣናት የሚፈፅሙት ሙስና ነው። ጉቦ በሚሹና መልካም አስተዳደር በሚጠይቁ ግለሰቦች መካከል የሚፈጠረው አለመግባባት ለግጭት ሌላኛው ምክንያት ሲሆን ሦስተኛው የገቢ ማደግ ከማንነት ጋር የሚያያዝ ጥያቄን ማስነሳት መቻሉ እንደሆነ እነ ኮለየር ያብራራሉ። ዜጎች የገቢ ምንጫቸው እያደገ በመጣ ቁጥር መሰረታዊ ፍላጐታቸውን ስለሚያሟላ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ደረጃም ከፍ እያለ ይመጣል ይላሉ። በተለይ የርዕዮት ዓለም እና የማንነት ጥያቄዎችን መንግስት ማስታረቅ ካልቻለ ልማቱ ብቻውን ከዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው አንፃር ሊቆም እንደማይችል እነዚህ ምሁራን ይገልፃሉ።

# የኤፍ.ኤም.ሬድዮ ጣቢያዎቹ ዓላማ ማዝናናት ወይስ ማዘናጋት



ሚኪያስ ዲኖ

አንዳንድ ሀሳቦች አሉ መፍታት አቅቷቸው በተኮራመቱበት የሌላ ሀሳብ ፀሐይ ሲያርፍባቸው ሙቀት አግኝተው ነፍስ የሚዘሩ:: የባለፈው ሳምንት የዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ ‹‹ፍሬንድ ዘመኑ የኤፍ.ኤም ነው›› የተሰኘው ቁንፅል መጣጥፍም ላልሰመረለት ምንጠራ ሲወጣ እግረ-መንገዱን ያዳፈንኩትን ሀሳብ እንድቆሰቁሰው ጐንትሎኛል::

ይህን ስለመሰለው ንሸጣቸው /Inspiration?/ ማመስገን ይኖርብኛል:: በኔ እምነት ግን ዶር/ በድሉ በዚህ መጣጥፋቸው ለትውልድ ከሚያሰጋው ገዳይና ፈዋሹ ተሰባጥሮ ከበቀለበት አምታች ጫካ መድረስ ቢችሉም በትክክል መርዘኛውን ዛፍ ግን መለየት አልቻሉም:: ስለዚህም መጥረቢያቸውን እንዲያው በዘፈቀደ ቀልባቸው ባልወደደው ዛፍ ላይ አሳርፈዋል::

በጋራ መሰረት ላይ ከሚያቆሙን እውነታዎች የመጀመሪያው ሁሉም የኤፍ.ኤም ጣቢያዎች (ከሸገር 102.1 በስተቀር) በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ መሆናቸው ነው:: በተጨማሪም ከነዚህ የራድዮ ጣቢያዎች የሚገኘው ትሩፋትም ሆነ ጉዳት የሚያስመሰግነውም ሆነ የሚያስወቅሰው አዘጋጁን ክፍል ነው::

እነዚህን ጣቢያዎች በባለቤትነት የሚቆጣጠረው መንግስት እነዚህን ‹‹አንደበቶቹን›› ለዓላማው ማስፈፀሚያ እንደሚጠቀምባቸው አይጠረጠርም:: ከሁሉም በፊት ደግሞ ፕሮፓጋንዳው ይቀድማል::

ብቻ ራዲዮኑ ሲከፈት ‹‹አደግን፣ ተመነደግን፣ ቀን ወጣላችሁ፣ በቀን ሶስቴ እየበላችሁ ነው፣ በነፃነት እየቦረቃችሁ ነው፣ የእኩልነት ዘመን ነውና ተሰብሰባችሁ ጨፍሩ›› ይለንና ከልማታዊ አርቲስቶች የአንዱን ዘፈን ይጋብዘናል::

ከዚህ በመለስ በሁሉም የኤፍ.ኤም ራዲዮ ጣቢያዎች ከሚቀርቡትና ሰፊ የአየር ሰዓት ከሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ዋነኛው ስፖርት (በተለይም እግር ኳስ) ሲሆን የዚህ ዝግጅት ተከታታይ ደግሞ ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ነው::

በተመሳሳይም ለአምባገነን ስርዓት ህልውና የፍርሃት ምንጭ ከሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ወጣቱ ቀዳሚው ነው:: ከሞላ ጐደል የአለም አብዮቶች የተመሩት በወጣቶች ነው:: በአለም ታሪክ በጥፋትም በልማትም የወጣቱ ሚና ጉልህ ነው:: ስለዚህም ይሄ አገዛዝ የወጣቱ ውሎና አዳር ያባንነዋል:: እያንዳንዷን እንቅስቃሴውን መከታተልና እርምጃ መውሰድ ይፈልጋል:: እንደ አመቺነቱ በጥቅም አባብሎ የስርዓቱ ሎሌ ማድረግ ተቀዳሚ ምርጫው ነው::

በዚህ ያልተሸነፈ ከዕለት ጥቅሙ ከግል ብልፅግናው አሻግሮ ማየት የቻለ ‹‹በትክክለኛው መንገድ ላይ አይደለንም›› ለማለት የደፈረ ግን ይገለላል፣ ይፈረጃል፣ ይሳደዳል ካስፈለገም ይታሰራል::

በእጅ አዙር የሚያጠቃቸው የሚያሽመደምዳቸው ክፍሎችም አሉ:: ለዚህ የእጅ አዙር ጥቃት ዋነኛው መሳሪያዎች እነኚህ የራዲዮ ጣቢያዎች ናቸው:: ስለጥቃቱ ስለማደንዘዣው ከማውራታችን በፊት በጤናማው አመለካከት ማህበረሰባችን ከነዚህ ጣቢያዎች ወይም ከዝግጅቶቹ ምን ማግኘት እንደነበረበት እንመልከት::

ብንታደል ኖሮ መንግስት ለዜጐቹ እንደ አባት ነበር:: እንደ መልካም አባትም ለትውልዱ የሚበጁ ዝግጅቶችን በባለሙያዎች አስጠንቶ (በተለይ) ወጣቱን-ስለታሪክ፣ ስለሀገር ፍቅር፣ ስለስነ-ምግባር፣ ስለ-ነፃነት፣ ስለስነ-ፅሁፍና ፈጠራ በሚያስተምሩ ዝግጅቶች ሊያንፀው፣ ሊያስተባብረው ሊያነሳሳው ይገባ ነበር::

ስላልታደልን (ስላልታገልን?) ግን መንግስት ለኛ አባት ሳይሆን ባሪያ አሳዳሪ ሆኖብናል:: ስለዚህም ከላይ የተመለከትናቸውን ነገሮች መጠበቅ ሞኝነት ነው:: ምክንያቱም በፖለቲካ የነቃ፣ ታሪኩን ጠንቅቆ የተረዳ፣ አቅሙን ያወቀ፣ በኪነ-ጥበብ የታነፀ ሕዝብ ለአገዛዝ ስርዓት የተመቸ አይደለም::

እናማ አምባ-ገነኑ ስርዓት በሚቆጣጠራቸው የሬዲዮ ጣቢያዎች ሲገለገል ከፕሮፓጋንዳው ባሻገር ድርብ ዓላማው አድርጐ የሚንቀሳቀሰው በዕውቀት አልባ አስተዳደር የተከሰተውን ሀገራዊ ዝቅጠት የማያስተውል ለሀገሩ ጉዳይ ባይተዋር ሆኖ በባዕድ ርዕስ በባዕድ ውሎና አዳር የሚትከነከን ቀላዋጭን ማፍራት ነው::

ስፖርት (በተለይም እግር ኳስ) ለአውሮፓውያን አንድም መዝናኛ አንድም ትልቅ የገቢ ምንጭ ነው:: የዚህ ዘርፍ ጉዳይ በኛ ሀገር ዓውድ (Context) በመልካምና መጥፎ ሚዛን የሚቀመጥ ሳይሆን ከቅደም ተከተል አንፃር የሚገመገም ነው::

ዘርፈ ብዙና ውስብስብ ሀገራዊ ጉዳች ተደቅነውብን ሳለ ታላቁን የቤት ስራችንን ገሸሽ አድርገን ቀጥሎ ሊመጣ በሚገባው መዝናናት ተጠምደናል:: ጋሪው ከፈረሱ ቀድሟል:: ስለዚህ ወደፊት መጓዝ አልቻልንም::

ገዥዎቻችን ዙሪያውን እንዳንመለከት እንደ አህያ የፊት የፊቱን ብቻ እንድናይ ግራና ቀኙን ጋርደው አበጅተውናል:: በጨዋታ ማርከው ተጫውተውብናል:: አዎ ሚዲያው የራሱን ግዳይ ጥሏል:: ምርኮኞቹን በየዕለቱ እየሰበሰበም መሰረት በሌለው የህልም ዓለም ያንሳፍፋቸዋል::

ኢትዮጵያን የመሰለች በችግሮች የተተበተበች ሀገር መፍትሄዎቿን የምትጠብቀው ከወጣቶቿ ነበር:: ሽማግሌዎቿማ ያንኑ ያረጀ ቁማራቸውን እየቆመሩ ነው:: ዛሬም ወጣትነታቸውን ባሳለፉበት እንካ ሰላንትያ፣ የስልጣን ሽሚያ፣ መገለባበጥ፣ መጠላለፍ... እዚያው አዙሪት ውስጥ ናቸው::

‹‹የአብዮት አቀጣጣይ›› ይሆናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ወጣት በራሱ (በሲስተሙም) ተሰናክሎ በየጫት ቤቱ፣ በሺሻና ሀሺሽ ማጨሻ ቦታዎች ተፋፍጐ ሞራሉ ወኔው ወድቆ ስብዕናው ላሽቆ ሲታይ...

በሌላ በኩል ከሆዱ አሻግሮ መመልከት ተስኖት ስለምግቡ ሲል ነጻነቱን አሳልፎ ሰጥቶ በገዛ ፈቃዱ የባርነትን ሰንሰለት ሲያጠልቅ...

ከዚህም የተረፈውን መንግስት ሚዲያዎችን እየጋለበ በያለበት መድረስ ‹‹ስፖርት እግር ኳስ፣ ፕሪሚየር ሊግ፣ ሻምፒዮንስ ሊግ፣ ዝውውር ጥሎ ማለፍ›› እያለ ያልጠማውን መረጃ ሲግተው...

እንዲህ አስረካቢዎች ለግመው ሀገር ተረካቢዎች ፈዘው ሲታይ የነፃነት ጊዜ ርቀቱ ከምፅአት ቀን ርቆ አይታይም?

በእርግጥም ይሄ ለአገዛዙ አንድ ጉልበት ነው:: የመንግስት ማኪያቬላዊ እቅዶችም እየሰመሩ ነው:: የአውሮፓ እግር ኳስን የመመልከት ጉጉትና ጥምን የፈጠሩት ሚዲያዎች ናቸው:: በተደጋጋሚ ቅጥቀጣ ነው ወጣቱ መሀላው ሳይቀር ‹‹እግር ኳሳዊ›› የሆነው::

የሚዲያዎቹ የማፍዘዝ ተልዕኮ ግቡን መቷል:: ለዚህም ነው በልማት ስም በከተማ በገጠር የወገኖቹ ከቀያቸው መፈንቀል ግድ ሳይሰጠው በአውሮፓ እግር ኳስ ከክለብ ወደ ክለብ ተከፍሏቸውና በፈቃዳቸው ለሚዘዋወሩ ተጫዋቾች ዕጣ ፈንታ ሲጨነቅ የሚታይ ትውልድ የበቀለው::

ግን እውነት እኛ የኢትዮጵያ ወጣቶች የራሳችን አንገብጋቢ ርዕስ የለንም? ከዕጣ-ፈንታችን ከህልውናችን ከደማችን የተዋሃደች ቀዳሚ ርዕሳችንስ ሀገራችን አይደለችም?

ምንም እንኳ እግር ኳስ እየተመለከትን ቢመስለንም እኛ ራሳችን በገዥዎቻችን የፖለቲካ ጨዋታ እንደ ኳስ ከወዲያ ወዲህ እየተለጋን አይደለም?

ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀረቆራችን ላይ ‹‹መዝናኛ›› የምትባል ኮፍያ ጣል አድርጐ መዘዋወርስ ይበጀናል? በዝምታችን በቸልታችንስ ለሀገር ውድቀት አባሪ ተባባሪ አልሆንምን?

# ኦዲት ያልተደረጉ የፖለቲካ ክስረቶች

ዳንኤል ተፈራ

እነሆ ወርሀ ሰኔ ገባ:: ተስፋ ያዘሉ የደመና ቁልሎች፣ የክረምቱን መግባት በሚያበስረው ነጐድጓድ እየታጀቡ ምድርን ማጠጣት ይጀምራሉ:: ከዝናብ ጋር ስር የሰደደ ቁርኝት ያለው የሀገሬ አርሶ አደርም ከሚወዳቸው በሬዎቹ ጋር ተቀናጅቶ፣ ማረሻ እንደጨበጠ ውሎ ጀምበር በምዕራብ አድማስ ስትሸሸግ እሱም ወደ ጐጆው ይሸከፋል:: ወርሃ ሰኔ ለገበሬው ከተፈጥሮ ጋር ግብግብ የሚገጥምበት፣ ተስፋ ሰንቆ የእህል ፍሬዎችን ለመሬት አደራ የሚሰጥበት፣ ፋታ የሌለበት የጥድፊያ ወር ነው:: ህይወትም ይቀጥላል... የገጠሩ ለፍቶ አዳሪ የህይወት መልክ እንደዚህ ይገለጣል::

ሰኔ በከተማስ? በከተማም በወርሃ ሰኔ ውጥረት ነው:: መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ‹‹ኦዲት›› በሚባል የሒሳብ ቋንቋ የሚጠመዱበት፤ የዓመቱን በጀት ፍሰትና ውድቀት የሚገመግሙበት፤ ወጪና ቀሪያቸውን የሚለዩበት፤ የተመደበውን በጀት ቀሪ ገንዘብ ገቢ ላለማድረግ ያልታሰበ ዕቃ የሚሸመትበት ወር ነው:: ‹‹ኦዲት›› ማድረግ የሚለው ቃል ‹‹መመርመር›› የሚል አቻ ትርጉም ቢሰጠው ይገልጠው ይሆናል:: የሚመረመረው በጀቱና ጉድለቱ ነው:: ወርሃ ሰኔ በከተማው ደግሞ ከላይ የጠቀስኩትን አይነት መልክ አለው::

አይገርምም! በገጠር ገበሬው አንዷት ቅንጣት ፍሬን አብዝቶ እንዲሰጠው ለመሬት አደራ የሚሰጥበት፤ በከተማ ደግሞ የተዘራው ዘር ፍሬው የሚሰበሰብበት ነው:: የህይወትን አንፃራዊነት የሚገልፅ ይመስላል:: ግን ስንት ያልተወራረዱ ሀገራዊ የትውልድ ክስረቶች ይኖሩን ይሆን? የትውልድ ሀገራዊ ክስረታችን ኦዲት ይደረግ ቢባልስ ትርፍና ኪሳራችን ስንት ይሆን? የዚች አጭር ፅሁፍ አላማም የተዝረከረኩና ለዘመናት የተቆለሉ የትውልድ ክስረቶቻችንን መዘርዘር አይደለም:: እሱማ እንዴት ይሆናል? ከሆነ ቁልል ነገር ላይ ቅንጣቷን አንስቶ የማሳየት ያህል ብላችሁ ውሰዱልኝ::

ከየት እንጀምር? ኦዲት ያልተደረጉ ክስረቶቻችን ከየት ጀመሩ እንበል? ቅንጣቷን ለማሳየት ሩቅ መሄድ እንደሌለብን እንስማማ:: በመቀጠልም ሀሳቡን ጠበብ እናድርገውና የፖለቲካ ክስረቶችን እንይ- ያውም ኦዲት ሳይደረጉ ተቆልለው ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገሩትን:: ‹‹የየትኛውን ትውልድ?›› የሚል ጥያቄም እንደሚነሳ እገምታለሁ:: የእኔንና የአባቴን ትውልድ የፖለቲካ ክስረት ነዋ!

ኦዲት ያልተደረጉ የፖለቲካ ችግሮች እየተቆለሉ ለዛሬው ትውልድ አስፈሪ ምስል ፈጥረው ሲያስቃገፉት ማየት እንዴት ያማል? ዛሬ በሀገር ጉዳይ መሳተፍ፣ ስለሀገር መወያየት፣ ፖለቲካ ማውራት አደባባይ ወጥቶ በሰላማዊ መንገድ መጠየቅ፣ ‹‹ራበኝ›› ብሎ ሰልፍ መውጣት፣ የምሁራን በዝምታ መዋጥ፣ የዜጐች ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱ ከንፈር ከመምጠጥ ባለፈ ትንፍሽ አለማለት፣ ‹‹ጥርጥር›› በሚባል ገመድ ራስን ገንዞ መንከላወሻ ማጣት... እነዚህ በሀገራችን ላይ የሰፈኑ ሀገራዊ ፍርሃቶች የመጡት ኦዲት ካልተደረጉ የትውልድ የፖለቲካ ክስረቶች አይደለምን?

እኛ በአይናችን ያላየነው ግን ደግሞ የሰማናቸው የትናንት ታሪኮች፤ ዛሬ ደግሞ በአይናችን የምናየውና እየኖርነው ያለ ህይወት የሚነግረን አለመግባባቶች ‹‹ኦዲት›› የሚደረጉት በሰከነ ንግግርና በመግባባት አይደለም:: እንዴ ጠመንጃስ ምን ሊሰራ፤ እስር ቤቶችስ ምን ይሁኑ? የምናውቀው መፍትሔ፣ ከመሪዎቻችን ያየነው የችግር መፍቻ ቁልፍ ‹‹መሳሪያ›› ነው:: አንድ ወዳጄ እንዳጫወተኝ ‹‹ባለፈው ስርዓት በአደባባይ ይገድሉና ፎክረው ሲያበቁ ‹እሬሳችሁን አንሱ!› ይላሉ:: አሁን ደግሞ ይገድሉና ሬሳውን አብረው ያፋልጉሃል ነበር›› ያለኝ:: ግርድፍም ቢሆን እውነት ነው::

ሒሳባቸው ያልተወራረደ ግርድፍ እውነቶች በሽበሽ ናቸው:: ለምን በስህተት እንጀምራለን? በስህተት መጀመር ከመሪዎቻችን ያየነው ነው:: ያለባቸውን ኪሳራና ትርፍ ሳያወራርዱ፤ ያተረፉትና ያጐደሉት ኦዲት ሳይደረግ እግሬ አውጭኝ ያሉት ኮሎኔል መንግስቱና ጓዶቻቸው ኦዲት ያልተደረገ የስንት ንፁህን ደም አለባቸው? ቢያንስ እንኳ ገና ወደ ስልጣኑ ከመምጣታቸው ልክ እንደ ቀልድ 10 ሳንቲም ጢርርር አድርገን ‹‹ጐፈር፣ ዘውድ!›› እንደምንለው አይነት ፍርድ በመፍረድ ወደ 60 የሚጠጉ የንጉሱ ሹማምንትና መኳንንት ላይ ሞት ሲፈርዱ፤ መፍረድ ብቻ ሳይሆን እንደ ምናምንቴ በፍጥነት ሲያስወግዷቸውና እጃቸውን በደም ሲለቀልቁ ከመስማት በላይ ምን ታሪካዊ ክስረት አለ? በስህተት መጀመር የምላችሁ ይሄንን ነው::

በስህተት የተጀመረው የደርጉ ስርዓትም በስህተት ተደምድሟል:: ብቻ በወቅቱ የነበረው ያለመደማመጥና አቅልን የመሳት ፖለቲካ ያስነሳው እሳት ይህችን ሀገር ክፉኛ ለብልቧታል:: እስቲ አንድ ጥያቄ እናንሳና ወደሚቀጥለው እንሸጋገር:: በደርጉ የ17 ዓመታት የአገዛዝ ጊዜ የደረሱብንን የፖለቲካ ክስረቶችና ክስረቶቹ ያመጡብንን ፍዳ በምን እንመዝነው? አንድ ሙሉ ትውልድ ከነምናምንቴው ከውጭ ተዝቆ በመጣ ርዕዮተ-ዓለም መሞከሪያ ይሆናል? የአሁኖቹ ገዥዎቻችን እኮ ‹‹ኦዲት›› ያልተደረገ የፖለቲካ ስርዓት ውጤቶች ናቸው::

የአሁኖቹ ማለቴ ኢህአዴግን ነው:: ኢህአዴግ ኦዲት ያልተደረገ ፖለቲካ ተቀብሎ እስካሁንም ክስረቱንና ልማቱን ኦዲት ሳያደርግ ቀጥሏል:: አሁን ስጋቴ ሒሳቡ ያልተወራረደ አሮጌ ፖለቲካ ከነኪሳራው ለቀጣዩ ትውልድም እንዳይተላለፍ ነው::

የተጠራቀሙ የፖለቲካ ክስረቶች ኦዲት የሚደረጉት በፖለቲካ ሀያሲ ነው:: እመኑኝ የፖለቲካ ሀያሲ ያስፈልገናል:: እንዳለመታደል ሆኖ የፖለቲካ ሀያሲዎች የሉንም:: የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ህይወት ሀያሲዎች የሉንም:: ሀያሲ የሌላት ሀገር ደግሞ ስህተቷን ለማረም ትቸገራለች:: እኛ የምናውቀው በጣም ጥቂት የሥነ-ፅሁፍ ሀያሲዎችን ነው::

እነዚህ የፖለቲካ ሀያሲዎች እስከሚመጡ እኛ እንፃፍ:: ኢህአዴጎችም ልክ እንደጣሉት የደርግ መንግስት የጀመሩት በፖለቲካ ክስረት ነው:: የፖለቲካ አዋቂዎች በተደጋጋሚ እንደሚያነሱት የፖለቲካ ክስረታቸው የሚጀምረው በርና መስኮት አጥታ የማታውቀውን ታላቅ ሀገር በርና መስኮቷን በማሳጣት ነው:: አዎ! ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችው በዘመነ ኢህአዴግ ነው:: ያውም ገና ወደ ስልጣኑ እንደወጡ:: ይሄ የፖለቲካ ክስረት ሒሳቡ ገና አልተወራረደም::

አሁንም የፖለቲካ አዋቂዎች እንደሚሉት እነ አቶ መለስ ሀገሪቱን በር አልባ ለማድረግ ከመጣደፍ ይልቅ ቆም ብሎ ማሰብ ይጠበቅባቸው ነበር:: የያዙት እኮ የሀገር ጉዳይ ነው:: የሚያስቆጨው ደግሞ ኳሷ በነሱ ቁጥጥር ስር ነበረች:: እነ አቶ መለስ አሁን የጐን ውጋት የሆነችው የቀድሞዋ አካላችን ከኤርትራ ኢትዮጵያ መገንጠሏን ባያፀድቁላት ኖሮ የሌላውን ዓለም ይሁንታ ለማግኘትና እንደ ሀገር ለመቆም ትቸገር ነበር:: ታዲያ ወደቡን ‹‹ግመሎቻቸውን ውሃ ያጠጡበት›› ሳይሆን ይባል የነበረው ‹‹እውቅና እንድንሰጣችሁ ከፈለጋችሁ አሰብን መልሱ›› ነበር:: ከዚህ በላይ ፖለቲካን በክስረት ከመጀመር ሌላ ምን አለ?

በነካካ እጃችን ከዚያው ከኤርትራ ጋር በተያያዘ ከደረሰብን ኦዲት ያልተደረገ የፖለቲካ ክስረት ሳንወጣ የድንበሩን ጉዳይ እናገኛለን:: ከ70ሺ በላይ ወጣት በሁለቱ ሀገሮች ዳግም ጦርነት የተገበረበት የኢትዮ-ኤርትራ የድንበር ጉዳይ ሌላው ትልቁ የፖለቲካ ክስረት ነው:: አሁንም ድረስ ከውጥረትና ከጦርነት ያልተለየው ይሄው የድንበር ጉዳይ ‹‹ወደቡንም ምኑንም ይዘሽ ሂጂ›› የተባለችው ኤርትራ ስትገነጠል ድንበሩን በወጉ ማስከለልና ዓለማቀፍ እውቅና እንዲያገኝ ማድረግ ተገቢ ነበር የሚሉ በርካታ ሰዎች አሉ:: ኢህአዴግ ግን ይሄን አላደረገም:: ‹‹ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል›› እንደሚባለው ልሉ ቋጠሮ አስር ዓመት እንኳን ሳይቆይ ተፈታ:: እንደገና ‹‹ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር›› ተባለ:: የበርካታ ወጣቶች፣ ህይወት፣ ሀብትና ንብረት ወደመ:: ‹‹ሉዓላዊነትህ ተነካ›› ብለው ያስቆጡትና የውጭ ጥቃት የማይችለው የኢትዮጵያ ህዝብ ኤርትራን ሊሰለቅጥ ሲል ‹‹ቁም!›› ተባለ:: ይሄ ሁሉ ሆኖም፤ ጉዳዩ አልጀርስ ደርሶና ተመልሶ እንኩሮ ሆነ:: አሁንም ድረስ አልተፈታም:: እና ይሄ የፖለቲካ ክስረት መቼ ኦዲት ይደረግ?

ሁለት ግዙፍ ግዙፍ የፖለቲካ ክስረቶችን 20 ዓመት ዝቅ ብለን ካየን ይበቃናል:: የሚያሳዝነው ክስረቱ አሁንም መቀጠሉ ነው:: እስቲ ከአሁኖቹ የፖለቲካ ክስረቶች ጥቂቶቹን እንይና የሳምንቱን ጦማር እናሳርግ::

ፖለቲካ ከሚባለው ማህበራዊ ሳይንስ ጀርባ ‹‹ስልጣን›› የሚባል አሳቲ ሰይጣን ይገኛል:: ከስልጣኑ ስር ደግሞ እንደኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ህዝብ አለ:: (በሰለጠኑት ሀገሮች ህዝብ ከላይ ስልጣን ከስር ስለሆነ ነው) ስለዚህ ህዝብ ስልጣኑን በማይቆጣጠርበት ሁኔታ ፖለቲካው በግለሰቦች እጅ ይወድቅና ክስረቱና ልማቱ በአንድ ግለሰብ ትከሻ ወይም ይሁንታ የሚወሰን ይሆናል:: ይሄ ደግሞ ለአንድ ሀገር የፖለቲካ ክስረት በር ይከፍታል:: በግለሰቦች ውሳኔ የተነሳ የከፈልነውን ዕዳ ከእኛ ከኢትዮጵያውያን በላይ ማን ያውቃል?

መንግስቱ ኃ/ማርያም ‹‹አንድ ሰው እና አንድ ጥይት እስከሚቀር እንዋጋለን!›› ብለው ሲያውጁ ማንን አማከሩ? ፖለቲካው በግለሰቦች የሚዘወር ሲሆን አንድ ግለሰብ በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዜጐች ህይወትና ሀገር ላይ ሊፈርድ ይችላል:: መንግስቱ ከነቅዠታቸው ተወግደው የተተኩት አቶ መለስም የኪሳራ ፖለቲካ ከማራመድ አልተቆጠቡም:: ዴሞክራሲውም፣ ልማቱም፣ ፖሊሲውም፣ ብቸኛ ተናጋሪውም፣ ተንባዩም... መለስና መለስ ብቻ ሆነዋል:: ወደድንም ጠላንም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ማለት መለስ ሆነዋል::

ይሄው ፖለቲካውን ግለሰቦች ላይ የማንጠልጠል በሽታ አሁንም አለቀቀንም:: ስለዚህ አቶ መለስ ከከሰሩ ኢትዮጵያ ከሰረች እንደማለት ሆነ:: አቶ መለስ ‹‹በቃ አባይን መገደቡን ትቸዋለሁ!›› ካሉ ይቆማል ማለት ነው:: ‹‹እግር እንቆርጣለን!›› ካሉም ይቆርጣሉ፤ ‹‹ሽብርተኛ!›› ብለው ከፈረጁም ይግባኝ የለውም... በአጠቃላይ ‹‹ሰማይ አይታረስ ንጉስ አይከሰስ›› የሚሉት ዓይነት ነው:: ከዚህ የበለጠ የፖለቲካ ኪሳራ ከየት ይመጣል? ይሄኛው ክስረትስ በየትኛው ኦዲተር ነው ኦዲት የሚደረገውና ሒሳቡ የሚወራረደው?

እንግዲህ በጥቂቱም ቢሆን ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በየጊዜው እንደሚቆለለው የብድር ዕዳችን የፖለቲካችን ችግርም እየተቆለለ ነው:: ከዚህ በፊት ሶሻሊዝም ተሞክሮ አልተሳካም:: አሁን ደግሞ በግድም ቢሆን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሔደናል:: ይሄን የተሻለ ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አንድም ችግር የለም:: እንደውም ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚመች ህዝብ ነው:: ይሄንን ጨዋነቱንም አሳይቷል:: ችግሩ ያለው መሪዎቻችን ላይ ይመስለኛል:: ችግራቸው ደግሞ ለህዝቡ አለመፍቀድ ነው:: እነሱ በቀደዱለት ቦይ ብቻ እንዲፈስ ይፈልጋሉ ይሄ አስተሳሰባቸውም ሀገራችንን ኦዲት ያልተደረገና የከሰረ ፖለቲካ አራማጅ ያደርጋታል:: ክስረቱን ለመፈተሽ ደግሞ ትዕግስትና መደማመጥ ያስፈልጋል:: ግን እሱም የለም:: ስለዚህ ኦዲት ያልተደረገው የፖለቲካ ክስረታችን ቀጥሏል:: ገና የሚቀጥልም ይመስላል:: ይሄ ትውልድ ግን ጠንቀቅ ማለት ይገባዋል::

የፍትህ ዓምድ

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

# የውል መሰረታዊያን ምን ምን ናቸው?

ግለሰባዊ ነፃነት በማህበረሰብ ውስጥ መንፀባረቅ መቻሉ የማህበረሰቡ ስርዓት ለሰዎች ጉራማይሌ ፍላጐትና አስተሳሰብ የሚሰጠውን ቦታ ያሳያል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ስርዓት ውስጥ የሚኖር ማህበረሰብም እንደ ስልጡን ህብረት ተደርጐም ይወሰዳል፡፡ ይሁንና ግለሰባዊነትን ብቻ እያቀነቀኑ መንቀሳቀስ ደግሞ ጥቂት ከማፍጨርጨር ውጭ ከህብረቱ ጋር አብሮ መራመድ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡ ይህ ማለት ግን በጋርዮሻዊ እና በጉበዝ አለቆች የሚመራ ህብረት ረጅም ርቀት ይጓዛል ወደሚል መደምደሚያ አይወስደንም፡፡ የሰዎች ፍላጐት በተናጠል ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ውጭ በማህበረሰባቸው ውስጥ በመብትና በግዴታ ተወስኖ መቀመጡ በራሱ የግለሰብ ነፃነት የት ድረስ እንደሆነ ስለሚያሳይ አንድ ግለሰብ በሌላው ላይ ተሻግሮ መብት የሚጋፋበት፣ ያለአግባብ የሚከብርበት፣ ግዴታውን የማይወጣበት፣ ለህግ ተገዢ የማይሆኑበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ ሰዎች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ አንዱ ከሌላው በብዙ መንገድ ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ ግንኙነቱም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በመብትና በግዴታ የታጠረ ነው፡፡ ጠዋት ከቤታችን ወጥተን ማታ እስክንመለስ ድረስ ያለን የዕለት እንቅስቃሴ መደበኛና ኢ-መደበኛ በሆነ መብትን የማስከበርና ግዴታን የመወጣት ሂደት ውስጥ የሚመላለስ የዘወትር ክንውን ነው፡፡ ታክሲ ውስጥ ገብተን ወደምንፈልግበት ቦታ ለመድረስ ለተጠቀምንበት ታክሲ የምንከፍለው ገንዘብ ግዴታን መወጣት ሲሆን ታክሲ ውስጥ ቁጭ ብለን በከፈልነው ቦታ ልክ እንዲያደርሰን ከባለታክሲው ደግሞ ለእሱ ግዴታ የሆነ የእኛን መብት እንጠብቃለን፡፡ በመብትና በግዴታ የታጠረ የሰዎች ግንኙነት ‹‹ውል›› በመባል ይታወቃል፡፡ ውል በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ወሳኝ ከሆኑት ግንኙነቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡ በግለሰቦች መካከል ከሚደረገው የውል ስምምነት ሌላ፤ ትክክለኛ የዴሞክራሲ ስርዓት ባለበት ሀገር በምርጫ መንግስታትን ወደስልጣን ማምጣት በህዝብና በመንግስታት መካከል የሚደረግ ውል ነው፡፡ ለመሆኑ በግለሰቦች መካከል የሚደረግ ውል በውስጡ ምን ምን ነገሮችን ሲይዝ ህጋዊ ውል ይባላል? የሀገራችን የፍትሐብሔር ሕግስ እንዴት ያየዋል?

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ በተለይም ከውልና ግዴታዎች ጋር በተያያዘ ጥናት ያደረጉት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቺቺኖቪችና ህጉን ያረቀቁት ሬኒ ዴቪድ የግዴታ ውሉን ለማርቀቅ የሲዊዝ የፍትሐብሔር ህግን መሰረት እንዳደረጉ ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የፈረንሳይ አንዳንድ ህጐችንም ጨማምረውበታል ይላሉ፡፡ ታዲያ ከዛሬ 51 ዓመት በፊት በእነኚህ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች የተረቀቀው የኢትዮጵያ የውል ህግ ምን ምን ነገሮችን ይዟል? ለዛሬ አንድ ህጋዊ ውል በውስጡ ማሟላት ያለበትን ነገሮች እናያለን፡፡

የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1675 ውል ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ሲሰጥ ‹‹ውል ማለት ንብረታቸውን የሚመለከት ግዴታዎችን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ባላቸው ተወዳዳሪ ግንኙነት በሁለት ወይም በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው›› ይላል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው በሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት ህጋዊ ውል ለመባል ከሚያስፈልጉት አበይት ነገሮች ውስጥ የመጀመሪያው ውሉ የሚፈፀመው ንብረትን የሚመለከት ግዴታዎችን ለማቋቋም ወይም ለመለወጥ ነው፡፡ እነዚህ ‹‹ንብረት›› የሚባሉ ቁሶች በኢትዮጵያ የንብረት ህግ መሰረት የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ በመባል የተቀመጡ ሲሆን እሴታቸውም በገንዘብ ሊቀመጥ ወይም ሊገለፅ የሚችሉትን ነው፡፡ ከንብረት ውጭ የሚደረግ ስምምነት ህጋዊ ውል ተደርጐ አይወሰድም፡፡ ልጆችን በህገ-ወጥ መንገድ ከአንድ ግለሰብ ወደሌላ ማዘዋወር፣ ትዳርን መሰረት ያደረገ የገንዘብ ልውውጥ መሰረቱ ንብረት እስካልሆነ ድረስ ህገ-ወጥ ስምምነት እንጂ ውል አይሆንም፡፡ ሌላው ነገር ውል በውስጡ ግዴታዎችን የማቋቋም ወይም የማስቀረት ስምምነት ሊያካትት ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን ግን መሰረቱ ሊሆን የሚገባው ንብረትና ንብረት ብቻ ነው፡፡ ሶስተኛው ነጥብ አንድ ውል ተፈፀመ የሚባለው ስምምነቱ ከላይ የተገለፁትን ነገሮች መሰረት አድርጐ ሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል ሲደረግ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል (ድርጅትን) ያጠቃልላል፡፡

ከላይ የተቀመጡት መሰረታዊያን እንደተጠበቁ ሆነው የኢትዮጵያ የውል ህግ የውል አቋሞች በሚል በአንቀጽ 1678 የሚከተሉትን መሰረታዊ ነገሮች ይዘረዝራል፡፡ አንድ ውል የሚፀና ውል ነው ለማለት ሦስት ሁኔታዎች ያስፈልጉታል፡
-

ሀ) ውል ለማዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፡፡

ለ) በቂ የሆነ እርግጠኝነት ያለው የሚቻልና ህጋዊ የሆነ ጉዳይ

ሐ) ይኸውም የውል አፃፃፍ ፎርም (ዓይነት) በሕግ የታዘዘ ሆኖ እንደ ትዕዛዙ ባይፈፀም ፈራሽነትን የሚያስከትል ሲሆን አንድ ልዩ ፎርም…

ይህ አንቀፅ ውልን ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ሶስት ሁኔታዎች ብሎ ቢያስቀምጣቸውም በውስጣቸው ግን ከዚያ በላይ የሆኑ መሰረታዊ ነጥቦች እንዲሟሉ ይጠይቃሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በሀገራችን ግለሰቦች መብትና ግዴታቸውን በበቂ ሁኔታ ባለማወቃቸው ምክንያት አላስፈላጊ ወጪ፣ የንብረት ኪሣራ፣ ለሙስና በር ከፋች እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፡፡ በተለይ ከውል ጋር በተያያዘ ጉዳይ ህጋዊ መንገድን ከመከተል ይበልጥ ወደ አልሆነ አቅጣጫ ይጓዛሉ ያንን ለማስቀረት በውል ስምምነት ውስጥ መኖር ያለባቸውን ነገሮች በበቂ ሁኔታ ማወቅ ይገባዋል፡፡

አንቀጽ 1678 መኖር ይገባቸዋል ብሎ ከአስቀመጣቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ችሎታ ነው፡፡ አንድ ሰው ውልን ለመዋዋል ችሎታ አለው የሚባለው እድሜው ለዚሁ የደረሰ የሆነ እንደሆነ ብቻ ሲሆን ይህም እድሜ በሀገራችን ህግ 18 ዓመት የሞላው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ሁኔታ የፍትሐብሔር አንቀጽ 198 በግልፅ ያስረዳል፡፡ አንድን ሰው ችሎታውን ሊያሳጡ የሚችሉ ሁኔታዎች እድሜ፣ የአእምሮ ሁኔታ ወይም የዚሁ ሰው ላይ የደረሰው የፍርድ ቅጣት ሊሆኑ እንደሚችሉ አንቀፅ 192 ይገልፃል፡፡ ስለዚህ በዚህ አነቀፅ ውስጥ በተገለፀው በየትኛውም ሁኔታ ችሎታውን ያጣ ሰው ውል ቢፈፅም ውሉ ህጋዊ ውል ሆኖ አይቆጠርም ማለት ነው፡፡ ችሎታ ከእድሜ ጋር የተያያዘበት ዋናው ምክንያት እድሜያቸው 18 ዓመት ያልሞላቸው ግለሰቦች ከልጅነት አእምሮ ውጭ አርቀው ሊያስቡ አይችሉም፣ እንዲሁም በማህበራዊ ህይወት ያላቸው ልምድ እምብዛም በመሆኑ በቀላሉ ሊታለሉ ይችላሉ፤ በውሉም ከመጠቀም ይልቅ የሚያጡት ነገር ይበልጣል በሚል እሳቤ ነው፡፡ ሁለተኛው ሁኔታ በተመሳሳይ ወገኖች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር ነው፡፡ በተመሳሳይ ወገኖች መካከል የሚኖረው ስምምነት ከማናቸውም ተፅዕኖ በፀዳ መልኩ ተፈፀመ የሚባለው ውል ሰጪም ሆነ ውል ተቀባይ ወደውና ፈቅደው ሲስማሙ ብቻ ነው፡፡ አንዳንዴ ተዋዋዮች አንድን ግለሰብ ጫና ውስጥ በመክተት እነሱ በፈለጉት መልኩ የውሉን ስምምነት እንዲፈርም ያደርጉታል፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የተፈረመ ውል ምንም እንኳ ግለሰቡ ፊርማውን በወረቀት ላይ ቢያሰፍርም፣ ወይም መስማማቱን ሊያስረዱ የሚችሉ ሌሎች ሁኔታዎች ቢቀመጡም ግለሰቡ ውሉን የፈረመው ወይንም የተስማማው በተፅዕኖ እና በነፃ ፍላጐቱ እንዳልሆነ ማስረዳት ከቻለ የፈረመው ውል ወይም ስምምነቱ ውድቅ ይሆናል፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር አብዛኛውን ጊዜ ከውል ጋር በተያያዘ በተግባር የሚታይ ችግር ነው፡፡ በሶስተኛ የተቀመጠው ሌላው መስፈርት በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገው ውል ህጋዊ መሆኑ ነው፡፡ በምንም ዓይነት መልኩ ህገ-ወጥ የሆነ ስምምነት እንደ ውል አይቆጠርም፣ ውጤትም አይኖረውም፡፡ አንድን ግለሰብ ለማጥቃት በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት፣ ስርቆት ለመፈፀም የሚደረግ ውል፣ ሰውን ለመግደል በሰዎች መካከል የተደረገ ውልና የመሳሰሉት ህገ-ወጥ ስምምነቶች ስለሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ መሰረት ህጋዊ ውል መሆን አይችሉም፡፡ አራተኛው ሁኔታ በውሉ ውስጥ ለተዋዋይ ወገኖች የሚሰጠው መብትና ግዴታ በማያሻማ መልኩ መቀመጥ አለበት፡፡ ለምሳሌ ‹‹አየለ ለደረሰ ስኳር ይሰጠዋል፡፡ ደረሰ በምላሹ 10000 ሺህ ብር ይከፍለዋል›› በሚለው ስምምነት ውስጥ እንበልና ሌሎች የውል ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተዋል ብንል አየለ ለደረሰ የሚሰጠው ስኳር ምን ያህል እንደሆነ በግልፅ ስላልተቀመጠ አየለን ማስገደድ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ይህ ስምምነት ‹‹ግልፅነት ይጐድለዋል›› በሚል ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በመጨረሻ በሁለቱ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት አስፈላጊ የህግ ፎርማሊቲ የግድ የሚለው ከሆነ መሟላት አለበት፡፡ በሀገራችን ብዙውን ጊዜ በውልና ማስረጃ ወኪልነት የሚደረጉ ውሎች እንዲሁም ከመንግስት ጋር በተለያዩ ደረጃዎች የሚፈፀሙ ስምምነቶች ፎርማሊቲ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ውል ስንፈፅም እነዚህ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በደንብ እናስተውል፡፡

ቸር እንሰንብት

---

# ሚስማሩን የሳተው … ከገፅ 6 የዞረ

“ያለ ምንጭ ማቅረብ ምሁራዊ አቀራረብ አይደለም” ስለዚህ ያባባሌን እውነትነት በማስረጃ ለማስደገፍ ነው ሲሉም ብሩምፊት እና ካርተር (ቅጥያ ስሞቹ ለጋዜጣ አላስፈላጊ ስለሆኑ ቆርጫቸዋለሁ) የተባሉ ሁለት ‘የመስኩ ሊቃውንት’ በ1986 (በፈረንጅ ይሁን በሀበሻ አቆጣጠር አልተጠቀሰም ግምቴ በመራኝ በፈረንጅ አቆጣጠር ሳሰላው ከ25 ዓመት በፊት) የፃፉትን በማስረጃነት እንዲህ ሲሉ ያስቀምጡታል፤

“አንድን ሀሳብ ለመሞገት፤‘አንባቢው ሀሳቤን በትክክል እንዲረዳ የሚያደርጉ ማጠናከሪያዎች የትኞቹ ናቸው?’ የሚለውን ጥያቄ መመለስ እንዳለባቸው የመስኩ ሊቃውንት ያስገነዝባሉ፡፡”

እስቲ እግዚአብሄር ያሳያችሁ አሁን ለዚህ ዋቤ መጥቀስ ትልቅ እና አስፈላጊ ነገር ሆኖ ነው ከ25 ዓመት በፊት ከተፃፈ መፅሐፍ ጥቅስ ቢጤ ተመዞ የሚቀርብልን? ለዚያውም አንብቡ፤ ተመራመሩ፤ፁሑፋችሁን ባግባቡ አደራጁ፤ ምንጭ ጥቀሱ… ከሚል ደርዘን ምክር ጋር፡፡ ብሩምፊት እና ካርተር በዶ/ር በድሉ በኩል ባይነገሩን የማንደርስበት ጥልቅ ሚስጢር መሆኑ ይሆን? ይሄንን ካሉ ደግሞ በነካ እጃቸው ገፁን እና ከየትኛው ቤተ-መፅሐፍት እንደምናገኘው ጭምር አብረው ቢጠቅሱልን መልካም ነበር፡፡ በ1986 የተፃፈውን የትብለን እንፈልገዋለን? እንዴ አሁን እኮ 2012 አጋማሽ ላይ ነው ያለነው፡፡

እነዚህ ‘የመስኩ ሊቃውንት’ ግን ከ1986 በኋላ መፅሐፋቸውን ስንቴ አሻሽለውት ይሆን? ስንት ሌሎች መፅሐፍትስ ለተጠቀሰው መስክ አበርክተው ይሆን? ምንአልባት በድሉ እንደ እድል የ1986ቱን ህትመት ብቻ ይሆን ያገኙት? ይሁን የተገኘውን መጥቀስ ነው፡፡ ምን ይደረግ፡፡ ውጭ አገር ተምረን ብንመጣም የምንኖረው እዚችው ምስኪን አገር ነው እናም የተገኘውን መብላት እጣ ፋንታው ለሆነ ለዚህ ህዝብ የተገኘውን ምንጭ መጥቀስ መቸ ያንስበታል ብለው እስበው ከሆነ ነው የሚያንገበግበን፡፡ እንኳንም ካፍዎት አልወጣ፡
፡

“ኮሌጅ ውስጥ ቢሆን ኖሮ…የሚያባርር አፀያፊ ተግባር ይሆን ነበር የሰራኸው ስራ” ነበር ያሉት ፀሐፊውን? እውነት ብለዋል፡፡ ኮሌጅ ውስጥ ያረጁ ያፈጁ መፅሐፍትን በምንጭነት መጥቀስም እኮ ለዚያውም በዚህ ዘመን የሚያባርርም ባይሆን ያስወቅሳል፡፡ ቢያንስ ምንነካዎት ያስብላል፡፡ ግን እርስዎ ተማሪዎችዎን እድሜ ጠገብ መፅሐፍትን በምንጭነት በመጥቀሳቸው ስንቴ ወቅሰዋቸው ይሆን? መቼም በብዙ የዓለማችን ዩንቨርስቲዎች ዋቤ መፅሃፍትን ለማጣቀስ የህትመት ዘመናቸው እንደዋና ጉዳይ እንደሚነሳ ጠንቅቀው ያውቃሉ ብዬ እገምታለሁ፡፡ የህትመት ጊዜ ገደብም የሚጣልበት አጋጣሚ አለ፡፡

ለማጠቃለል በድሉ ፀሐፊነት ስነምግባር እንደሚያስፈልገው በማንኛውም ሚዲያ ላይ በሚነሱ ውይይቶች ውስጥ በቃላት አጠቃቀማችን ጥንቁቅ መሆን እንዳለብን ፤ ዝም ብሎ የጭቃ ጅራፍ እያነሱ መለጠፍ ተገቢ አለመሆኑን እና ሌሎች ያነሷቸው ተዛማጅ ጉዳዮች በአብዛኛው የምስማማባቸው ናቸው፡፡ ይህንን ለማስረዳት የሄዱበት መንገድ በብዙ መልኩ ወጥነት የጎደለው መሆኑ፤ በጋዜጣዋ በኩል ለመምከር እና ለማስተማር የሞከሩበት አካሄድ ፤የጠቃቀሷቸው ምሳሌዎች እና የደረሱባቸው ድምዳሜዎች የቃላት አጠቃቀማቸውን ጨምሮ ተገቢ እና የበሰሉ ናቸው ብዬ አላምንም፡፡ ለእኔ በአብዛኛው የበድሉ መዶሻ ሚስማሩን እየሳተ ሲንገዳገድ ነው የሚታየኝ፡፡

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን በጥቅል ፁሑፋቸውን ለመረዳት የሞከረ ጥንቁቅ አንባቢ ዋና ግባቸው በበዕውቀቱ ስዩም ላይ የሚወርደውን ‘ጅራፍ’ መመከት እንደሆነ የሚረዳ ይመስለኛል፡
፡ ዶ/ር በድሉ ወደዚህ ሙግት እንዴት መጡ? የሚለዉን ሌላ ሌላውን ነገር ቁፈራ ትተን ከዚህ ቀደም የፃፏትን አንብበን ወደዚህኛው ፁሑፋቸው ስንመለስ ዓላማው የበለጠ የሚገባን ይመስለኛል፡፡ በግልፅ ወግኖ መሟገት ክፋት ባይኖረውም፡፡ ከዚህ በመነሳትም እራሳቸው በፁሑፋቸው መግቢያ የጠቀሷት እኔም ከመሀል ላስረጅነት ያመጧኋትን መልካምሰው የተባሉት ፀሐፊ በዕውቀቱን የገለፁባት በድሉንም ቢሆን በተገቢው መንገድ የምትገልፅ ይመስለኛል እንዲህ ብናስተካክላት፡፡

‘በድሉ ዋቅጅራ የመልካምሰውን ሀሳብ ለመሞገት ተፈጥሯዊ አቋማቸውን ትተው አንድ እግራቸውን አላልተው አንድ እግራቸውን አጠንክረው በአንድ ጎናቸው በመቆም ጋሻቸውን ወድረዋል ለበዕውቀቱ ዘብ ለመቆም፡፡’

‹‹ስድአደግ ቃላት›› ተጠቅሜ ይሆን? ይቅርታ አብዝቼ ይሆን? ጨረስኩ…

---

# “የቃሊቲ ምስጢሮች” … ከገፅ 7 የዞረ

ለማለት የፈለገው ለራሱም እንኳ አልገባውም የምለው ለዚህ ነው፡፡ እኔ በአፅንኦት ያሠመርኩባቸውን ሀሳቦች ልብ በሉ! . . ግኝት ማለት ምንድነው? ብርሃኑ ሥለምን ግኝት ነው የሚያወራው? በፖለቲከኞቹ የተፃፈ ጉዳይስ በሌላ ሰው በሌላ ጊዜ አይፃፍም ወይም መፃፍ የለበትም ያለው ማነው? የአደባባይ ዕውቀት ሆኗል ማለትስ ምን ማለት ነው? እኛ አውቀናልና ሌላው ማወቅ የለበትም ማለት ነው?

እንዲህ አይነቱን አመለካከት ነው እኔ ከአናት መበላሸት ነው የምለው፡፡ ለዚህ አባባሌ አንድ አስረጅ ብቻ ልጥቀስ፡፡ የቃሊቲ ምስጢሮች መፅሐፍ ለአንባቢያን ከቀረበ በኋላ በርካታ አስተያየቶች በድምፅም በሞባይል ፅሁፍ መልዕክትም ተቀብያለሁ፡፡ አንዱ መልዕክት እንዲህ ይላል፡-

“ወሰን የቃሊቲ ምስጢሮችን አነበብኩት፡፡ አሹ! እንኳንም ታሠርክ! ለምን መሠለህ? ባትታሠር ኖሮ ይህንን የመሰለ ታሪክ ማን ይነግረን ነበር . . .
.”

ይህ የሞባይል ፅሑፍ መልዕክት የላከልኝ ሰው ነዋሪነቱ ሻሸመኔ ነው፡፡ በንግድ ሥራ ላይ ነው የተሰማራው፡፡ የሁለት ልጆች አባት ነው፡፡ በፅሑፍ መልዕክት ብቻ ስሜቱን ገልፆ አልወጣለትም፡፡ መልሶ ደወለልኝና አነጋገረኝ፡፡ የተነጋገርነውን እዚህ ላይ አልፅፈውም፡፡ በሞባይል ስልክ የላከልኝን የፅሁፍ መልእክት ግን ለማንም ማስነበብ እችላለሁ፡፡

እንዲህ ከሆነ ደግሞ የታሪክ ተመራማሪው ብርሃኑ ደቦጭ የተቃዋሚዎችን ማንነት ለማወቅ መታሰር ያስፈልጋል ወይ የሚለው አጉል አተካራ አስተያየቱን በሰጠኝ ሰው ሀሳብ ከሸፈ ማለት ነው፡
፡ ይህ ሰው ብርሃኑ እናውቀዋለን ያለውን ምስጢር አያውቅም ነበር ማለት ነው፡፡ እኛ ብቻ እናውቅልሀለን ብሎ ነገር አይሠራም ማለት ነው፡፡

የቃሊቲ ምስጢሮች መፅሐፍ የሻሸመኔውን አንባቢ መሠል ቅን ኢትዮጵያውያንን ዓይን ገልጧል ማለት ነው፡፡ ዓይኑን ያልገለጠ ወይም ገልጦ ማየት ያልፈለገ ደግሞ ምርጫው የራሱ ነው፡፡ የተጣመመውን ለማቅናት የህሊና ፈቃድ ያሻልና፡፡

ቢሆንም በስተመጨረሻ አንድ ነገር ልበል፡
፡ “የቃሊቲ ምስጢሮች” መፅሐፍ ዓላማውም ሆነ ዒላማው አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ እሱም ራሳችንን መመርመር፣ መፈተሽና ማየት አለብን የሚል ነው፡
፡ ራሳችንን ካላየን የሌላውን ጉድፍ ለማፅዳት የሞራል ብቃት ይጎድለናል ማለት ነው፡፡ ምነው ቢሉ ኢትዮጵያ የጋራ ቤታችን ናት፡፡ የጋራ ቤታችንን ችግር ለማፅዳት ደግሞ የየራሳችንን ጉድፍ አስቀድመን መንቀስ የግድ ይመስለኛል፡፡

ልክ እንደዚያው ሁሉ ካለአድልዎና ካለመወገን መፃፍና እውነቱን ገላልጦ ማሳየት ይመስለኛል የጋዜጠኞችና የታሪክ ተመራማሪዎች ተግባር፡፡ “የቃሊቲ ምስጢሮች”ን የፃፍኩት በዚህ የእውነት መሠረት ላይ ቆሜ ነው፡፡ እውነትን ቁልጭ አድርጌ ለማሣየት እንደታሪክ ተመራማሪው ብርሃኑ ደቦጭ “ትርክት›› እና ሌሎች ቃላትን በሚጠቀም የቃላት ጥርቅሞሽ ነገሮችን አላድበሰበስኩም፡፡ ቀለል ባሉ ቃላቶች፣ ሁሉም ሰው ሊረዳው በሚችለው መንገድ፣ ጥርት ባለ ቋንቋ ነው የፃፍኩት፡፡ ይኸው ነው፡፡ ከዚህ በላይ ማለት ጉንጭ ማልፋት ነው፡፡ አበቃሁ!!

---

# የእርዳታ ጥሪ



በፎቶው ላይ የምትመለከቱኝ ወ/ት ሶስና ዲልካሣ ሰው ጋር ተቀጥሬ የምሠራ ስሆን ከፍተኛ የልብ ህመም ላይ እገኛለሁ፡፡ በሀገር ውስጥ ባለ የህክምና ተቋማት በተደረገልኝ ህክምና መዳን ባለመቻሌ የጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ቦርዱ ወደ ውጪ ሀገር ሄጄ መታከም እንዳለብኝ ወስኗል፡፡ ይህንን ህክምና ለማድረግ 450000 (አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ደግሞ እኔም ሆንኩ ቤተሰቦቼ አቅም የለንም፡፡ በመሆኑም እናንተ ወገኖቼ እንድትረዱኝ ስል ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼን በማክበር እርዳታችሁን እጠይቃለሁ፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዳማ አባገዳ ቅርንጫፍ
የባንክ ቁጥር፡- 515501001830
ስልክ፡- 0911 70 96 97

# ኪነጥበብ

# ፔዳል ዴሞክራሲ 4



ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

የላም በረት!
አንዲት ሐገር ነበረች
እሺ...?...
ከአለም ቀድማ የነቃች
እሺ...?..
ስልጡንና ሐያል ነበረች
እሺ...?...
ስትኖር... ስትኖር... ስትኖር... ስትኖር...

ታላቂቷ ኢትዮጵያ እንደ ጅማሮዋ የእድገት ጎዳናዋ... ፈጣን እንዳይሆን አንዳንዴ አቀባዮች ሲንቀራፈፉ... ብዙ ጊዜ ተቀባዮች... ሲያንቀላፉ... ተፎካካሪዎቿ ከጀርባዋ ተነስተው የድል አክሊልን ከስልጣኔ ማማ ላይ ወጥተው ሲሸለሙ... እርሷ ግን የመሮጫው መሥመር ጠፍቷት... ብዙ መንገድ እየሰራች... የተሠራውን እየናደች... በአያቶቿ ፍጥነት እየኮራች... በመንገዳቸው ለመጓዝ... እየተፀየፈች የአባቶቿን-ጥበብ ያለምርምር ንቃ... እስካሁን... መንገድ ላይ ናት...መንገድ ላይ... ለምን???

በዱላ ቅብብል ጨዋታ... ሦስትም ይሁኑ ዐራት ሰዎች ወደ መሮጫው ጎዳና ገብተው ከተሠለፉ በኋላ ዋነኛ ዐላማቸው ዱላውን ተቀባብለው ማሸነፍ ዐልያም ውድድሩን መፈፀም ነው... አብዛኞቹ ሰልፈኞች እነኚህን ሁለት ነገሮች... የተረዱ ናቸው...

* ዱላውን የያዘው ለማን እንደሚያቀብል ያውቃል።...

* ዱላውን የሚጠብቀውም ከማን እንደሚቀበል ያውቃል።

ኢትዮጵያን ወክለው በውድድሩ መስመር የተሰለፉት አብዛኞቹ ግን ለማን... እንደሚሮጡ... ለምን እንደሚሮጡ... የያዙትን ዱላ (በትረ ስልጣን)... ለማን እንደሚያቀብሉ አያውቁትም... (ቢያውቁም አያደርጉትም)። ይህም እስከዛሬ ድረስ እንደ-ሠንደቅ ዐላማዋ ቀለም ደምቆ የሚታይ... እውነት ነው... ስለዚህ ርስ በርስ አልተዋወቁምና ማሸ(ቸ)ነፍ አልተቻላቸውም... ይህም ዐንዱ የኢትዮጵያ መንገድ... ስሪት ነው...

ይህም የትውልድን ክፍተት እየፈጠረ ‹‹አሮጌው በልጁ ወጣትነት... ወጣቱ ደግሞ ተንኮልና መጠላለፍን ዕውቀት ባደረገች በአባቱ ሸበት እየተቀናኑ እና እየተናናቁ ዱላቸውን የትም ጥለው ዘመናቸውን ያሸልቡባት ዘንድ ተገደዋል።... የተሰራው ሲናቅ... አዲስ ሊገነባ... የተሞከረው ሲተች... የተቸው ከተሞከረው በላይ ሲሰንፍ (ሲሳሳት) የብስክሌቱ... መጓጓዣ መንገድ በሁለት ጎማ ወደ ስልሳ አቅጣጫዎች መበታተን ሆኗል... ዕጣ ፈንታው...

ዱላው የትም ይወድቅ... ነበረ።...

እናም?...

እንዴት እንደተጣለ ያልታወቀውን... መንገድ የወደቀውን ዱላ... ድንገተኛ... መንገደኛ... ያነሣዋል።.... እርሱም እርሱን-ብቻ ደስ ባሰኘው መንገድ ሩጫውን ይጀምራል (ይቀጥላል ዐላልኩም)... አንዱ ጎዳና ላይ የርሱን ዐይነት ማልያ የለበሰው ጠልፎ እስኪነጥቀው ድረስ...(እስኪቀበለው ዐላልኩም)... ይህ የመጠላለፍ የሩጫ-ዘዬ የጠይም ሕዝብ ጎዳና ሕግ... ይባላል... የዱላ ቅብብልን ስነ-ስርዓት ያልጠበቀ... ሕግ...

‹‹ዱላው ይረሳ ነበረ››...

ከአክሱም ስልጣኔ... እስከ ላሊበላ... ከዛግዌ... እስከ ጎንደር... ከፍታ ድረስ... የስንት መቶ ዓመታቶች ክፍተት አለ?... የስንት ጥበባት ክፍተት አለ... የስንት ትውልድስ?...

የጠይም ሕዝብ ጎዳና ዱላን በመቀበል ላይ የተመሰረተ አልነበረም፤ ይልቁንም በመነጣጠቅ ላይ እንጂ።... የጀመሩትን መንገድ እንዳይፈፅሙ በያዙት ዱላ ዐናታቸውን ተመተው... የትም የወደቁ... የአቢሲኒያ መንገደኞች ናቸው።... በነጠቁት ዱላ... የተመቱም እንዲሁ... (የሞትንም እኛ... ያለንም እኛ... የምንገድልም... እኛ(ን))

በተንኮል የተያዘ ዱላ ፍፃሜው ምን እንደሆነ ስለማይታወቅ... ሌላኛውም መንገዱን የሚያንፀው በተንኮል ለተንኮል ነበር... የዚያኛው ጎዳና እንዳይጥለው አስቀድሞ መጥለፍያውን ማበጀት... ስለዚህም ሁሉም የገነቡት የብስክሌቱ... መንገድ... ቁልቁለት... ነበረ... ቁልቁለት...

ስለዚህም...

አክሱም ላይ ወደ ሰማይ ከሚጣቀሰው ሃውልት በላይ... ወሎ ውስጥ መሠረቱን ዐናት... ዐናቱን... መሰረት... አድርጎ የጀመረው የላሊበላ ቤተ-መቅደስ የኢትዮጵያን ዕድገትና የሕዝቧን ማንነት በጉልህ የፃፈ ይመስላል...

የአክሱም ሀውልት የነበረችውን ኢትዮጵያ እንጂ መጪዋን ኢትዮጵያ ዐይጠቁምም... የላሊበላ መቅደስ ግን የነበረችውንና የምትመጣውን ኢትዮጵያ ማንነት... ድንጋዩን ፊደል አድርጎ ፅፏል... የነበረችውን... በቁሙ (በመቅደሱ ውበትና ጥበብ)... የምትመጣውን ደግሞ... በህንፃው አንድምታ/ትርጓሜ/ ህንፃው የተሰራው... ከዐናቱ ነበር... ከጉልላቱ ወደ መሠረቱ... ከላይ ወደ ታች። ቁልቁል የወረዱ... ይህ የላሊበላ ቤተ-መቅደስ ህንፃ አሰራር... የአሁኒቷን ኢትዮጵያ... የሚገልፅ ትርጓሜ አለው... ከመሠረቷ ተገንጥላ... ሠርክ አዲስ እየሆነች ሁሌም...ከዜሮ የምትጀምረዋን ኢትዮጵያ... ሃላፊው ከመጭው... መጪው ከሂያጁ የማይተዋወቁበትን... ቢተዋወቁም የሚናናቁበትን... አባት... ለልጁ... ግድ የለሽ የሆነባትን ኢትዮጵያ...

በመዳፏ ላይ ያለውን ፀጋ ጨብጣ እንደያዘች... የውጪውን ስትማትር የራሷን የዘነጋች ኢትዮጵያ... በዐይኖቿ ከዐድማስ ባሻገር ያለውን እንጂ የራሷን ማጀት ማስተዋል አልተቻላትምና እንዲህ ተቀኙባት... ሊቃውንት...

ቀራንብት ኃቤሁ እንዘ ቅሩባን
ቀራንብተ ኢይኔድር ዐይን።...

ቅንድብ ካዐይናችን ፊት ካጠገቡ ሣለ
ዐይናችን ቅንድቡን ከቶ መች ልብ ዐለ።...

....እንግዲህ ዱላውን በያዘውና ዱላውን በሚቀበለው መካከል ያለው ቅርበት የዐይንና የቅንድብን ያህል ነው። ...ነገር ግን በዱላ ቅብብል ጨዋታ ተቀባይ ዱላውን በእጁ ካላስገባ... የሩጫው አባል አይሆንምና... ተቀባይም እንዳፈጠጠ... አቀባይም እንደጨበጠ በርካታ... የኢትዮጵያ ዘመንና... ጎዳናዎች ተሥተዋል።... ይህም የትውልድንና የጥበብን ክፍተት እየፈጠረ... በአባትና በልጅ መካከል ፍቅር... ሣይሆን ባላንጣነት... ጥበብ ሣይሆን ተንኮል... የመንገዱን መሠረት ... ከድነውታል።...

መንገዱ ፈታኝ ቢሆንም... ጥርጊያው እስኪቃና... እውነተኛው... የኢትዮጵያ መሲህ በኢትዮጵያ... ለኢትዮጵያ እስኪሆን ድረስ ተራራው ዝቅ... እስኪል... እሾሁ እስኪነቀል ድረስ... የኢትዮጵያ ልጆች... በዚህ መንገድ ላይ... ከዚህ ወደዚያ... ከዚያም ወደዚህ ይመላለሱ ዘንድ... መንገዱ እንዲህ ተበጅቷል።

ለኛ ሐገር... ብስክሌት... ከዳገትና ከቁልቁለት በቀር... ለጥ ያለ የተደመደመ... መንገድ የለም... ቁልቁለት የምትጋለብ... ብስክሌት ወደ ጎን ካዘመመች... ዳገት የምትወጣውም... ጉልበት ከጨረሰች... ጎማዋን ከበላች... መንገዱ ተመልሶ ወደ ኋላ።... መንገዱ ሥሪቱ ለደካማ ነውና...

ጎዳናው

ሥለ ብስክሌት ምንነት አንድምታና ስለብይ ጉድጓድ- ሕይወታዊ ትርጓሜ በመጠኑ ከተባለ አሁን ደግሞ ስለብስክሌቱ መንገድ ስለጎዳናው እነሆ...

መንገዱ በየጊዜው እየተሠራ በየጊዜው ሲፈርስ ኖሯል። አንደኛው የጠረገውን ጎዳና አንደኛው እየናደው... ሌላኛው የናደውን መጪው እያፈረሰው ተንዶ በተከመረው ኮረት ስር በፍርስራሹ መሃል ለምን ፈረሰ? ብሎ የጠየቀው... ፍርስራሹ ስር እየተደበቀ... የተደበቀው ሌላ አዲስ መንገድ እየቀየሰ ሥነ-ስርዓት እንደሌለው ‹የዱላ ቅብብል› ጨዋታ መነሻው እንጂ መድረሻውና ማድረሻው ስፍራ ሣይታወቅ በየትም አቅጣጫ ጎዳናው ተሠራ።

በዱላ ቅብብል ጨዋታ የመጀመርያውን ሠው ፍጥነት ያህል... ተቀባዩ ከሌለው ወይም ለሁለተኛው ተቀባይ የመጀመሪያው ሯጭ ዘግይቶ ካቀበለው (ምናልባት ሁለተኛው ከቀዳሚው የላቀ ፍጥነት ከሌለው በስተቀር)... ማሸነፍ... ድል ማድረግና የሜዳልያ ሽልማት ተረት እንደሚሆን... መሠረቱ ‹እውነት› የነበረው የአቢሲኒያ... መንገድ በተረት ተገነባ....

ተረት? ተረት?...

## ጥንቃቄና ትኩረት ... ከገፅ 7 የዞረ

... ከገፅ 7 የዞረ

በግርጌ ማጣቀሻ እያስደገፉ ቢጽፉ/ annotate (ይሄ ከፍተኛ ጥናትንና ዝግጅትን ይጠይቃል) የህዝባዊ ታሪክ ጸሐፊያንን ደረጃና አስተዋጽኦ ከፍታ እንድንመሰክር የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዲህ ዓይነት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያነቃቃ ይሆን ነበር። በሰነዶቹ በቃል መረጃዎቹና እዚህ ላይ አስተያየት እንደሰጠሁት በግርጌ ማስታወሻው የተጠቀሱ ስሞችን ሁሉ ጨምረው መጠቁም ቢያዘጋጁ ከትችት በዳኑ ነበር።

ሌላው ሳይነሳ የማይቀረው ጥያቄ ደግሞ ሰነዶቹ የተገኙበት ቦታና ሁኔታ አለመገለጹ ነው። ይህ ዓይነት አቀራረብም በተለይ አዘጋጁ ከዋናው ቅጂ ገልብጠው በታይፕ ያስመቷቸውንና አውቀውም ይሁን ሳያውቁ በመጽሐፉ እንዳይካተቱ የዘለሏቸውንና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ለማጣራት አስቸጋሪ ያደርገዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከዕለቱ መጽሐፍ ክበብ ወጥተን ሰፋ አድርገን ስንነጋገር የቤተመዛግብት አጠባበቃችንና አጠቃቀማችንን እንድናስብ ማድረጉ አይቀርም።

### የቤተመዛግብት አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት

አገሪቱ እንደረዥም የታሪክ ባለቤትነቷ የተደራጀ የቤተመዛግብት አያያዝ ሥርዓት የላትም። የቆየውን የታሪካችን ሂደት ትተን እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰነዶች በአገሪቱ የመንግሥት ለውጦች ሲደረጉ የገጠሟቸው ዕጣ ፈንታ አሳዛኝ ስለመሆኑ የደርጉንና የኢህአዴግን ወደሥልጣን የመጡበት ዘመን ክስተት ማሰብ ይበቃል። በእንዲህ ዓይነቶቹ ጊዜ ባለማወቅ የባከኑ ሰነዶች እና ሆን ተብሎ የተሰወሩ ማስረጃዎች ምን ያህል እንደሆኑ አይታወቅም። ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ በማ/ጥ/መ በተዘጋጀውና ‹‹Development and Public Access to Information in Ethiopia›› በሚል ርዕስ ስር በታተመው ‹‹Archive and Historical Research›› የተሰኘ መጣጥፋቸው ስጋቱ የምር እንደሆነ መጥቀሳቸው አሳማኝ ነው። በሰላሙም ጊዜ ቢሆን የቆዩ/‹‹ሙት ፋይሎች›› የሚቀመጡበት ሁኔታም አገሪቱን ‹‹ህልም የለሽ›› የሚያሰኛት ነው። በአንድ ወቅት በአገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ቤተመዛግብት ያሉበት ሁኔታ መመርመሩ በቅርቡ ለተቋቋመው ብሔራዊ ቤተመዛግብት ድርጅት መጠናከር አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይገመታል። ብዙ ሳንርቅ በአዲስአበባችን በአራዳ ሕንጻ ስር የሚገኘው የማዘጋጃ ቤቱ የቆዩ ሰነዶች ማከማቻ ከላይ በ ተከፈቱ ቢራቤቶች የሽንት ቤት ፍሳሽ መበላሸታቸው አሳዛኝ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ቤተመዛግብት ገብቶ ለመጠቀም ያሉ ማነቆዎች ሊታገሱት ከሚችሉት በላይ መሆኑ ነው። አሁንም ለሕዝብ ክፍት ያልሆኑ ብዙ ሰነዶች ያሉባቸው ቦታዎች አሉን። ብዙ ጊዜም በልዩ ዝምድናና የባለሥልጣኖች ፈቃድ ብቻ የሚደርሱባቸው ወይም የሚፈቀድላቸው መኖራቸውም ያበሳጫል። በታወቀ ሥርዓት አጥኚዎች/ተመራማሪዎችና ሌሎች ዜጎች እኩል የመጠቀም መብታቸው ሊረጋገጥ ይገባል። ያኔ በልዩ ገጠመኝ መረጃዎቹን ገልብጦ ገንዘብ ሊሠራ የሚወደውም ሆነ ያለውን የዕውቀት ክፍተት ለማጥበብ የሚዳክረው ፍትሐዊና ተጠያቂነት ያለበት አጠቃቀም ሥርዓት እኩል ተጠቃሚዎች ይሆናሉ።

### የፎቶና የቃል መረጃ

በአገራችን የሕትመት ደረጃ የቆዩና በተለይ ከጋዜጣ የሚወሰዱ ምስሎችን ጥራት ለመጠበቅ አልተቻለም። በዚህ ረገድ ይህም መጽሐፍ የችግሩ ሰለባ መሆኑን ከመጥቀስ ያለፈ ማለት አልችልም። ይሁን እንጂ 112 ታሪካዊ ፎቶ እንደያዘ አዘጋጁ በመሰከሩለት መጽሐፍ ፎቶዎቹ ስለተካተቱበት ሁኔታ አስተያየት መስጠት ግድ ይላል። ንጉሡ ከአስራአምስት በላይ ፎቶ/ምስል አላቸው። ብ/ጀ መንግሥቱ 5፣ አቶ ግርማሜ 4፣ ሌ/ኮ ወርቅነህ 3 ወዘተ። የዚህ ድግግሞሽን አስፈላጊነት በተለይ የጉርዶቹ ለማሳመን ይከብዳል። ነገረ ጉዳዩ የጥቂት ቀናት ክስተት መሆኑ ሲታሰብማ ከገጽ ማብዛት ጋር ወይም መካሪ ማጣት ጋር ይያያዛል። በድግግሞሽ ለሚፈጠር ችግር አንዱ ማሳያ እስከሦስት ጊዜ ድረስ ፎቷቸው የተካተተላቸው ሻለቃ ተፈራ በላይ ስማቸው ተገልብጦ መጻፉ ነው። ፎቶዎቹ ከመደጋገማቸው ባሻገር በዘፈቀደ መቀመጣቸውም አሳማኝ አይደለም። በገጽ 138 አንድ የምድርጦር ተዋጊ መሐንዲስ አዛዥ ለምድር ጦሩ ጠቅላይ አዛዥ የጻፉት ደብዳቤ ስር የተካተቱት ሁለት ምስሎች ለእንዲህ ዓይነቶቹ ጥሩ ማሳያ ይሆናሉ። በምስክርነት፣ በክስ ሂደት ዘገባና በተለያዩ የደብዳቤዎች ሰነዶች መሃል የተዶሉት ፎቶዎችም በወጡ/ኦሪጂናል መረጃዎች የሌሉ በመሆናቸው እንዲህ ዓይነት አቀራረብ የተገቢነት ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። አዘጋጁ ከጋዜጣዎች ላይ ስለ ሙከራው የተዘገቡ ዜናዎችን በአንድ ምዕራፍ ማስቀመጣቸው ተገቢ ሲሆን በመሃል ያስገቧቸው የንጉሡ የተለያዩ ምስሎች ግን በጋዜጦቹ ላይ የወጡ ይሁኑ አይሁኑ የሚገልጽ ነገር የለም።

ብዙ ሰነዶችን የያዘው ይህ መጽሐፍ በፊት ለፊት ሽፋኑ በያዘው ምስል ስር የተጻፈው አልጋ ወራሹ ንጉሠ ነገሥቱ ስር በግንባራቸው ተደፍተው ‹‹ምህረት እጠይቃለሁ›› እንዳሉ የተጠቀሰው ንግግር በመጽሐፉ ዝርዝር ይሄን ሲሉ ማን እንዳደመጣቸው እንዴትስ በሌሎች ዘንድ እንደተሰማ ባለመገለጹ ዋንኛው ዓላማው ማስረጃ ማቅረብ ለሆነለት መጽሐፍ የሚመጥን የሽፋን ዝርዝር ነው ለማለት እቸገራለሁ።

ሌላው በመጽሐፉ የተካተተው አንደኛ ደረጃ መረጃ የተሳታፊዎች የቃል መረጃ ነው። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ ናቸው። የእርሳቸው ሙሉ ቃል ከገጽ 190-196 ከሌላ አንድ ሰነድ ጋር ራሱን ችሎ አንድ ምዕራፍ ተሰኝቶ ተካቷል። የቃል መረጃው ከሰነዱ ጋር በቀጥታ የሚያገናኘው ነገር የለም። አረ እንደውም ፕሬዝዳንቱ በመፈንቅለ መንግሥቱ ከነበራቸው ሚና አኳያ ቃለመጠይቃቸው ይሄን ያህል ለአዘጋጁ አንገብጋቢ መሆኑም ግር ያሰኛል። ይልቅስ ፕሬዚዳንቱ ስለመጽሐፉ ሰጡ የተባለው አስተያየት ተስፋፍቶ በቀዳሚ ቃልነት ቢደረዝ ዋጋ ይኖረው ነበር።

### የመጽሐፉ ዋና ፋይዳ

ከላይ እንደጠቀስሁት የገድለ መፈንቅለ መንግሥት ዋና ዋጋ ሰነዶችን ማቅረቡ ነው። ሰነዶቹ የምርመራ ሪፖርት፣ የፍርድ ውሳኔ፣ የትዕዛዝ ደብዳቤና የአፈጻጸም ሪፖርት ሲሆኑ ስለክስተቱ በቅርብ ጊዜ የተሰበሰቡ የምስክርነቶች ቃልም ተካቶበታል። ስለመፈንቅለ መንግሥቱ የተጻፉትና ከላይ የጠቀስኳቸው መጽሐፎችና መመረቂያ ጽሑፎች በክስተቱ ዙሪያ የተፈጠሩ በራሪ ጽሑፎችን፣ የክስ ሂደቶችን፣ የምስክሮችን ቃልና የተሳታፊ የቃል መረጃዎችን እንዲሁም በጣም አነስተኛ ቢሆንም በውጭ የሚገኙ ሰነዶችን ተጠቅመዋል። የታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ አዲሱ መጽሐፍ ዋጋ በተለይ ሌሎች ጸሐፊዎች የተጠቀሙበትን የነጀነራል መንግስቱን የፍርድ ሂደት ስሚ ሳይሆን፤ ጀኔራሉ ለወንጀል አጣሪ ኮሚቴ የሰጡትን ቃል መጠቀማቸውና በክስተቱ ከተሳተፉት የአክሻፊዎቹ ወገን የተመላለሱት ዘገባና ደብዳቤዎችን ኦሪጂናል ቅጂ ማቅረባቸው ነው። እነግሪንፊልድ በሥራዎቻቸው የውጭ እጅ አለበት ተብሎ በውጭ ጋዜጦች መጻፉን ለመቀበል እንደተቸገሩ ሁሉ፤ በዚህ መጽሐፍ እንደተካተተው ለወንጀል አጣሪ ኮሚቴ የተሰጠውም ቃል ሆነ ሌሎች ጥቂት ደብዳቤዎች በሂደቱ የአሜሪካና የግብጹ መንግስታት ተሳትፎ እንደነበራቸው የሚከሱ በመሆናቸው ቢያንስ በመንግሥት በኩል ያለውን ዕምነት በግልጽ የሚያስቀምጡ ይሆናሉ።

### መጽሐፉ እንደመጽሐፍ ሲታይ

መቼም ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ እስካሁን ሦስት መጽሐፎች ጽፈውልናል። ወደፊት የሚታተሙ ሰባት መጽሐፎችም እንዳዘጋጁ ገልጸውልናል። እኛም በጉጉት እንጠብቃለን። ይሁን እንጂ እስከአሁን ያላቸውን ልምድ እንኳን የሚመጥን ጥረት በዚህኛው መጽሐፍ አላሳዩንም። በተለይ ‹‹አይ ምዕዋ›› ላይ ያየነውን ጥንቃቄ በፍጹም አጥተናል። መጽሐፍ ማለት ደራሲው ያገኘውን ሁሉ በዘፈቀደ የሚጽፍበት እንዳልሆነ መናገር አንባቢዬንም ሆነ የዚህ አስተያየቴ መነሻ የሆነኝን መጽሐፍ አዘጋጅ መናቅ ይሆንብኛል። ልረዳው በማልችለው ሁኔታ ግን ከመጽሐፉ የመጀመሪያው የውስጥ ገጽ ጀምሮ አዘጋጁ ‹‹ሲዘባርቁ›› የሚያሰኝ ሁኔታ መመልከቴ ጥቂት ነገር ማለት እንዳለብኝ እንዲሰማኝ አስገድዶኛል። በመጽሐፉ የመጀመሪያው የውስጥ ገጽ ከውስጥ ገጽ ርዕስ ቀጥሎ የመጽሐፉ ዝግጅት የተጀመረበት፣ የተጠናቀቀበት፣ ለህትመት የበቃበት፣ የገጾቹ ብዛት፣ የሰነዶቹና የፎቶዎች ቁጥር የተዘረዘረበት መንገድ(I) መግቢያ ይሁን ምን ይሁን የማይታወቅ ነገር ስለመጽሐፉ የሚገልጽ ነገር ያትትና እንደገና በገጽ (X-XI) መግቢያ በሚል ርዕስ ስር ስለመጽሐፉ ዝግጅት አንዳንድ ነገሮችን ይጠቁማል። እነዚህን ገጾች በማገናኘት የተደጋገመውን በማውጣት ትርጉም ያለው መግቢያ ማድረግ ይቻል ነበር። በገጽXI ከመግቢያው ጋር አያይዘው ያስቀመጡት 14 ለሕይወት የሚጠቅሙ ምክር አዘል አባባሎችም ከመጽሐፉ ርዕስጉዳይ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። እንደገና በገጽ 233 ዜጎች በዚህ ዘመን ማድረግ አለባቸው ብለውየጠቀሷቸው አራት ሰፋፊ ነጥቦችንም ለምን እንዳካተቱት መናገር የሚችሉ አይመስለኝም። በነገራችን ላይ ምክሮቹ ትክክልና ተገቢ አይደሉም ለማለት ሳይሆን ጸሐፊው በአእምሯቸው የመጣውን ሁሉ ባነሱት ርዕሰ ጉዳይ ላይ እየለጠፉ የመጽሐፍ አካል ማድረግ እንደማይገባቸው ለመጠቆም ነው። በገጽ 234 እና 235 ስለአጼ ኃይለሥላሴ የተካተተው አንድ አንቀጽና ፎቶ ስለረዥሙ የክቡር ዘበኛ ወታደር ኡመር ናስር የሚያስረዱት ሁለት አንቀጾችና አንድ ፎቶ መጽሐፉ ተጠናቀቀ ተብሎ ዋቤ መጻሕፍት (ገጽ 232 ላይ) ከተጠቆሙ በኋላ በመሆኑ አዘጋጁን እጅግ እንዳያስወቅስ እሰጋለሁ።

እንግዲህ ከዝግጅቱ ክብደትና ቅለት ጋር በተያያዘ ከሚፈጠረው ወጭ ጋር ተገናዝቦ ስለመጽሐፍ ኢኮኖሚክስ መነጋገርም እንዳያመጣ ያሰጋል። ይህ አስተያቴ ግን በመጽሐፉ ውስጥ ለተካተቱት ሰነዶች ያለኝን ስስት በፍጹም ጥያቄ ውስጥ አያስገባም።

## የአቶ አሥራት ጣሴ ... ከገፅ 4 የዞረ

... ከገፅ 4 የዞረ

አሥራት ፍላጎትና ጭካኔ ከአንድነት የተባረሩት ብዙዎቹ ዛሬ በሕይወት ባልተገኙ ነበር።

ምርጫ ቦርድ ለጉባኤያችን በደብዳቤ ማረጋገጫ ሰጥቶናል

አቶ አስራት ይህን መጻፍ ለምን እንዳስፈለጋቸው አልገባኝም። ቢሆንም እንኳን ደስ አለዎት እላለሁ። ሁለት ሰዎች ፕሮግራምና ደንብ ስትለውጡ (ኢ/ር ግዛቸው ለሪፖርተር ጋዜጣ እንደገለጹት)፣ ያለ ምርጫ ዶ/ር ነጋሶንና አቶ ስዬን ሊቀመንበር ብላችሁ ስትሾሙ፣ በምክር ቤት የጸደቀን የሥነ-ሥርዓት መመሪያ አንቀጾች ስትቀይሩ ወዘተ አቤቱታ የቀረበለት ምርጫ ቦርድ ደንባችሁን አክብሩ ያለማለቱን ማስታወስ ያስፈልግ ይሆን? አሁን ሠማያዊ ፓርቲን የመሰረቱትን ወጣቶች ከዚህ በኋላ አንድነት ነን ስትሉ እንዳልሰማ ብሎ ለእነሱም፣ ለእናንተም፣ ለፖሊስና ለአቃቤ ሕግም ደብዳቤ ጽፎ ‹‹የገላገላችሁ›› ምርጫ ቦርድ መሆኑንስ ለምን ሳይጠቅሱ አለፉ?

**‹‹ኢ/ር ግዛቸው መመረጥ ያልፈለጉት ለወጣቶች ለመልቀቅ ብለው ነው፡-››** በማለት የገለጹትም ሀሰት ነው። እሳቸው በጉባኤው ላይ የተናገሩት በአመራርነት ለመቀጠል የሚያስችል ወኔ እንደሌላቸውና ተተኪ ማፍራት ያልተቻለው አመራሩ ውስጥ ባለ ሽኩቻ መሆኑን ነው። ‹‹በቃኝ ወኔዬ ተሟጧል›› ብለው የተቀመጡት ሰው ላይ መንጠላጠል ለምን አስፈለገ? ኢ/ር ላቀው እና ስንት ወጣቶች ሥራ አስፈፃሚ ሆኑ? 40 ዓመትስ ወጣትነት ነው?

‹‹በሥልጣን የቆየሁት ምክር ቤቱ ስለፈለገኝ ነው፡-›› በማለትም አፍቅሮተ ወንበር ከተጠናወታቸው ፖለቲከኞች ስንሰማ የነበረውንም አስነብበውናል። ነገ ምን እንደሚሆን ባይታወቅም እስከ ዛሬ ግን የአቶ አስራት የሴራ ፖለቲካ ሰርቶላቸዋል። ሰኔ 11/2000 ዓ.ም. የተመሰረተው አንድነት ዛሬ የለም። ፕሮግራምና ደንቡ ተለውጦ፣ ጠንካራ አባላቱ ተባረው፣ የተለየ ሀሳብ የማይደመጥበት፣ ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት በተግባር የማይታይበት ፓርቲ ሆኗል። ሁሉንም ‹‹በጥበብ›› ሸኝተው አዛዥ ናዛዥ ሆነዋል።የአቶ አስራትን ሴራ በሚያሳይ አንድ ማስረጃ ፅሁፌን ላብቃ።

ውይይት ተጠልፎና ተፈርቶ ችግሮች እየተባባሱ ሲሄዱ አንድነት ውስጥ በአቀራራቢነትና በሽማግሌነት የሚታወቁትና ‹‹ፕ/ር ኤፍሬም›› የሚል ቅጽል ስም የወጣላቸው አቶ ይልማ ይፍሩ፣ ከአመራሮቹ ጋር በመነጋገር መጋቢት 8/2001 ዓ.ም. የውይይት መድረክ አመቻቹ። ሰብሳቢና ተሰብሳቢ አዳራሽ ገብተው ውይይቱ ሊጀመር ሲል አቶ አስራት ጣሴ አንዳንድ አባላትን እየጠቆሙ ‹‹ስብሰባው የማይመለከታቸው እንዴት ሊገኙ ቻሉ?›› በማለት ጠየቁ። አባላቱም ማን እንደጠራቸው ተናገሩ። ጠሩ የተባሉት ደግሞ አቶ አስራት ጥሩ ብለውን ነው በስልክ የጠራናቸው አሉ። አቶ አስራትም በዚህ ግርግር አስነስተው በለመዱት ‹‹ጥበብ›› (ሴራ) ውይይቱን ሳይጀመር በተኑት። በሌላ ጊዜ እንዲቀጥል ጥረት ሲደረግም በአውራምባ ጋዜጣ አማካኝነት ከማንም ጋር አንነጋገርም፤ ፖለቲካዊ ርምጃ እንወስዳለን አሉ። የዋና ጸሐፊነት ሥልጣናቸውን ተጠቅመውም የቻሉትን ርምጃ ወሰዱ። ዛሬ ደግሞ የሰሩት ሴራ እያባነናቸው በሃያ አመት ትውውቃችን ሁለተኛ በሆነው የጋዜጣ ጽሑፋቸው ራሳቸውን አጋለጡ። አዎ በእውነት ላይ ሸፍጦ እስከ መጨረሻ መዝለቅ አይቻልም።

# ረመዷንን ጠርጥሮ - ምርጫን በጓሮ



**ሁሴን ከድር**
**የቀድሞ የጦቢያ መፅሔት ጋዜጠኛ**

ረመዷን በአረብኛው የወራት አቆጣጠር (በሒጅሪያ) ዘጠነኛው ወር ላይ የሚገኝ የወር ስያሜ ነው ብሎም የፆም ወር። ረመዷን በእስልምና ብዙ ኹነቶች እንደተከናወነበት ይነገራል። ከብዙ በጥቂቱ ቁርአን የወረደበት የመጀመሪያው የበድር ጦርነት (ሙስሊሞች ከጣኦት አምላኪያን ጋር የተዋጉበት) የተካሄደበት በወሩ ውስጥ አንዲት የተከበረች ሌሊት ያለችበትና ሌላም ሌላም።

ረመዷን ሲመጣ በርካታ ሕዝብ ወደ መስጅዶች ይተማል። ለወትሮው በየቤቱ በየሥራው ቦታ ይሰግድ የነበረ ምዕመን በረመዷን በመስጅዶች የሶላት ወቅቶችን ማሳለፍ ይፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች ከየመ/ቤታቸው የዓመት እረፍት በመጠየቅ ጾሙን በሥርዓቱ ለማሳለፍ መስጅድ ይውላሉ። ከእህል ውሃ የራቀ ነፍሱ ትደክማለችና ለመንፈሳዊነት ስብር ትላለች።

መስጅድ የጸሎት ሥፍራ ብቻ አይደለም የእስልምና ሃይማኖታዊ እውቀቶች 80 በመቶ የሚሰጡት መስጅድ ውስጥ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። መስጅድ የእውቀት ማዕከል፣ የሥነ-ምግባር ማነጨያ ሥፍራ፣ የትውልድ ማፍሪያ፣ የመንፈሳዊ እምነት ማጐልበቻ፣ የአለማዊ ሕይወት ሥርዓት ማነጨያም ነው። ከሕልፈተ ሕይወት በኋላ ለሟች ፍትሐተ ጸሎት ማከናወኛም ሥፍራ ነው። ማንኛውም ሙስሊም ሟች በመስጅድ ሳይሰገድበት ወደ መቃብሩ አይወሰድም። በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን መስጅድ የጦርነት እቅድ መንደፊያ ሥፍራ፣ የሐገር ጉዳይ መወያያ አዳራሽ (ዛሬ ፓርላማ እንደምንለው) ሁሉ ነበር። አንዳንድ ሰዎች መስጅድን የጋብቻ ሥፍራም ያደርጉታል፤ ይሄ ሁሉ መሆኑ በእስልምና ስህተት አይደለም።

መስጅድ የመወያያ፣ ሃሳብ የመለዋወጫ፣ የመመካከሪያ መድረክ የመሆኑን ያህል የሙስሊሞች መሪ መምረጫም ሥፍራ ነው። ከነቢዩ ሙሐመድ ሕልፈት በኋላ በትረ መንግሥቱን የጨበጡት አቡበከር፣ ዑመር፣ ዑስማንና ዐሊ መስጅድ ውስጥ በተደረገ የምዕመናን ምርጫ ነው የተመረጡት። በአጠቃላይ የሙስሊም መሪዎች የሚመረጡት ባላቸው የሃይማኖታዊ ዕውቀት ደረጃ የተለያዩ የሰው ልጅ አስተሳሰቦችን አቻችሎ የመምራት ብቃት፣ ጥንካሬና የአመራር ብቃት መስጅድ ውስጥ በሕዝብ ሲታመንባቸው ነው። ማንኛውም የሙስሊም መሪ በጐሳ፣ በዘር፣ በሃብት መጠን መብለጥ ወይም በአንዳች ሕሊናን በሚጐረብጥ ከእውቀትና ችሎታ ውጪ ያለ የንቅዘት ምርጫ አይመረጥም። ይህ የኢስላም ሥርዓትና ደንብ ነው።

### ምርጫ በጓሮ

"በሃይማኖት ጉዳይ እጅህን አታስገባ ሲል ሕገ-መንግሥቱ ከልክሎኛል" እያለ በየአደባባዩ የሚፎክረው መንግሥት በእስልምና ጉዳይ እጅና እግሩን አንከርፍፎ ማስገባቱን በማን አለብኝነት እያሳየ ነው። ከሰሞኑ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ መሪዎቼን የመምረጥ መብት ይኑረኝ በሚል ያቀረበውን ጥያቄ መንግሥት መሪዎቹን ሊመረጥለት ሽቶ እንደሆን ባይታወቅም በይፋ በማይታወቅበት መልኩ በጓሮ በር በወረዳ ደረጃ አንዳንድ ሰዎች እየተጠሩ የምርጫ ድራማ እየተለማመዱ ነው የሚባል ወሬ፣ እየተሰማ ነው። ምን ያህል እውነት እንደሆነ ባላረጋገጥም››

እንደሚታወቀው ባለፉት ስድስት ወራት በመጅሊስ ላይ የተደረገው የሕዝበ ሙስሊም ተቃውሞ በመንግሥት አመራሮችና በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ጭራና ቀንድ ተስሎለት የሙስሊሙን ጥያቄ የአውሬ ገጽታ ቢያላብሱትም፤ በአወሊያ ት/ቤት የተቀሰቀሰው ብሶት የወለደው የሕዝበ ሙስሊም ተቃውሞ መላ ኢትዮጵያን እያዳረሰ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የክልል ከተሞች የአህባሽን የግዳጅ አስተምህሮ በመቃወምና የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮችን አመራሮች በመቃወም የየራሳቸውን እርምጃ እየወሰዱ ሲሆን በአዲስ አበባ ለዘመናት በጥቃቅን ልዩነት ተለያይቶ የነበረው መላው ሙስሊም ማኅበረሰብ በመሰባሰብ "የሰደቃና የዳዕዋ" ፕሮግራም በማዘጋጀት በየሳምንቱ አዲስ አበባ በሚገኙ የተለያዩ መስጊዶች ሕዝቡ ከኪሱ እያወጣ ድግስ እያዘጋጀ ነው። መንግሥት ለክፉ የተመኘው ሕዝበ ሙስሊም በተቃራኒው በፍቅርና በወዳጅነት መንፈስ በመሰባሰብ አንድ መሆን ጀምሯል። ይህ ከ22 ዓመታት በፊት ወደነበረው የሐጂ ሳኒ ሐቢብ የአመራር ዘመን ይመልሰናል። ሐጂ ሳኒ ሐቢብ በ1969 የተደረገው ታላቁ የሙስሊሞች የመንግሥት ተቃውሞና መብት የማስከበር ሂደት ውጤት ናቸው። በወቅቱ ከነበረው የመብት ጥያቄዎች አንዱ የሙስሊም ተቋም ይኑር እና መሪዎቻችንን እንምረጥ የሚል የነበረ ሲሆን በወቅቱ በመንግሥት ይሁንታ ሕዝበ ሙስሊሙን ወደ አንድነት ማምጣት ይችላሉ ተብለው ተመርጠው ለ13 ዓመታት ያህል ሙስሊሙን በአንድ መንፈስ ሲመሩ እስከ ሕልፈታቸው ቀን ድረስ ቆይተዋል። የአሁኑ ተሰናባች የመጅሊስ ሊቀመንበር ሐጂ አብዱላሂ ጨሎ አንድም ቀን መስጅድ ውስጥ ኢስላማዊ መጽሐፍ ይዘው ሃይማኖታዊ ትምህርት ሲያስተምሩ በግሌ አላየሁም፤ አንድም ቀን ሙስሊሙን ሰብስበው በሃይማኖታዊ ጉዳይ ሲያማክሩ አልሰማሁም። የመረጣቸው አካል መጠቀሚያ ሆነው በገቡበት የጓሮ በር ወጥተዋል።

የአወሊያ ተማሪዎች ጥያቄ ወደ ሀገር አቀፍ ጥያቄነት ከተለወጠና ሙስሊሙም የመብት ጥያቄዎቼ ናቸው ብሎ ያሰፈራቸውን ሦስት ጥያቄዎቹን እንዲያስመልሱለት 17 ሰዎችን ቢመርጥም ተመራጮቹን እውቅና የነፈጉት አካላት የመሰላቸውን ሲያሰሩ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ቆይተዋል።

### መንግሥት በሙስሊሞች መቼ ተለወጠ?

የየሀገራቱን መንግሥታት ጉድ የሚያጋልጠው ዊክሊክስ የኢትዮጵያ መንግሥትን ምስጢሮች አዝረክርኮ እንደነበረ ይታወሳል። ይህን ጽሑፍ በማጠናቀርበት ወቅት በ2009ዓ.ም የአሜሪካ ኤምባሲ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ የላከውን መረጃ ከድረ-ገጽ ላይ ቃኝቼ ነበር።

ኤምባሲው ኢትዮጵያን በተመለከተ ካሾለከው መረጃ አንዱ ወሃቢያን የተመለከተ ነው። ወሃቢዝም በኢትዮጵያ ማቆጥቆጥ ጀመረ የሚለው ከ9/11 የአሜሪካ ጥቃት ወዲህ እንደሆነና ካልቸራል ኢምፔሪያሊዝም እየተስፋፋ መሆኑን ያትታል። አክሎም ከመስከረም አሥራ አንዱ የአሜሪካ መጠቃት በፊት በኢትዮጵያ ወሃቢዝም እንዳልነበረና ከዚያ ወዲህ የመጣ ጭራቅ እንደሆነ ያትታል። ይህንን ከየት እንዳመጣው ማወቅ አልችልም። የኔ ማስረጃ ይቅርና በቅርቡ ጠቅላይ ሚንስትሩ በፓርላማ ለሕዝብ ተወካዮች እንዳብራሩት ወሃቢዝም በትክክለኛው አጠራሩ ሰለፊ በኢትዮጵያ አስተሳሰቡን ማስፈን የጀመረው ከ30 ዓመት ወዲህ እንደሆነ መግለጻቸው ይታወሳል። ታዲያ የኤምባሲው መረጃ ምንን ያመለክታል?

እንደኔ ግምትና አብዛኞች ጉዳዩ የሚያሳስባቸው ሙስሊም ምሁራን የተስማሙበት እውነት አሜሪካ በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ይስፋፋል ብላ የምታስበውን የእስልምና አክራሪነትን ለመግታት ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ የእቅድ ለውጥ ማድረጓን ነው። ይኸውም ሥጋቱ አለኝ በምቻላቸው ሀገራትን ላሉ መንግሥታት የኢኮኖሚ ድጋፍና ከእስልምና አስተምህሮ ይልቅ እስልምና ወደ ባህላዊ እምነት የመለወጥ ሥልትን የሚከተለውን የአህባሽን አስተሳሰብ ማስረጽ ነው። ይህን ለማድረግ የመንግሥታቱንና የሃይማኖት ተቋማቱን በተቻለ መጠን በቁጥጥር ሥር ማድረግ አማራጭ ተደርጐ ተወስዷል። አሜሪካ በተለያዩ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት የእስልምና ጉዳይ ቢሮዎች እጇን አስገብታለች እየተባለ ይወራል። አህባሽ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በኬንያ፣ በዑጋንዳ፣ በጅቡቲና በሌሎችም ሀገራት እንዲስፋፋ ጥርጊያ መንገድ እየተመቻቸለት ነው። አሁን አሁን ስሙን ቀይሮ ሙስሊሞች ሁሉ የሚጠቀሙበትን "አህለሱና ወልጀመአ" የሚል ስያሜን እየተጠቀመ ነው።

የአሜሪካ ኤምባቢ ከ2009 ወዲህ በእስልምና ተቋማት ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ መጀመሩን በተለያዩ ተግባራቱ አሳይቷል።

የእስልምና አጋርነቱን ለማሳየት የባሌ ሸኽና ሁሴን መቃብር ሥፍራን እድሳት አድርጓል። ለሐረር ሙዚየም ጥበቃም ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በአዲስ አበባ የመሐመድ ዐሊ ቤትን እድሳት አድርጓል። ይህ ሁሉ ጠንካራው የእስልምና አስተምህሮ የማይፈልጋቸውን ቦታዎች በማሰስ አማኙን ሕዝብ የማማለል ሥራ እየሰራ ነው። ከዚህም ባሻገር የእስላማዊ ድርሳናት ጥበቃ ማዕከል በሙዚየም ውስጥ እንዲቋቋም፣ አደጋ ላይ የነበሩና ከኢትዮጵያ ሊወጡ የነበሩ ኢስላማዊ ድርሳናትን ገዝቶ እንዲጠበቁ ጥረት አድርጓል። ይህ መልካም ገጽታ ያለው ተግባር ነው። ማንም ሙስሊም ጥንታዊ የምርምራ ሥራዎች እንዲወድሙ አይፈልግም። በእርግጥ ይህ ለእስልምና ከመቆርቆር አንፃር ነውን?

የዊክሊክስ ሌላው መረጃ የወሃቢያ ተጽእኖን ለመቋቋም ባህላዊ መርሐግብሮችን ማከናወን በሚል ርዕስ ኤምባሲው ወደ አሜሪካ የላከውን ትንታኔ የሚያጋልጥ ነው። ኤምባሲው ከላይ እንደገለጽኩት እስልምናን ለማሽመድመድ ከተፈለገ ባህላዊ እሳቤዎችን ማጠንከር ነው፤ ለዚህም ለቦታዎች፣ ለቁሳቁሶች፣ ለልማዳዊ ተግባራት ትኩረት ሠጥቶ በመሥራት የሰዎችን የትኩረት አቅጣጫ ማሳትና የትርኪ ምርኪ አስተሳሰብ ማጠራቀሚያ ማድረግ ነው። ለዚህ ደግሞ በዋነኛነት የሚጠቀመው የእስልምና መንገድ በጽዮናዊያን ከፍተኛ ድጋፍ እየጐለበት የመጣውን አህባሽን ማጠናከር ነው። (ስለ አህባሽ ማንነት በዚህ ጋዜጣ በተለያየ ጊዜ በወዳጆቹ ዩሱፍ፣ ይስሃቅና አክመል የተዘረዘረ በመሆኑ አልመለስበትም)

ዊክሊክስ የኻሊድ አቡ ኤልፈድልንም ጉዳይ አንስቶ ነበር። ይህ ሰው አሜሪካዊ ሙስሊም ሲሆን ወሐቢያን የሚያጠላሽ መጽሐፍ ጽፏል። መጽሐፉ ወሐቢያ ጽንፈኛና አሸባሪ መሆኑን የሚተነትን ነው። ይህ መጽሐፍ በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በሱማሊኛ ቋንቋ ለማስተርጐም ኤምባሲው ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም ተርጓሚዎች መጽሐፉ አደገኛና የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የመከፋፈል አጀንዳ የያዘ ነው በማለት ለመተርጐም አንገራግረዋል። ኤምባሲው ግን የሰዎቹን እምቢተኝነት በመልካም አላየውም ከተርጓሚዎቹ ሥጋት ይልቅ ኤምባሲው ወሃቢያ በኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ እንደማሳያ ነው ብሎ ነው የተረዳው።

### ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሙስሊም ተለውጧልን?

በጋዜጠኝነት ባለፉት 13 ዓመታት አገልግያለሁ። የተለያዩ ምሁራንንም በተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች አነጋግሬያለሁ። ከሰባት ዓመታት በፊት የታሪክ ምሁሩን መድኃኔ ታደሰን ስለታሪክ ፋይዳ አነጋግሬያቸው ነበር። "የታሪክ ጥናት ፋይዳ..." ይላሉ አቶ መድኃኔ "የታሪክ ጥናት ከትናንት ለመማር ዛሬ ያለንበትን ሁኔታ ለመረዳትና ነገን ከዛሬ የተሻለ ለማድረግ ነው" ብለውኝ ነበር።

የኢትዮጵያ ሙስሊም መንግሥት እንደሚፈልገው ትናንት "በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ መስሊሞች" ተብሎ እንደተጠራው ዛሬ እንዲጠራ አይፈልግም። ትናንት ያለፉት አዬዎች በእስልምና ላይ ጥቁር አሻራን ጥለው አልፈዋል። ዛሬ የትናንት ኹነቶች በደንብ እየተፈተሹ ነው ከ40 ዓመታት ወዲህ ስሙን ሳይቀይር መማር የጀመረው ሙስሊም ዛሬ በትናንት ላይ የምርምር ሥራዎቹን እያደረገ ነው። ዛሬ ማለትም ከኢህአዲግ ሥልጣንን መጨበጥና ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ሊያስማማ የሚችል ሕገ-መንግሥት አርቅቆ ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ ወዲህ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ ሕገ-መንግሥቱ የሰጠውን ነፃነት በጥቂቱም ቢሆን መጠቀም ጀምሯል። ከዚህም የተነሳ ሐይማኖቱን በነፃነትና በእውቀት በማዳበር እየተገበረው ይገኛል። በዚህ ዲሞክራሲ በሰጠው ነፃነት የተለያዩ አመለካከት ያላቸው የእስልምና አስተሳሰቦች ተስፋፍተዋል። ሁሉም የአስተሳሰብ መንገዶች በሂደት ወደ አንድነት መጥተዋል ማለት ይቻላል። ይህን የአንድነት መንፈስ በመጠቀም ሙስሊሞች በመሪ ተቋማቸው ያለውን ድክመት በማጋለጥ ነጻና በሕዝብ ፍቃድ የተመረጠ አመራር እንዲኖራቸው ጠየቁ። ከትናንት የተማሩ ሙስሊሞች ነገን ላለማበላሸት ዛሬን ማስተካከል የሚል አላማን አነገቡ። ይህ ያበገነው መንግሥት የሙስሊሞች ወደ አንድነት መምጣትና ሊበትናቸው ወደ መሐላቸው የወረወረውን አህባሽ መቃወማቸው የእግር እሳት ሆኖበት ለሙስሊሞች የተለያዩ ስያሜዎችን መስጠት ጀመረ። ሲያሻው "በኢትዮጵያ ውስጥ ኢስላማዊ መንግሥት ሊያቋቁሙ የፈለጉ ናቸው" ሲል ሌላ ጊዜ ደግሞ "ጽንፈኛ አሸባሪ፣ ግብር አንከፍልም የሚሉ ወሃቢያ፣ ሰለፊያ" እያለ በየዘው የመገናኛ መሣሪያ የስድብና የዘለፋ ተግባሩን ማከናወን ከጀመረ ዋል አደር ብሏል።

ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ባለፉት 20ዓመታት የአስተሳሰብ ለወጥ ማምጣቱ አይካድም። ይህም የሆነው መንግሥት በፈጠረው ምቹ አጋጣሚ ነው። በቀድሞ ዘመናት ያለእውቀት ይሠሩ የነበሩ ሃይማኖታዊ ተግባራት አሁን በእውቀት እየተተገበሩ ናቸው። ኢሰላማዊ እውቀት ማስፋፊያ ማዕከላት በድረ-ገጽ በሠፊው ይገኛሉ። ባለፉት ሃያ ዓመታት በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በርካታ መስጊዶች ተሠርተዋል። ይሄ የሆነው ግን ወሃቢያ ወይም ሠለፊያ ስለተስፋፋ አይደለም። የሙስሊሙ ንቃት ሕሊና በተፈጠረው ምቹ አጋጣሚ ስለዳበረ ነው። ሌላው ወደ አረብ አገራት የሚሄዱ እህቶቻችን እየበዙና የእስልምናን ምንነት እያወቁት መምጣታቸው ቀድሞ በጭፍን ጥላቻ ፊት ይነሳ የነበረው እስልምና ከእውነታው ጋር አለመጣጣሙ አንድ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

ለውጦች በሀገራችን በተለያዩ መስኮች ተከናውነዋል። ባለፉት 20 ዓመታት እውቀት በቀላሉ መሠራጨት ጀምሯል። ሠዎች በመማር ራሳቸውን መለወጥ ችለዋል። ዓለምን ወደ አንድ መንደርነት የለወጠው ቴክኖሎጂ በየትኛውም ሀገር የሚከናወነውን ነገር በቀላሉ ለመረዳት ራስን ካለው ነገር ጋር ለማዋሃድ ሕይወትን ለመለወጥ መንቀሳቀስ በርክቷል። የኢትዮጺያ ሙስሊሞች የዚህ ዕድል ተቋዳሽ በመሆን ስለ ሃይማኖታቸው ብዙ ነገሮችን ማስተንተን ጀምረዋል።

በፊት የነበሩት ባህሎች፣ ወጐች፣ ደንቦችና ሥርዓቶች ዛሬ እየተለወጡና እየተሻሻሉ በአዳዲስ እየተተኩ መጥተዋል። ሌላው ቀርቶ አልባሳት በየዘመኑ ተለውጠዋል፣ የፀጉር አበጣጠር ስልት፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የዘይቤ፣ የስልታዊ አነጋገር፣ ከዘመንና ከለውጥ ጋር ከእድገትና ከእውቀት ጋር ይለወጣል።

የኢትዮጵያ ሙስሊሞችም ሃይማኖትን ማወቅና መተግበር፣ ስህተትን ማረም፣ ከእውቀት ማነስ የማይከወኑ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን መከወን ከማወቅ የመጣ እንጂ በጽንፈኝነትና በአክራሪነት የተነሳ የመጣ አይደለም። ባለፉት 20 ዓመታት በርካታ መስጊዶች ተሠርተዋል። ሆኖም አክራሪና አሸባሪዎች ባቀረቡት ጥያቄ አልነበረም መስጊዶቹ የተሰሩት። የኢትዮጵያ ሙስሊም ለዘመናት መስጊድ የመሥራት ፈቃድ ተከልክሎ ስለነበር ነው። በነዚህ መስጊዶች ውስጥ የሚሰግዱ ሰዎች ብዙ መስጊድ ውስጥም ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ይሰጡ ጀመር። በመሆኑም ብዙ ሰዎች ሃይማኖታቸውን አወቁ። ቀድሞ ይሰሯቸው የነበሩ ነገሮች ቀስ በቀስ መተው ጀመሩ። ይህ አክራሪነት፣ አሸባሪነት አልያም አዲስ እስልምና መጣ አያስብልም።

### የሙስሊሙ ጥያቄ ተመልሷልን;

ባለፉት ስድስት ወራት በአወሊያ ት/ቤት ቅጥር ግቢ የመብት ጥያቄ እንቅስቃሴ መደረጉና ሙስሊሙ ጥያቄዬን ያሰሙልኛል ያላቸውን 17 ምእመናን መምረጡ ይታወሳል። ምእመናኑ ለመንግሥት መቅረብ ይገባቸዋል ያሏቸውንና ሕዝቡ በፊርማ ያጸደቃቸውን ሦስት ጥያቄዎች ለመንግሥት አካላት ቢያቀርብም የመንግሥት ሹማምንት ታዋቂውን የፖለቲካ ቁማራቸውን በጥያቄዎቹ ላይ እየተጫወቱ ነው። ጥያቄዎቹ በግርድፉ የነበሩት

1. የመሪ ድርጅታችንን (መጅሊስ) መሪዎች በነፃነት እንምረጥ
2. እጅ ተጠምዝዞ የሚሰጠው የአሕባሽ አስተምህሮ ይቁም
3. አወሊያ የሙስሊሙ ተቋም እንደመሆኑ ሕዝበ ሙስሊሙ በሚመርጣቸው ቦርድ አባላት ይመራ ነበር።

መንግሥት ጥያቄዎቹን እንደተቀበለና ምላሽ እንደሚሰጥ ገልጾ በፌደራል ጉዳዮች አመራሮችና በሬዲዮ ፋና የፌዝ ሠርግና ምላሽ ዓይነት ሥራ ተሠራ።

በቅርቡ ደግሞ ማንነታቸውንና ምንነታቸው የማይታወቁ ሰዎች በወረዳ በኩል የእስልምና ጉዳዮች አመራር ምርጫ ሊደረግ እንደሆነ እየተነገረ ነው። ይህ ይፋዊ ያልሆነ የጓሮ ወሬ ሙስሊሙ ሊጠየቀው መሪዎቻችንን በመስጂዶቻችን እንምረጥ ጥያቄ የፌዝ ምላሽ የሰጠ ነው።

በአሁኑ ጊዜ በአንድ ወረዳ ውስጥ ያሉ ዜጎች የሚተዋወቁ አይደሉም። ማን አዲስ ይሁን ማን ነባር፣ የቱ የወረዳው ነዋሪ ይሁን የትኛው መጤ የወረዳው ሰዎች አያውቁም። ለመሆኑ መንግሥት እንደሚፈልገው ምርጫው በወረዳ ከተካሄደ ሙስሊሙ መሪ መረጠ ሊባል ነው? ቀድሞ ነገር መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ምን ጥልቅ አደረገውና ነው በፌደራል ጉዳይ ቢሮ አማካይነት ምርጫውን የሚያካሂድልን? ለእስልምናና ለሙስሊም የመንግሥት አመራሮችና ጋዜጠኞች ያላቸው የንቀት ደረጃ እንዲህ ከፍ ያደረገው በአሜሪካ አይዟችሁ ባይነት ነውን? ይህ በጓሮ በር የሚመረጠውን መሪ እንግዲህ እንደሚታወቀው የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በተለመደው ድራማዊ የማንቀለጳጰስና "ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ" የፉገራ ስልት ብሎም "አንዳንድ የአዲስ አበባ ሙስሊም ነዋሪዎች" የሚባል ለክፉ ጊዜ የተቀመጠ ቃላት ቡራኬ በመስጠት አብዛኛውን ሕዝበ መስሊም እንዳላዋቂ ለማድረግ ጥረት መደረጉ አይቀርም። የተለመደው ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ወሃቢያ በሚል ታፔላ፤ አንዳንዱን ደግሞ ጽንፈኛና አሸባሪ በሚል ትርዒቶች ሊሠሩ እንደሚችሉ ይገመታል። ይህ መቼም የፕሮፓጋንዳውን ስልት አብሮ ከመኖርና ብዙ ከማየት የምናውቀው ነውና አይጠፋንም። በዚህ ሁኔታ የተመረጠው መሪ በእውነት ከሕዝቡና ከመንግሥት ጋር ተስማምቶ የሚኖር ነው ተብሎ ይገመታልን? ይሄ ሁሉ አባጣ ጐርባጣ መንገድ ከመሄድ ኢህአዴግ ጉንበስ ማለትን ለምን ጠላ; ለምንስ እውነታው አነቀው; ለምን የሚተቹትን ይፈራል፤ ያስፈራራል፤ ያስራል፤ ይገድላል; እስከ መቼ በዚህ ሁኔታ እየመራ ይኖራል; እሱ ያውቃል!

እውነቱ ግልጥልጥ ብላ የወጣች ቀን ዛሬ ለፍርፋሪ ብለው ሕሊናቸውን የሸጡ ሕዝብን የማተራመስ ተንኮላቸውን በብዕር ያራመዱ ጋዜጦች አያፍሩም ይሆን? ለነገሩ ራሳቸውን በብዕር ስም ጋሻነት የከለሉ በመሆናቸው እፍረታቸው ሊታወቅ አይችልም። ብሎም የነሱ ሳይሆን የፕሮፓጋንዳው አጀንዳ ሰለባ በመሆናቸው የታዘዙትንና ተፈልፍሎ የተሰጣቸውን አቅጣጫ ተከትለው ነው የሚሠሩት። እስከ መቼ ከሕሊናቸው ተጣልተው እንደሚኖሩ ራሳቸው ይወቁት።

የሆነ ሆኖ ከወር በኋላ የሚመጣው ረመዷን ሕዝበ ሙስሊሙን ወደ መስጂድ ይሰበስበዋል። ስለነገሩ በጥልቀት ያልተረዳው ነገሩን እያወቀ ይሄዳል። በረመዷን ሊፈጠር የሚችለውን ነገር መንግሥት መስጋቱ እውነትነት አለው። ሆኖም ከሥጋት ለመዳን ከሕዝብ መጣላት መቼ መፍትሔ መሆኑን ሰምቼ አላውቅም።

መስማት የምትችሉ አመራሮች ካላችሁ የሙስሊሙን ጥያቄ በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ፣ ሁሉንም ወገን በሚያስማማ መልኩ መመለስ ይሻላል። በግሌ ነገሩ ካፈነገጠ የሚኖረው አደጋ ያስፈራኛል። ቸር እንሰንብት። ቸር ያሰማን።

---

## ነገረ መጻሕፍት

… ከገፅ 13 የዞረ

ለእናንተም ጥቅም ነው፤ ጭናችሁ ትወስዳላችሁ አለን፤ ሌላው ደግሞ፤ በፍጹም አይሆንም፤ መጽሐፉን ሸጠን ምን ብለን ነው ገቢ የምናደርገው? አለ። ከብዙ ክርክር በኋላ ተፈቀደልንና ሁለት አይሱዙ መኪና ጭነን ወደ አዲስ አበባችን። ሁለት ሺህ አራት መቶ ብር ነው የፈጀብን። ወልቂጤ ሄደንም የራስ ዘሥላሴን ት/ቤት ደጅ አንኳኳን፤ ወሊሶ ዘልቀንም የገረሱ ዱኪ ት/ቤት ሰዎችን አነጋገርን፤ አላሳፈሩንም።

በኋላ ግን አንድ መዘዝ መጣ፤ ከጓደኞችን አንዱ የሆነው መስፍን አርጋው በደህንነቶች እጅ ተያዘ፤ ታሰረ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፎቶ ያለባቸውን መጻሕፍት በድብቅ ሲሸጥ ነው የተገኘው። በዘውዱ ሥርዓት ደራስያን ሲያሳትሙ፤ ከመጀመሪያዎቹ ገፆች ባንዱ፤ የጃንሆይን፣ የእቴጌ መነንና የአልጋ ወራሹን ፎቶ ያትሙ ነበር፤ ቢያንስ ያንዳቸውን። እኛ ከየት/ቤቱ የሰበሰብናቸውን መጻሕፍት ለአንባብያን እንዳንሸጥ ብንታዘዝም እኛ ግን ደርግ የማይፈቅዳቸውን ፎቶዎች እየገነጠልን በድብቅ እንሸጥ ነበር። ድንገት ከመስፍን እጅ አንድ መጽሐፍ ሾልኮ ወጣ፤ የጃንሆይ ፎቶ ያረፈበት። በዚህ የተነሣ ታሰረ። ስንት ወር እስር ቤት እንደቆየ ታውቃለህ? በዚያች መጽሐፍ ሰበብ ሦስት ወር ታሰረ፤ ማዕከላዊ እስር ቤት። አስረው ሲገርፉት ጊዜ፤ ከአንተ ጋር ማን ነበር? ሲባል፤ ቢጨንቀው የእኛን ስም ሰጠ፤ የአስራ አንዶቻችንንም። ተጠራን፤ ፈርሙ ተባልን፤ አይለመደንም በሉ ተባልን፤ ፈርመን ወጣን፤ እኛም መስፍንም። እሱ በታሰረ ጊዜ ቤተሰቦቹን እየተመላለስን እንጠይቅ፣ እንደግፍ ነበር፤ በሥራ ጊዜ አብረነው ሆነን በችግር ጊዜ ከጐኑ አንርቅም ብለን …

(በነገራችን ላይ ሦስት ወር ማዕከላዊ እስር ቤት ታስሮ የተፈታው መስፍን አርጋው ማለት፤ ባለፈው ሣምንት ለአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ መጽሐፍ እሸጥላቸው ነበር ብሎ ለጌጡ የነገረው ነው።)

… … …

ይኸው ነው፤ ጋሽ ይልማ በረካ እንዲህ ናቸው፤ ይኼ ነው የፈሰሱበትና እየፈሰሱበት ያለው የሕይወት ወንዝ። ጋሽ ይልማም፣ ጋሽ ተስፋዬ አዳልም - እንዳልኳችሁ - እንደሚሸጧቸው መጻሕፍት ሊነበቡ የሚገባቸው ባለታሪኮች ናቸው። እኔ - በወፍ በረር ቅኝት እንዲህ ካነበብኳቸው - እናንተ ብትሆኑ - በእነሱ ውስጥ - ስንትና ስንት ዓለም ታዩ ነበር? ስንትና ስንት ቦታ አስጉዘው ይመልሷችሁ ነበር?

# ነገረ መጻሕፍት - ፪

# የአፄ ኃይለሥላሴ ፎቶ ያለበት መጽሐፍ ሲሸጥ ተይዞ 3 ወር ታሰረ



እንዳለጌታ ከበደ

ጋሽ ይልማ በረካ ጋ እንሂድ። ጋሽ ይልማ አዲስ አበባ፤ ፒያሣ ደርሰን፤ አራዳ ጊዮርጊስን አልፈን፤ አዲስ አበባ ሜዲካል ዩኒቨርሳል ኮሌጅ አካባቢ ከምናገኛቸው አሮጌ መጽሐፍ ሻጮች መሐል አንዱ ናቸው። ጋሽ ይልማ ብዙ ናቸው፤ ትሁት ናቸው፤ በዚህ ሙያ ሰበብ ብዙ የመውጣትና የመውረድ ህይወት አሣልፈዋል። ያሳለፉትን ውጣ ውረድ እንዲህ አውግተውኛል …

… … …

በአንድ ወቅት አቶ ዳኛቸው ወርቁን አግኝቸው ነበር፤ አቶ ዳኛቸው በመልክ ብዙ የሚታወቅ አልነበረምና፤ ራሱ ነው፤ መጽሐፍ ወደምሸጥበት ቦታ መጥቶ የተዋወቀኝ "ዳኛቸው ነኝ፤ አደፍርስ የሚል ልቦለድ ከሃያ ዓመት በፊት አሣትሜ ነበር፤ እና አሁን የተወሰኑ ቅጂዎች ስላሉኝ ልትገዛኝ ትችላለህ?" ብሎ ነበር የጠየቀኝ።

ስለመጽሐፉ አውቃለሁ፤ አንዳንድ ትላልቅ ሰዎች ይፈልጉታል፤ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና የሥነጽሑፍ ምሁራን ይጠይቁናል፤ መጽሐፉ ገበያ ላይ ከዋለ በኂላ፤ ጋዜጠኞችና ደራሲያን መጽሐፉን ሲያብጠለጥሉበት ጊዜ፤ ተናዶ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእኔን መጽሐፍ አንብቦ ለመረዳት ገና ነው፤ ገና ሃያ ዓመት ይቀረዋል ብሎ፤ ያሰራጨውን መጽሐፍ ሰብስቦ፤ ቤቱ ቆለፈበት ሲባል በወሬ ሰምተናል።

ይኸው አሁን መጣ፤ አንድ ሺህ ቅጂ አለኝ አለ። ልያቸው አልኩት፤ ተያይዘን ወደ ቤቱ ሄድን፤ ሰውየው ብዙ አያወራም፤ ዝግ ነው፤ ከሚመስሉት ሰዎች ጋር ያወራ ይሆናል፤ ከእኔ ጋር ግን ቃል ሳንለዋወጥ ቤቱ ደረስን። ቤት ውስጥ አንዲት ልጅ እግር ሴት ነበረች - ወዲያ ወዲህ የምትል። ልጅ ትሁን ሰራተኛው አላውቅም። አስከትሎኝ ወደ አንድ ክፍል ገባን። ክፍሉ በ 'አደፍርስ' ተሞልቷል፤ እዚያና እዚህ በተበታተኑ፤ በወረቀት ታሽገው በተደረደሩ፤ አንድ ሺህ ቅጂውን ነው የምሸጠው? አለኝ፤ በስንት ሂሣብ? አልኩት፤ አንዱን በ12 ብር። 12ሺህ በጠቅላላ አለኝ፤ አንዱን 12 ብር? 12 ሺህ በጠቅላላ? እንዴት ይሆናል? በአሁን ዘመን ትልቅ የተባለው ባለ ስድስት መቶ ገፅ መጽሐፍ የአሌክሳንደር ዱማስ ፔሬ 'እፎይታ' ነው፤ ዋጋውም ዘጠኝ ብር ነው፤ እኔ 12 ብር ገዝቼ ለነጋዴ ስንት ልሸጠው? ባይሆን 11 ብር ይደረግልኝ አልኩ፤ አላስጨረሰኝም፤ ውጣ! ውጣልኝ ከቤቴ አለ፤ ተቆጣ፤ አደፍርስን 11 ብር ትለኛለህ፤ ውጣ ሲለኝ፤ አሰብኩበት፤ አያዋጣኝም ይሆን? ብዬ ፈራሁ፤ በመጨረሻም ልግዛው ብዬ ቆረጥኩ፤ በቃ እሺ፤ 12 ብር ሂሣብ እወስዳቸዋለሁ አልኩት፤ እሱም አልሸጥም አለኝ፤ አስራ ሁለት ብር እኮ ነው ያልኩት፤ አንተ ልትሸጥ ባሰብክበት ዋጋ ልስጥህ … ስለው፤ አስራ ሁለት ብር አልሸጥም፤ የምትገዛ ከሆነ አንዱን 15 ብር ሂሣብ ውሰድ …አለኝ፤ አሁን በአሁን? ስለው ደግሞ፤ አዎ፤ ሦስት ብር ጭማሪ አድርጌበታለሁ። ቅድም በጠራሁልህ ዋጋ ወዲያውኑ ብትስማማ ኖሮ አይጨምርም ነበር፤ አለኝ። ትቼ ወጣሁ፤ ቆይቶ ለሌላ ነጋዴ ሽጦ አከፋፈለው፤ ስንት እንደሸጠው አላውቅም።

… የአንዳንድ ደራስያን ባህርይ አይገባም፤ አይገባኝም፤ አይግባቡንም። አንዳንዶቹ ደግሞ የተለየ ልማድ አላቸው፤ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ገብረኢየሱስ ኃ/ማርያም የተባለ ሰው "የጫሙት ሽካ" የሚል በጉራጊኛ ቋንቋ ልቦለድ አሣተመ። ይህ ሰው በፊት አርዕስት ስጡልኝ፤ ጉዱና ታሪኩ፣ "የመዓዛ ጉዞ" እና ሌሎችም ሥራዎች አሉት፤ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ደግሞ "የጉራጌ ባህልና ታሪክ" የሚያወሳ መጽሐፍ ውጭ ሀገር ታትሞለታል።

የመጻሕፍት ምረቃ ተብለን፤ ግብዣ ተደርጎልን፤ ቤቱ ሄድን። ብዙ ሰው ጠርቷል፤ ከአሮጌ መጽሐፍ ሻጮች እኔ ክብሩ ክፍሌ እና ሌሎችም አለን። በላን፤ ጠጣን ቁርጡም ክትፎውም ጠጅና ውስኪውም ተቀዳ። በኂላ፤ አንድ ትልቅ ሰው ኧረ ይኼ ነገር ምንድነው፤ መጽሐፍ ምረቃ ብለህ ጠራኸን፤ ማለፊያ መስተንግዶ አደረግህልን፤ ግን የት አለ መጽሐፉ? ሸጥልን እንጂ ገዝተን እናንብብ አሉት - ደራሲውን። ደራሲውም፤ ይኼን ግብዣ አሰናድቼ እናንተን መጥራቴ፤ ከሃያ ዓመት በፊት የፃፍኩትን፤ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በጉራጊኛ ቋንቋ የተፃፈ ልቦለድ በማሣተሜ የልብ ኩራት አድሮብኝ፤ የደስታዬ ተካፋይ እንድትሆኑ ነው እንጂ፤ መቼ መጽሐፍ ልሸጥላችሁ ሆነና? … መጽሐፌን መግዛት ከፈለጋችሁ ከነገ ጀምሮ በየመደብሩ ሂዱና ግዙ እንጂ እኔ መች ለንግድ ፈለግኂችሁ? አለን - አልረሣውም።

… ደርግ እንደወደቀ፤ እኛ መጻሕፍት ነጋዴዎች ተባድነን፤ መጽሐፍ የማሳተም ሥራ መስራት ጀመርን፤ በዝና የሰማነውን መጽሐፍ ማስተርጐሙን ተያያዝነው - ገቢያችንም ዳጐስ ያለ ሆነ። ቃል ኪዳን ልቦለድን ከጌታቸው አያልቄ ተረክበን ያሣተምነው እኛ ነበርን - የመጀመሪያ ርዕሱ ሰቀቀን ነበር፤ ሰቀቀን ሣቢ ርዕስ አይደለም፤ ሌላ ይሁን፤ ለምሣሌ ቃል ኪዳን ቢሆን ከታሪኩ ጋር ይስማማል ብለን ደራሲውን አሣምነን አሣተምነው።

አንዴ ሙያው መምህር የሆነ - የፊዚክስ መምህር ቢሆንም ለሥነ ጽሑፍ ልዩ ፍቅር የነበረው - ደበበ የሚባል ወዳጅ ነበረን። የኬን ፎሌትን ‹‹eyes of the needle›› የሚለውን ተወዳጅ ፊክሽን የመርፌው ዓይን በሚል ርዕስ ይዞት መጣ። ሥራውን ወድደን ርዕሱን ጠላነው፤ ቀይረው፤ አልነው፤ ካልቀየርከው አናሣትምልህም አልነው፤ ተቆጣ፤ ተቀየመን፤ ሥራዬ ልጄ ነው፤ የልጄን ሥም ቀይር፤ ለውጥ የምትሉኝ እናንተ እነማን ናችሁ? ይህንን መብትማ አልሰጣችሁም፤ ብሎ ረቂቅ ድርሰቱን ይዞ ሄደ፤ ጥቂት ቀናት ቆይቶ ተመልሶ መጣ፤ መጽሐፌን መርፌው ብዬዋለሁ አሁንስ? አለን፤ ያው ነው አልነው፤ ያው አይደለም፤ ይኼ መርፌው ነው የበፊቱ የመርፌው አይን፤ አይገናኝም አለን፤ እኛም፤ ቀይር ገንዘባችንን አውጥተን ስናሳትም ለኪሣራ አይደለም አልነው፤ አልሰማንም፤ ሄደ፤ ተዉት እናንተን አልፈልግም፤ አንጋፋው ደራሲና ሀያሲ አስፋው ዳምጤን - አድራሻውን ፈልጌ፤ ሥራዬን አሳይቼ፤ አስተያየቱን ተቀብዬ፤ በፕሮፌሽናል አሳታሚ ማሳተም እፈልጋለሁ፤ ብሎ ተጣልቶን ሄደ - እንዴት ያለ ወዳጃችን።

ብዙም ሣይቆይ፤ ማሞ ውድነህ አዲስ የትርጉም መጽሐፍ አወጣ ተባልን፤ መጽሐፉ በእጃችን ገባ፤ ሾተላዩ ሰላይ ይላል፤ ደራሲው ኬን ፎሌት። ደነገጥን፤ ያ መምህር ተቀደመ፤ የለፋበት ስራ ከንቱ ሆነ። … በጣም ነበር ያዘንነው።

… መንግሥት ሲቀየር እና የአገዛዝ ስርዓት ሲለወጥ የእኛም ሕይወት ቅርፁን ይለውጣል፤ ኢሕአዴግ ሊገባ ሲል፤ ሲገባ እና ከገባ በኂላ የሲድኒ ሼልደንን፣ የዳንኤላ ስቲልን፣ የአጋታ ክርስቲን ስራዎች አስተርጉመን፤ የዳግላስ ጴጥሮስን ስሞተኛውን አሳትመን፣ የአሸናፊ ዘደቡብ መጣጥፎችን ለኅትመት አብቅተን፤ የገንዘብ አቅማችን ከፍ ብሎ አልነበር? ደርግ ሥልጣን ላይ ሲወጣ ደግሞ ሌላ የተለየ ሕይወት ነበረን።

አንዴ - ከጓደኞቼ ጋር ሆኜ - መድኀኔዓለም ት/ቤት ኳስ እየተጫወትኩ ነበር። ኳሱ የተጠለዘበት ቦታ ስንደርስ አንድ ነገር አየን። ያየነው ነገር ቅጠል ለብሷል - የባህርዛፍ ቅጠል። ምንድነው ይኼ ቁልል? ብለን አጥብቀን ስናይ ለካስ መጽሐፎች ናቸው። ቅጠሉን ገልጠን ስናይ የታሪክ፣ የልቦለድና የትምህርት መጻሕፍት ተከምረዋል። የትንቢት ቀጠሮ፣ ሆኅተ ጥበብ፣ ፍቅር እስከ መቃብር፣ አርአያ፣ ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ። ብዙ የምናውቃቸው አንብበንና አስነብበን የተመሰጥንባቸው መጻሕፍት እዚህ ትንሽ የተራራ ቁልል ሠርተዋል። ይኼ ነገር ምንድነው ብለን ተጠግተን የት/ቤቱን አስተዳደር ስንጠይቅ፤ በእሳት ለመቃጠል የተዘጋጁ ናቸው አለን። ደነገጥን፤ ተሳቀቅን። ለምንድነው የሚቃጠሉት ስንል ደግሞ፤ መጻሕፍቱ ደርግ ከሚከተለው ርዕዮተ ዓለም ጋር አብረው አይሄዱም፤ የአገር አቆርቋዥ፣ የፊውዳል ርዝራዥ አመለካከት የሰፈረባቸው ናቸው አለን። እነ ፍቅር እስከ መቃብር፣ እነ አርአያ ሁሉ ሊቃጠሉ? ስንል፤ የነዳጅ ጉዳይ ቸግሮን ነው እንጂ ይኼን ጊዜ በቦታው የአመድ ክምር ነበር የምታዩት፤ ነዳጁም ጠፍቶ ሳይሆን በየትኛው በጀት ይውጣ ብለን እየመከርንበት ነው አለን።

በዚህ ጊዜ፤ ከት/ቤቱ አስተዳደር ተነጥለን፤ ለምን አንገዛቸውም ተባብለን ተወያየን፤ ገብተንም ነገርናቸው፤ ለወረቀት ፋብሪካ የምትሸጡት ወይም ለንባብ ሳይሆን ለእቃ መጠቅለያ የምታውሉት ከሆነ እሺ አለን ዳይሬክተሩ፤ ደስ አለን። ስንት ኪሎ መጻሕፍት አስመዝነን እንደገዛን ታውቃለህ? አስራ አንድ ሺህ ኪሎ። ለአንድ ኪሎ ስንት እንደከፈልን ልንገርህ? ሰባ አምስት ሳንቲም።

ከዚያ በየት/ቤቱ መሄድ ጀመርን፤ ምክንያቱም እነዚህ ነባርና በንጉሡ ዘመን የታተሙ መጻሕፍት ተዘምቶባቸዋል። ከበላይ አካል በወረደ ትዕዛዝ፤ ቤተመጻሕፍት ውስጥ ያሉ ነባር ድርሳናት ቦታቸውን የማርክሲዝም፣ ሌኒኒዝምን ርዕዮተ ዓለም ለሚያስተዋውቁ የፖለቲካ መጻሕፍት እንዲለቁ እየተደረገ ነው።

ይህ ነገር አሳሰበንና፤ በአንድ ጓደኛችን ሃሳብ አፍላቂነትና ጠቋሚነት ወደ አንድ ምሁር ሄድን። ምሁሩን ታውቃቸዋለህ። ያኔም ተሰሚና ዝነኛ ነበሩ፤ አሁን ደግሞ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የህግ አማካሪ ሆነዋል ብለውኛል። እሳቸው ጋ ሄደን፤ ትዝ ይለኛል፤ ስድስት ኪሎ ማደያው አጠገብ መኪናቸው ውስጥ አገኘናቸውና ያየነውን ነገርናቸው፤ ፊታቸው ተለዋወጠ፤ ከዓይናቸው እንባ ወረደ፤ እንዴት መጽሐፍ ይቃጠላል? አሉ፤ ተቆጡ፤ ተቆጩ፤ መጽሐፎቹ ከተቃጠሉ ስለትላንት እንዴት እናውቃለን? ታሪካችንን ማን ይነግረናል? እነዚህ እኮ የትላንትም የዛሬም ታሪኮቻችን ናቸው አሉ። በማግሥቱ ይህንን አባባላቸውን በቴሌቭዥን ሲናገሩት ሰማን።

ከዚያም አንድ ፈቃድ ተሰጠን፤ የተወገዱትን እንድንገዛ፤ የገዛነውን ደግሞ ለወረቀት ፋብሪካ እንድንሸጥ። ይህችን አጋጣሚ ተጠቅመን አዲስ አበባን አካለልነው። ኮልፌ፣ አዲስ ከተማ፣ ኮከበ ጽባህ፣ ንፋስ ስልክ፣ …እየተባደንን ገዛናቸው። አግዓዚ፣ እንደወጣች ቀረች፣ ሴተኛ አዳሪ፣ እንቅልፍ ለምኔ፣ የከበደ ሚካኤል ሥራዎች፣ የተክለፃዲቅ መኩሪያ ሥራዎች … ሌሎችም ለጊዜው ርዕሳቸው የተዘነጋኝ፤ ብዙ ዓይነት መጻሕፍት …

ከአዲስ አበባ ወጣንና ደግሞ ወደ ሰባት ቤት ጉራጌ እንድብር ሄድን። እዚያም ለእሣት እራት ሊሆኑ ተሰናድተው ነበር። አንዱ የት/ቤቱ ማኅበረሰብ አባል፤ ችግር የለውም ከሚቃጠሉ ለት/ቤቱ ገቢ ነው፤

ወደ ገፅ 12 ዞሯል »

## ዜናዎች

### በሁለት የሙስና ወንጀል ክሶች የተከሰሰው ግለሰብ 19 ዓመት ተፈረደበት

በሁለት የሙስና ወንጀል ክሶች ተከሶ ጉዳዩን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ወንጀል ችሎት ይከታተል የነበረው ግለሰብ ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ባሳለፍነው ማክሰኞ ዕለት በ19 ዓመት ከስድስት ወር እስራትና በብር 25,000 እንዲቀጣ ተወሰነ።

በፌዴራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ክስ የተመሰረተበት አቶ ተፈራ ደበበ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በሀዋሳ የደንበኞች አገልግሎት መስጫ ማዕከል ሰራተኛ ነበር።

የመጀመሪያው ክስ እንደሚያስረዳው ከሆነ ግለሰቡ ከላይ በተጠቀሰው የኃላፊነት ቦታ ላይ ተመድቦ በሚሰራበት ወቅት የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ከሚያዝያ 29/2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ የካቲት 24 ቀን 2003 ዓ.ም. ድረስ ለደንበኞች ሸጦ ለኮርፖሬሽኑ ገቢ እንዲያደርግ ከተረከባቸው ቢሎች ውስጥ በድምሩ 2,274,922.74 አጉድሎ ለግል ጥቅሙ አውሏል።

በሁለተኛው ክስ ደግሞ ተከሳሹ በተጠቀሰው መ/ቤትና የኃላፊነት ቦታ ላይ ተመድቦ ሲሰራ ከሚያዝያ 2001-ታህሳስ 2003 ዓ.ም. ድረስ ከተረከባቸው ቢሎች ውስጥ የገንዘብ መጠናቸው ኔጋቲቭ ብር 806,209.04 በሆኑ 265 ቢሎች ላይ የሚገኘውን የኔጋቲቭ ምልክት በመፋቅና ወደ ፖዘቲቭ በመቀየር፣ እንዲሁም ከፖዘቲቭ ቢሎች ጋር ቀላቅሎ ለኮርፖሬሽኑ መመለሱን ለመረዳት ተችሏል።

በዚህ መሰረት ተከሳሹ በከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል እና መንግስታዊ ሰነዶችን ወደ ሀሰት በመለወጥና በእነዚህ ሰነዶች በመገልገል በሁለት የሙስና ወንጀሎች ክስ ተመስርቶበት ጉዳዩ ከግንቦት ወር 2003 ዓ.ም. ጀምሮ በፍ/ቤቱ ሲታይ ቆይቷል። በመሆኑም ተከሳሹ ኮሚሽኑ የመሰረተበትን እነዚህን ክሶች ሊከላከል ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት የተገለፀውን የእስርና የገንዘብ ቅጣት ወስኖበታል።

### ‹‹የ2005 በጀት የሚሸፈነው በአገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ ነው››

የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ሚ/ር

### ‹‹ለፖለቲካ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም››

አቶ ተመስገን ዘውዴ

የኢትዮጵያ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የ2005 ዓ.ም በጀትን ከፍተኛ ድርሻ የሚሸፍነው በሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ መሆኑን እና በጀቱም 137.8 ቢሊዮን ብር እንደሆነ ጠየቀ።

ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው የ2005ዓ.ም በጀት አመት የተደገፈው በበጀት ዝግጅቱ በአመቱ የዋጋ ንረትን ወደ አንድ አሀዝ ማውረድ፣ የብር የውጭ ምንዛሬን ተመን የ5 በመቶ ቅናሽ እንዲያሳይ እና ለብሄራዊ ክልላዊ መንግስት መንግስታት የሚውለው የወጪ በጀት ድጋፍ ካለፉት ጊዚያት አንፃር እንዲጨምር ማድረግ የሚሉትን ታሣቢ ያደረገ መሆኑን በረቂቁ ተገልጿል።

የ2005 ዓ.ም በበጀቱ ላይ የሚታየውን 26.6 ቢሊዮን ብር ጉድለት በሀገር ውስጥ እና ከውጪ ሀገራት በሚገኝ ብድር ለመሸፈን ማቀዱን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አስታውቋል።

መከላከያ 6.5 ቢሊዮን፣ ፍትህና ደህንነት 1.8 ቢሊዮን፣ የፌዴራል ፖሊሲ 876.5 ሚሊዮን ፣የትራንስፖርትና መገናኛ 667.6 ሚሊዮን፣ ኢሬቴድ 311.9 ሚሊዮን፣ የከተማ ልማት ኮንስትራክሽን 296 ሚሊዮን ብር በማግኘት ከበጀቱ ከፍተኛውን ድርሻ የወሰዱ ተቋማት ሲሆኑ ከ2004 ዓ.ም. በጀት ጋር ሲነፃፀር ተቋማቱ ከ2-27 በመቶ ጭማሪ ተደርጎላቸዋል።

በበጀት አመቱ መንግስት የዋጋ ንረቱን ወደ አንድ አሀዝ ማውረድ የሚለውን ታሳቢ በማድረግ የነደፈውን እቅድ ‹‹በመንግስት ችሎታ ወደ አንድ አሀዝ ይገባል ማለት አይቻልም›› በማለት የምክር ቤት አባል የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ሪፖርቱን ነቅፈዋል።

የቀድሞ የምክር ቤቱ አባል እና የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራር እና የኢኮኖሚ ባለሙያ የሆኑት አቶ ተመስገን ዘውዴ ‹‹አመታዊ በጀቱን እየጨመሩ የዋጋ ንረቱን አሁን ካለበት 40 በመቶ የዋጋ ንረት ወደ አንድ አሀዝ አስገባለሁ ማለት ለፖለቲካ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅም። አብሮ የሚሄድ ነገር አይደለም›› ሲሉ በጀቱን ተችተዋል።

የኢኮኖሚ ባለሙያው ‹‹ቀድሞም ልማታዊ መንግስት የተባለው ከማክሮ ኢኮኖሚ ጋር ተጣጥሞ የመሄድ ግንዛቤ ያለው አይመስለኝም›› ሲሉ ስጋታቸውን ለፍትሕ ገልፀዋል።

የበጀት ጉድለቱን ለማሟላት የውጪ እርዳታው ምን ያህል አስተማማኝ ነው የሚል ጥያቄ ከምክር ቤቱ የቀረበላቸው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ሶፊያን አህመድ ‹‹በጀቱን ስንሰራ አጠቃላይ ዝርዝር ላይ አተኩረን ነው። ቃል የገቡትን በወቅቱ ይሠጣሉ›› ሲሉ መልሰዋል። አያይዘውም የበጀቱን ጉድለት ለማሟላት በዋናነት የአለም ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ እና የእንግሊዝ መንግስት ላይ መንግስት ተስፋ ሰንቋል›› ሲሉ ሚኒስቴሩ አቶ ሶፊያን አህመድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተናግረዋል።

### የሠመጉ 8 ሚሊዮን ብር ይገባኛል የፍርድ ቤት ክርክር ዛሬ መቋጫ ያገኛል

የሠብዓዊ መብት ጉባኤ (ሠመጉ) በ2001 ዓ.ም. የታገደብኝ ከ8 ሚሊዮን ብር በላይ ይገባኛል በሚል ከማህበራት ማደራጃ ኤጀንሲ ጋር እያደረገ ያለው ክርክር ዛሬ በሰበር ሰሚ ችሎት ይታያል።

ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሠመጉ በ2001 ዓ.ም. የወጣውን አዋጅ ተከትሎ የማህበራት ማደራጃ የኤጀንሲ ቦርድ ያገደውን ገንዘብ መልክቶ ለኤጀንሲው የፀና እንዲሆን ወስኖ ነበር።

የከፍተኛውን ፍርድ ቤት የፍርድ ውሳኔ ተከትሎ ሠመጉ ለሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው አቤቱታ መሰረት ፍርድ ቤቱ የህግ ግድፈት ተፈጽሞ ከሆነ ይታያል በማለት ለውሳኔ ቀጠሮ በያዘው መሠረት ዛሬ ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል።

### ‹‹ሜድ ኢን ቻይና›› ኮሜዲ ፊልም እሁድ ይመረቃል

በመስፍን ኃ/እየሱስ (ጠጆ) እና ቴዎድሮስ ስዩም ደራሲና ዳይሬክተርነት የተዘጋጀውና በምሳሌ ፊልም ፕሮዳክሽን በኩል የቀረበው ‹‹ሜድ ኢን ቻይና›› የተሰኘ አዲስ ልብ አንጠልጣይ ኮሜዲ ፊልም እሁድ ሰኔ 10 ቀን 2004 ዓ.ም. በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች ባሉት በግል ሲኒማ ቤቶች በ8፡00፣ በ10፡00 እና በ12፡00 ሰዓት ይመረቃል።

ከ100 በላይ ተዋንያን የተሳተፉበት ይሄው ፊልም ተሰርቶ ለመጠናቀቅ የአንድ አመት ጊዜ ሲፈጅበት ከእሁድ ባሻገር በልዩ ፕሮግራም ሰኞ ሰኔ 11 ቀን 2004 ዓ.ም. በ11፡30 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር ጥሪ የተደረገላቸው ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮች፣ ታዋቂ ግለሰቦች አርቲስቶችና ጋዜጠኞች በተገኙበት በድምቀት እንደሚመረቅ አዘጋጆቹ በተለይ ለፍትሕ ገልፀዋል።

### ‹‹የማስተዋልና የመገንዘብ ጥረትና ውጤት›› በሚል ርዕስ የቀረበው መፀሐፍ በገበያ ላይ ዋለ

‹‹የማስተዋልና የመገንዘብ ጥረትና ውጤት›› የተሰኘው የአማረ መልካ መፀሐፍ በ ተክሌ መፀሐፍት መደብር አከፋፋይነት ከትናንት በስቲያ ለገበያ ውሏል። መፀሐፉ በ11 ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በእለት ተለት እንቅስቃሴዎቻ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችና ውጤቶቻቸው፣ እንዲሁም አገር የሚያስተዳድሩ መሪዎች ያላስተዋሉዋቸውንና ሊያስተውሏቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ይዳስሳል ተብሏል። መፀሐፉ 196 ገጾች ሲኖሩት ዋጋውም 40 ብር መሆኑ ተገልጿል።

### የአፍሪካ የህፃናት ቀንን በማስመልከት የኪነጥበባት ፕሮግራም ተዘጋጀ

ዛጎል ቤተመፃሕፍት ከእሸት ኢሲዋይዲኦ ጋር በመተባበር 5ኛውን ልዩ የጥበብ መሰናዶ ቅዳሜ ሰኔ 9 ቀን 2004 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ ልዩ የልጆች የኪነጥበባት ፕሮግራም በሀገር ፍቅር ቲያትር አዘጋጀ።

በዝግጅቱ ግጥሞች፣ ትረካዎች፣ የልጆች መዝሙር፣ መነባንቦችና ሌሎች አዝናኝ የሰርከስና የዳንስ ትርኢቶች በልጆችና በታዋቂ አርቲስቶች እንደሚቀርቡ ተነግሯል። ዝግጅቱ ልጆችን ከማዝናናት በተጨማሪ በመልካም ስነምግባር እንዲታነፁና የኪነ ጥበብ ተሰጥኦዋቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስችል ነው ተብሏል።

# እንኳን እናቱ የወለደችው፤ አማቱ ኮራች የተጋባችው::



ከታዴዎስ ታንቱ

የኢትዮጵያ አርበኛ በከፍተኛ የሥነ ልቦና ዝግጅት በተጠንቀቅ ይስተዋላል:: የነፃነት ትግል ራሱ የራሱን ተመን አስቀምጧል:: የግድ ይከፈላል:: ጀግና አያቅማማም:: ፈሪ አይቆርጥም:: ትግል ድልን ያፈራል:: ድል ባርነትን ያሽቀነጥረዋል:: አሁን በቀያ ሞረት ጎሸ ቀበሌ ውስጥ ቆመናል:: አርበኛው ያቅራራል:: ፉከራው ደርቷል:: ጦርነቱ ሊከፈት ተቃርቧል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እየተግተለተለ መጥቷል:: ዕብሪትን የዘራ ውድቀትን ያጭዳል:: ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ለሀገሩ በሀገሩ በክብር ይሰዋል:: ወራሪው ኃይል ግን በሰው ሀገር ይቅበዘበዛል:: የዘራውን ያጭዳል:: ያጨደውን ይሰበስባል:: አሁን ወራሪው ኃይል በቅድሚያ ተነሳሽነት የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ድምፅ አሰምቷል:: ያበጠው ይፈንዳ! አርበኛው አፀፋውን መልሷል:: ጦርነቱ ተከፍቷል:: በቀያ ሞረት ጎሸ እሳት ይንቦገቦጋል:: ባሩድ ይሸትታል:: ትንታግ ይወረወራል:: ቡም! ቡም! ቡም! ቦምብ! ድም! ድም! ድም! ጠብመንጃ! ድፍን ቀያ ሞረት ጎሸ ተናወጠ:: ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ በኃይል ሚዛን የበላይነትን ጨብጧል:: ወራሪው ኃይል ተጠቅቷል:: ሳይወድ በግድ አፈግፍጓል:: አሁንም ግን ይተኩሳል:: በሙሉ አቅሙ ይዋጋል:: በአልቦ ተስፋ ይወራጫል:: ከአናብስት መንጋጋ ሥጋ ሊያወጣ ይፍጨረጨራል:: የማይቻል ነገር ቋምጧል!

ቀያ ሞረት ጎሸ የደም ጎርፍ መሬት ሆኗል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አርበኛውን አልተቋቋመም:: በጦርነቱ ሒደት ትኩስ ወሬ ተሰምቷል:: የሻለቃ አዛዥ መኮንን በጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ተገድሏል:: በምኞት አልተነዛም:: በፈጠራ አልተወራም:: የሻለቃ አዛዡ ተገድሏል:: ሬሣው ተዘርሯል:: ለማንሣት የደፈረ አልነበረም:: ወራሪው ኃይል ፈርጥጧል:: ሬሣ በየቦታው ተዝረክርኳል:: አርበኛው በርካታ የጦር መሣሪያዎች ማርኳል:: የመኮንኑ ሬሣ ሳይነሳ ውሎ አድሯል:: አሞራ በጥብጦታል:: ጅብም ጎትቶታል:: ምንም አያስደንቅም:: ዕብድ ውሻ ተገድሎ የትም ይጣላል:: ጉሮ ወሸባ! ይህ የቀያ ሞረት ጎሸ የድል ድምፅ ነው! አርበኛው ኃይሌ ሽንቁጥ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን አጭዷል:: አጭዶ ከምሯል:: ከምሮ ለሰማይ አዕዋፍና ለምድር አራዊት ሰጥቷል:: መስኩን ለቅቋል:: ይህ የቀያ ሞረት ጎሸ የድል ድምፅ ነው! ሕዳር 23 ቀን 1930 ዓ.ም. ጉሮ ወሸባ! ጉሮ ወሸባ! የኢትዮጵያ አርበኛ ድል አድርጎ ሲገባ! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! ከቀያ ሞረት!

ጀግናው አርበኛ ኃይሌ ሽንቁጥ አሁን መርሐቤቴ ከራ ገብቷል:: ታሪክ ሊሠራ መጥቷል:: አንድ ጭንቅሎ የተባለ ለማዳ ባንዳ ሕዝቡን በማተረማመስ ላይ እንደነበረ ሰምቷል:: በጌታዋ የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች! ጭንቅሎ ከጣሊያን በላይ ጣሊያን ሆኗል! ሰላማዊውን ሕዝብ ይገድላል:: ሰበብ እየፈጠረ ይረሽናል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እስካለ ማንም እንደማይነካው ተሰማው:: በቂ የጦር መሣሪያ አከማችቷል:: ምልምል ባንዳ አስከትሏል:: ጠንካራ ምሽግ ሠርቷል:: ትንሹ የመርሐቤቴ ቄሣር ሆኗል:: ጥቁሩ ሞሶሎኒ! ጀግናው አርበኛ ኃይሌ ሽንቁጥ ጠንካራውን የጭንቅሎን ምሽግ ከበበው:: ሞት ወይም ሽረት! ለማዳው ባንዳ ጭንቅሎ ማምለጫ አጣ:: የግድ ተታኩሶ ለመሞት ወሰነ:: ውሳኔውን ገቢራዊ አደረገ:: በፈጣን አፀፋ ጦርነቱ ተፋፋመ:: ለሰዓታት ቀጠለ:: በዚህ ሒደት ቆራጡ ኃይሌ ሽንቁጥ በቀዳሚ ተነሣሽነት በአንደኛው የምሽጉ ክንፍ ላይ አደጋ በመጣል በርካታ ምልምል ባንዳዎችን ገድሏል:: ጭንቅሎ ተጨነቀ:: የጦር አይሮፕላን እንደሚደርስለት በተስፋ ጠበቀ:: ተስፋው በተስፋ ቀረ:: በተግባር ምንም አልታየም:: ምኞት ድርጊት አይሆንም:: ጦርነቱ በአርበኛው ድል አድራጊነት ተፈፀመ:: ስንት ሞተ? ምን ያህል ቆሰለ? ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አገልጋዮች 38 ተገድለዋል:: በማን አህሎኝነት ልኩን የዘነጋው ጭንቅሎ በዚሁ ጦርነት ምሱን አግኝቷል:: የውሻ ሞት ሞቷል! ‹‹እኔን ያየህ ተቀጣ›› ብሏል:: በዚሁ ጦርነት በጀግናው ኃይሌ ሽንቁጥ ከተመራው የኢትዮጵያ አርበኛ መካከል አምሥት ጀግኖች ተሰውተዋል:: ድል አድራጊው አርበኛ ተንጎማለለ:: የድል ድምፅ ተስተጋባ! የአርበኛ እናት ኩሪ! የአርበኛ አማት ኩሪ! የአርበኛ ሚስት ኩሪ! ኢትዮጵያ እናታችን ኩሪ! ጥር 19 ቀን 1930 ዓ.ም. ከመርሐቤቴ ኩራ!

ቆራጡ የጦር ሰው ኃይሌ ሽንቁጥ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከመያዙ ጥቂት ቀደም በማለት አዲስ አበባን ለቆ መውጣቱን ታሪክ ይመሰክራል:: ጀግናው ኃይሌ ሽንቁጥ ከአዲስ አበባ በቀጥታ ወደ መርሐቤቴ አመራ:: በሚያዝያ ወር 1928 ዓ.ም. ለአርበኝነት ቆርጦ ተነሣ:: ቆራጡ የኢትዮጵያ ልጅ ኃይሌ ሽንቁጥ የወገን ሠራዊት በማይጨው ጦርነት በመፈታቱ ከፍተኛ ሐዘን ተሰምቶታል:: ቀደምት የኢትዮጵያ ጀግኖች በአድዋ ድባቅ የመቱት የኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በማይጨው ጦርነት በወገን ድል ነሺነት መፈፀሙ አንገብግቦታል:: በእርግጥ ጀግናው ኃይሌ ሽንቁጥ በኮሎኒያሊስትና በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መካከል የነበረውን ልዩነት አላጣውም:: ልዩነቱ በግልፅ ይታየዋል:: ኮሎኒያሊስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አይሮፕላኖችንና ታንኮችን አልታጠቀም:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን አይሮፕላኖችንና ታንኮችን እስከ አፍንጫው ታጥቋል:: ኮሎኒያሊስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያን ለመያዝ በመጣ ጊዜ ሕዝቡ ለመሪዎቹ የነበረው ፍቅር በጣም ከፍተኛ እንደነበረ ይታወቃል:: መሳፍንትና መኳንንቱም ይከባበሩ ነበር:: ጥቂት ከሃዲ መኳንንት ከኮሎኒያሊስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጎን መቆማቸው በእርግጥ አልቀረም:: በአምባላጌ ላይ የጀግናውን የአጼ ምኒልክን ክንድ ከቀመሱ በኋላ ግን አድዋ ላይ ከወገን ጋር ሆነዋል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በመጣ ጊዜ አንዳንድ መሣፍንትና መኳንንት ከተከታዮቻቸው ጋር ግማሽ መንገድ ሄደው ወራሪውን ኃይል እንደ ተቀበሉ ታሪክ ያረጋግጣል:: ይህ ሁኔታ ክፍተት ፈጥሯል:: ወራሪው ኃይል በዚህ ክፍተት ፈጥሯል:: የኢትዮጵያ ወታደራዊ አደረጃጀትም ከአርባ ዓመታት በፊት ከነበረበት አንዳችም ለውጥ አልተደረገበትም:: ኢትዮጵያ የቀድሞ ዓለም ማህበር አባል እንደነበረች ይታወቃል:: በዚህ ምክንያት እንደማትደፈር ግምት ተወስዷል:: ግምቱ ግን አልሰራም:: ኢትዮጵያ ተደፈረች! ተወደደም ተጠላ ኢትዮጵያ የቀድሞ ዓለም ማህበር አባል መሆኗ በሠራዊቱ አመራር ላይ የሥነ ልቦና ተፅዕኖ አድርጓል:: ውጤት አልባ ተስፋ አስጨብጧል:: ሰውን ማመን ቀብሮ ነው:: ኃያላን ራሳቸውን ለማዳን ተሽቀዳደሙ::

ቆፍጣናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጅ ኃይሌ ሽንቁጥ በዘመኑ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል የነበሩ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ድክመቶችን ለመረዳት የአስተውሎት ደኃ አልነበረም:: ድክመቶች ሁሉ እንደነበሩ ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ሠራዊት ግፈኛውን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ማሸነፍ እንደነበረበት አቋም ይዟል:: በእልህ ይተናነቅ ገባ:: ቆራጡ ኃይሌ ሽንቁጥ በ1928 ዓ.ም. መርሐቤቴ እንደገባ የምልመላ ተግባርን ተያያዘው:: ከሁሉ በፊት ግን ያባቱ ባልደረባ የነበሩ ሰዎችን ለማግባባት ቅድሚያ ትኩረት ሰጠ:: የአርበኝነት ሐሳቡን አካፈላቸው:: አባቱን ይወዱትና ያከብሩ የነበሩ ሁሉ እሱንም በአባቱ ዓይን ተመለከቱት:: የጋለ የሀገር ፍቅር ስሜቱን በጣም አደነቁ:: በዚህ መልካም አጋጣሚ ኃይሌ በጣም ተደሰተ:: ለሀሳቡ መግቢያ በር አገኘ:: የቅስቀሳ ሥራ ወሳኝነትን ደግሞ ያውቃል:: ሕዝቡ እንዳይሰበክ ይሰብክ ገባ:: ወንድ ልጅ የሆነ ሁሉ የጦር መሳሪያ እንዲሸምት አሳሰበ:: አመፅ አነሳሳ ሕዝቡን አሳደመ:: እስከ ጥቅምት 1929 ዓ.ም. በቅስቀሳ ተጋ:: በህብረተሰቡ መካከል ፀረ ፋሽስት ሥነ ልቦናን ቀረፀ:: ኃይሌ ሽንቁጥ ውጤት አስመዘገበ:: ሕዝብ ነቅቷል:: አቅም በፈቀደ መሣሪያ ተገኝቷል:: ቀጥሎ ምን ይደረጋል? ጀግናው ኃይሌ ሽንቁጥ ወስኗል:: አንድ! አንድ! አንድ! አሁን ጀግናው ኃይሌ ሽንቁጥ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ መሸገበት ተንቀሳቅሷል:: ተከታዮቹም በከፍተኛ የውጊያ ዝግጁነት ተነስተዋል:: የቡድን መሣሪያ አልያዙም:: አንዳንዶች እንዲያውም በጎራዴ ብቻ ተሰልፈዋል:: ምንም መሳሪያ ያልያዙም ተስተውለዋል:: የተማረከ መሳሪያ ለመታጠቅ ተሰልፈዋል:: የኢትዮጵያ አርበኛ ልበ ሙሉ ነው:: በተስፋ ይዘምታል:: በድል ይመለሳል:: ጦርነቱ ሊከፈት ተቃርቧል:: አርበኛው ተጠግቷል:: ፉከራው ቀልጧል:: ቀረርቶው ጦፏል:: ኢትዮጵያ ልጅ አላት:: ማን የማንን ሀገር ይወርራል? ኢትዮጵያ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መቃብር ትሆናለች! ግፉ ወደ ፊት! እናት ሀገር በምንም አትለወጥም! አርበኛው ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ምሽግ በቅርብ ርቀት ይስተዋላል:: ተቃርቧል! ተቃርቧል! ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ተኩስ ከፍቷል! ዶባ ወዲያው ቀውጢ ሆነ:: በጠብመንጃ ቃና የሞት መዝሙር ተዘመረ:: ጀግና ይወድቃል:: ጀግና ይገባል:: አለየለትም:: ቀጥሏል:: የተሰዉ ጀግኖች አስክሬን በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እንዳይማረክ በቅፅበት የማግለል ተግባር ይከናወናል:: አሸናፊው አልታወቀም:: አርበኛው ሬሣ ያመርታል:: ወኔው እንደነበረ ተሰንቋል:: አሁን የጦርነቱ ስልት ተቀይሯል:: አርበኛው በጎራዴ ገብቷል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በሣንጃ ተንቀሳቅሷል:: የጨበጣ ጦርነት ጦፏል:: የኢትዮጵያ አርበኛ አይሸሽም:: የዶባ መሬት በደም ጎርፍ ታጥቧል:: የሰው ማረጃ ቄራ ሆኗል:: ማን ድልን እንደሚቀዳጅ መተንበይ ያዳግታል:: በጎራዴ የተባረከ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎች በየቦታው ተጋድመዋል::

ወራሪው ኃይል በተስፋ የአይሮፕላን እርዳታን ቋምጠዋል:: አርበኛው ደግሞ ለይቶ ለመምታት በማያስችል መልኩ ተቀላቅሏል:: ሣንጃ ከሣንጃ ተሞሻልቋል:: ጎራዴ ከሣንጃ ተላትሟል:: ሰዓታት ነጎዱ:: ብዙ ቀላሆች ተዘርተዋል:: የድል ሚዛን ግን አልታወቀም:: ዶባ ላይ እሳት ነዷል:: ጦርነቱ በጨበጣ ቀጥሏል:: በጣም ያስደንቃል:: ኃይሌ ትንታጉ ከወራሪው ኃይል ምሽግ ዘልቋል:: አርበኛው የበላይነትን ጨብጧል:: የሞተው ተጋድሟል:: የቆሰለው ያቃስታል:: ጤነኛው ፈርጥጧል:: የድል ደውል ተሰማ:: የጀብዱ ብሥራት ተስተጋባ:: አርበኛው ዶባን ተቆጣጠረ:: የአንበሣ ዘመቻ በድል ተቋጨ:: ይህ የአርበኛው ድምፅ ነው! የዶባ ጦርነት ተጠናቅቋል:: ኃይሌ ሽንቁጥ የጀግኖች አውራ! ጥቅምት 13 ቀን 1929 ዓ.ም. ከዶባ!

ቆፍጣናው አርበኛ ኃይሌ ሽንቁጥ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሀገራችንን ለቆ ሳይወጣ ትጥቁን አይፈታም:: ዕረፍትም አይሻም:: ትግሉ ቀጥሏል! አሁን ትኩስ መረጃ ከኃይሌ ጆሮ ደርሷል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በለብቃ በኩል ቀወት አፋፍ ላይ ተደራጅቷል:: ኃይሌ ሽንቁጥ ዳቦ በማር አግኝቷል:: ይህችን ይፈልጋታል! አርበኛው በምርኮ አዳዲስ የጦር መሣሪያዎችን ታጥቋል:: ብሔራዊ ስሜቱ ጨምሯል:: የውጊያ ፍላጎቱ አሻቅቧል:: ለፍልሚያ አላቅማማም:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሥጋ ለምድር አራዊትና ለሰማይ አዕዋፍ ይሰጣል:: ኃይሌ ሽንቁጥ አሁን

**ከሥነ ቃል የተወሰደ**

ቀወት አፋፍ ላይ ሊደርስ ተቃርቧል:: አይጥ ሞቷን ስትሻ የድመትን አፍንጫ እንደምታሸት ይታወቃል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልም በምርጫው ምሱን ያገኛል:: ጦርነቱ ተከፍቷል:: ጀግናው ኃይሌ ሽንቁጥ እንደ ቀትር እባብ ተወረወረ:: የኢትዮጵያ አርበኛ አዲስ ታሪክ ይፅፋል:: ከኃይሌ ሽንቁጥ ጋር የዋለ ሞትን አይፈራም:: ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ቸኮዝ! ዲሞትፎር! ቤልጅግ! ቦምብ! ይህ የኢትዮጵያ ጀግና የአርበኝነት ድምፅ ነው! ይህ የጀግናው አርበኛ የኃይሌ ሽንቁጥ የጦር ሜዳ ድምፅ ነው! እሳት ይወረወራል:: ጦርነቱ ቀጥሏል! የጨበጣ ውጊያ አይስተዋልም:: አርበኛው ግን ወደ ወራሪ ኃይል በጣም ተጠግቷል:: የአርበኞች ሁለት ዙር ዝናር ባዶ ሊሆን ተቃርቧል:: ድም! ቡም! ድም! ቡም! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሬሣውን ይሰበስባል:: ምናልባት ሊሸሽ አቅዷል:: አርበኛው በርትቷል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን አጥቅቷል:: ወራሪ ኃይል ፈርጥጧል:: የኢትዮጵያ አርበኛ እያሳደደ ይደፋው ገባ:: አርበኛው በቀወት አፋፍ ላይ አዲስ ታሪክ አስመዘገበ:: የጀግና ዘር በተግባር ጀግና ሆኗል! ሀገሩን ከምንም በላይ ይወድል! በቀወት መሬት ላይ የነፃነት ፀሐይ በራች:: ታሪክ ይናገራል:: እውነት ተመዝግቧል! ኃይሌ ሽንቁጥ አሁንም የጀግኖች አውራ! ይህ የድል ድምጽ ነው! መስከረም 11 ቀን 1931 ዓ.ም. ከቀወት የጦር ሜዳ!

አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! ጀግናው አርበኛ ኃይሌ ሽንቁጥ አሁን የኮሎኔል ሎሬንዚኒን ወራሪ ኃይል ባሻጋሪ ለመምታት በመንደርደር ላይ ይስተዋላል:: ኃይሌ ፍርሃት አያውቅም:: ጭንቀት የለበትም:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ህልቆ መሣፍርት የለውም:: የኢትዮጵያ አርበኛ ከየአቅጣጫው መጥቷል:: የወራሪውን ኃይል ልዩ ልዩ ክንፎች ነጥሎ ለመምታት ታስቧል:: ኮሎኔል ሎሬንዚኒ ይፎክራል:: ኃይሌ ሽንቁጥ ባሻጋሪ ተኮሰበት:: ሆኖም ኮሎኔሉ አልተመታም:: ጦርነቱ ከመቅፅበት ተወሳሰበ:: ወራሪ ኃይል እየነጠለ ይመታ ገባ:: የኢትዮጵያ አርበኛ አቅሙ የፈቀደለትን ሁሉ አድርጓል:: በዚህ መካከል ጀግናው አርበኛ ኃይሌ ሽንቁጥ በጥይት ተመታ:: አጥንቱ ደቋል:: አንበሣው መራመድ አልቻለም:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አባላት ለመማረክ ተጠጉት:: ከመካከላቸው ሁለቱን ገደላቸው:: እንደማይማረክ አወቁ:: በእጅ ቦምብ ጨረሱት:: እንደ መጥመቁ ዮሐንስ አንገቱን ሰየፉት:: አንድ ታላቅ አርበኛ ተሠዋ:: ጥቅምት 19 ቀን 1931 ዓ.ም. አለቀ ደቀቀ! ብርሌው ተሰበረ! ጀግናው ወደቀ!

ዛሬ እውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች በጀግናው ኃይሌ ሽንቁጥ ላይ ልዩ በደል እንደተፈፀመበት ይሰማናል:: ምንም እንኳን ከድል በፊት ቢሰዋም ባህላዊም ሆነ ወታደራዊ ማዕረግ ሊነፈገው አይገባም ነበር:: ጀግና ወንድሞቹ ባጋጣሚ በህይወት በመቆየታቸው ከኃላፊነት ጋር እስከ ደጃዝማችነት ደርሰዋል:: ለተሰዋ ወንድማቸው ታዲያ ለምን አልተሚገቱለትም? ኃይሌ ሽንቁጥ ግራዝማችነት እንኳ ይጣ?

ጭንቅላቱ ተቆርጦ ወደ ሮማ መወሰዱ ተነግሯል:: ተአማኒነት ግን የለውም:: ከድል በኋላ ጭንቅላቱን በማፈላለግ ከሌላው አካሉ ጋር አፅሙን በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅጥር ግቢ ውስጥ ለማሳረፍ ሳይሞከር መቅረቱም የወንድሞቹ ድክመት እንደሆነ ይሰማናል:: ጀግናው አርበኛ ኃይሌ ሽንቁጥ በተሰዋበት ወይም በተወለደበት መንደር ትምህርት ቤት ወይም ሆስፒታል ካለ መታሰቢያነቱ በስሙ ይመዝገብ! ያም ያንሰዋል! ጀግናው አርበኛ ኃይሌ ሽንቁጥ ልጆች አሉት:: ሐረጉ ይቀጥላል! ዘሩ ይለምልም! ክብር ለኃይሌ ሽንቁጥ! ክብር ለነፃነታችንና ለአንድነታችን ሲሉ በዱር በገደሉ ለወደቁ ሁሉ!

እንኳን እናቱ የወለደችው፤
አማቱ ኮራች የተጋባችው::

# የጠፋው ትውልድ ... ከገፅ 5 የዞረ

ጠዋት ፈጥረው ማታ ሲያፈርሱ ለሚስተዋሉት ተቃዋሚዎች ትኩረት የሚሰጥበት ምክንያት አልነበረም:: ከዚህም ሌላ የምዕራቡ ዓለም በል ካለው ከአስር ሜትር እርቀት መርፌ እንደሚያይ ከጠመመ ደግሞ በጠራራው ፀሐይ ከጎኑ የቆመን ዝሆን ማየት እንደማይፈልግ ያልተረዱት ተቃዋሚዎች ‹ለካፒታል ሂል› መናፍስት በከንቱ ደጅ ሲጠኑ ከረሙ››

ሪቻርድ ዳውደንም ‹‹We only talked about Egypt’s role in the region, never about what was happening in side Egypt. It’s the same with Ethiopia›› (እኛ ከሙባረክ ጋር የተነጋገርነው ግብፅ በአካባቢው ላይ ስለሚኖራት ሚና ነበር:: ግብፅ ውስጥ በሚፈጠሩ ነገሮች ላይ በጭራሽ አልተነጋገርንም:: ከኢትዮጵያም ጋር ያለው የዚህ ተመሳሳይ ነው) በማለት አሜሪካዊ ዲፕሎማት የነገሩትን ጠቅሶ ይህንኑ ያጠናክራል::

ለዚህም ነው ግብፃውያን ለመጀመሪያ ጊዜ በታህሪር አደባባይ በተሰባሰቡበት ጊዜ በፖሊሶች ተገርፎ የተገደለ ካህሊል ሰይድ የተባለ ግብፃዊን ሞት ከጥያቄያቸው ጋር አሰናስለው ለተከታታይ ቀን ያዜሙበት:: ‹‹ሁላችንም ካህሊል ሰይድ ነን›› ይላል የመዝሙሩ ርዕስ:: …የዛሬ 42 አመት ወደ ኋላ ስንሄድ ደግሞ የቀድሞው ‹‹ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዩንቨርስቲ›› ተማሪ እና ‹‹የመሬት ላራሹ›› ዋነኛ አቀንቃኝ የነበረውን የጥላሁን ግዛውን በመንግስት ታጣቂዎች መገደል ተከትሎ የዩንቨርስቲው ተማሪዎችን ተከትለው መላው ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ‹‹ጥላሁን ለምን ሞተ? ለምን? ለምን ሞተ?›› ሲሉ ዘምረው አንጋፋውን ንጉሳዊ ስርአት የገረሰሱበትን ወርቃማ ታሪክ እናገኛለን:: ይህ ትውልድ ደግሞ እንዲህ የሚል ይመስለኛል ‹‹የኔሰው ገብሬ ለምን ሞተ? ለምን? ለምን ሞተ?››፣ ‹‹ዳዊት ለምን ሞተ? ለምን? ለምን ሞተ?›› …

ምክንያቱ ደግሞ በርካታ ተደራራቢ እና ከባድ ጭቆናዎችን ተከትሎ የተፈጠረው የለውጥ ጥያቄ ብቸኛው መነሻም ሆነ መድርሻው ሀገር ውስጥ በመሆኑ ነው:: ለዚህ ጥሪ ምላሽ የሚሰጡ የሃያ አንድ አመት ችግሮች የወለዷቸው ብዙ ቅሬታዎች አሉና:: እዚህ ጋር የትውልድ ተጋሪዎቼን ወኔ ለሚጠራጠሩ የጨረፍታ ምልክታ ልስጥ:: ከሃያ አንድ አመት በኋላ የምንመራው በቅዱስ ቁራን እንጂ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አይደለም፤ የሚያገለግሉንም ካድሬዎች ሳይሆኑ መንፈሳውያን መሆን አለባቸው ሲሉ ጠንካራ የፀረ-መጅሊስ እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉትን ሙስሊም ወንድምና እህቶቻችንን ሀገራዊ ለውጥ ናፋቂውን ትውልድ አይወክሉም ብሎ የሚከራከር ያለ አይመስለኝም:: ከማህበራዊ ድረ ገፆች ጀምሮ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ‹‹ሀገሬን ሀገሬን…›› የሚሉ አፍላ ወጣቶችም እንዲሁ በየአካባቢው የፈነጠቁ ሌላው የለውጡ ተስፋዎች ናቸው:: ሃያ አመት በቅጡ ካልሞላቸው ወጣቶች (ሴቶችም ወንዶችም) ውስጥ የፖለቲካ ጋዜጣና መፅሀፍ በቀንደኝነት የሚከታተሉ እየበረከቱ የሄዱበት ዘመን ነው-ይህ ዘመን:: ዛሬ ገጣሚያኖቻችንም ቢሆኑ እንደቀድሞው በቀንዳ አውጣ ስልት አይደለም እያስደመሙን ያሉት:: ድንገት ገንፍለው የፍርሃትን መጋረጃ ቀዳደው ባይጥሉም ቢያንስ እየበሳሱት እንደሆነ የሚታዩ ምልክቶች አሉ::

በአናቱም ሁላችንም እንደምናውቀው በ2002ቱ ምርጫ ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ አሸንፌያለሁ ብሎናል:: መቼም ይህ ማለት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ደጋፊዬና ወዳጄ ነው የማለት ያህል ነው:: ይህ ሁኔታ ህዝቡ ከገዥው ፓርቲ ጋር ለተያያዙ ነገሮች በሚሰጠው ትኩረት ይለካ ቢባልስ? ለምሳሌ ‹‹ህዳሴ›› የተሰኘው የኢህአዴግ ጋዜጣ እና ፍትህ ጋዜጣ ቢነፃፀሩ የትኛው በስርጭት ብዛት ይበልጣል? ብለን ልንነሳ እንችላለን:: ያለአንዳች ክርክርም ፍትህ ብለን ከተስማማን ኢህአዴግ ሙሉ በሙሉ መረጡኝ ያላቸውን ኢትዮጵያዊ ፈልገን ልናገኝ አንችልም ማለት ነው:: ከኢትዮጵያ ሬዲዮ እና ከዶቼ ቬሌና ቪኦኤ የሬዲዮ ፕሮግራሞች በአድማጭ ቁጥር ማን የተሻለ ነው? የሚል ጥያቄም ማንሳት ይቻላል:: አቶ መለስን አወድሰው የተፃፉ መጽሐፍቶች ከዋጋቸው በታች ሲሸጡ የነጋሶ ጊዳዳ ‹‹ዳንዲ›› መጽሐፍ ከ25ሺ ኮፒ በላይ በአጭር ቀን ውስጥ ተሸጦ ማለቁም ቢሆን የሚያመላክተው ነገር አለ:: የአቶ በረከት ስምኦን ‹‹የሁለት ምርጫ ወግ›› መጽሐፍ ገዢ ሲያጣ፣ በቅርቡ ያውም ከጋዜጣ ላይ ተሰባስቦ የታተመ መፅሀፍ በአስር ቀን ውስጥ 40 ሺህ ኮፒ ተሸጦ ማለቁም የሚያስተላልፈው መልዕክት አለ::

እንዲህ አይነት የህዝብ ውሳኔዎችን ዳኛ አድርገን ብንወስድ በትውልዱ ሀገር ወዳድና የመንፈስ ጥንካሬ ላይ ጥያቄ ያላቸው ሰዎች መልስ ያገኛል ብዬ አስባለሁ:: የእኔም በሀገሬ ወጣቶች ላይ የመተማመን መነሻ ይህ ነው-ሌላ አይደለም:: እነዚህ ወጣቶች ናቸው ታህሪርን ተስፋ ያደረጉት:: ይህ ማለት ግን በዱር በገደሉ ከሚሰደዱትም በላይ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ አቅም እያላቸው ኢትዮጵያ የተፀነሰውን ፅንስ ሳይቀር አሜሪካ ሄደው በመውለድ መጭው ትውልድንም ከሀገሩ አርቀው ለስደት ያዘጋጁ ኢትዮጵያውያኖች የሉም ማለት አይደለም:: ይህ እንዳለ ሆኖ በየጫት ቤቱ የሚሰበሰቡ ስርዓቱ የፈጠራቸው ‹‹ወጣት ስራ ዓጦች›› በዋነኛነት አጀንዳ አድርገው የሚያነሱት ፖለቲካ መሆኑንም ልብ ልንለው የሚገባው:: እኔም እያልኩ ያለሁት ‹‹ፖለቲካ እና ኮረንቲን በሩቁ›› የሚል ፈሊጥ ተከታዮች ያሉትን ያህል ‹‹ፖለቲካ እና ኮረንቲ ብርሃን ይፈጥራሉ›› ብለው የሚያምኑና ለችግሮቻችን ሁሉ መፍትሄ በሀገራችን ነው ያለው የሚሉ የአዲሱ ትውልድ ብላቴናዎች በዝተዋል ነው::

የሆነ ሆኖ ከጥቂት ዓመታት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጋዜጠኞች ‹‹ልጆቹ ‹ፋኖ ተሰማራ› ብለው እንዲዘምሩ አልፈልግም ሲሉ ከዚህ በኋላ የ‹‹ጓዶች እንመለሳለን›› ተስፋ የሞተ ታሪክ ነው የሚል አንድምታ ያለው መልስ ሰጥተው ነበር:: ባለፈው አመት የግንቦት ሃያን በዓል አስታኮ በሚሊኒየም አዳራሽ ፓርቲያቸው በጠራው ስብሰባ ላይ ደግሞ የታህሪር ናፍቂዎች ሟርት መክሸፉን ተናግረዋል:: ዘንድሮ ግን እንዲህ የሚሉ አይመስለኝም:: ከፈርኦን ምድር የተነሳው የታህሪር ሽታ ወይ እየሰነፈጣቸው አሊያም እያወዳቸው ነውና:: ትውልዱም ቢሆን የያ ትውልድን ‹‹ጓዶች እንመለሳለን›› መዝሙር የሚመርጠው አይመስለኝም:: ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ጀምሮ የሚተወው ነገር የለምና:: ምናአልባት የያ ትውልድ ወካይ በአፓርታይድ የጭቆና ዘመናት ነፃነታቸውን ለማግኘት ላይ ታች ሲሉ የዋተቱትን የደቡብ አፍሪካ ልጆችን አንድ የሀገራቸው ባለቅኔ በጠራበት መንፈስ ይናገሩም ይሆናል:: እንዲህ እያሉ:-

‹‹ተራሮችን እየወጡ፣ ወንዞችን እና ሸለቆዎችን
አቋርጠው እየመጡ ያሉት ልጆቹ ናቸው››

## ሁለት ጋዜጣ አዟሪዎች ‹‹ፍትህ ጋዜጣ ሕገ-ወጥ ነው እንዳትሸጡ›› ተብለን ነበር አሉ

### ‹‹ጋዜጣው የተያዘው ሕጋዊ ነው፣ አይደለም በሚል ሳይሆን በእግረኛ መንገድ ላይ ተዘርግቶ ስለተገኘ ነው››

/ወ/ት መብርሀት ገ/ሚካኤል (የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ የወረዳ 04 አስተዳደር ጽ/ቤት የፍትሕ ጽ/ቤት ኃላፊ/

ግንቦት 24/2004 ዓ.ም. ለንባብ የበቃችውን ፍትሕ ጋዜጣን ምሽት 12፡00 ሰዓት ገደማ ሳር ቤት አደባባይ አካባቢ በመሸጥ ላይ እያሉ ‹‹ጋዜጣውን መሸጥ አትችሉም፣ ተከልክሏል›› በሚል ከያዙት ጋዜጣ ጋር በፖሊሶች ተይዘው ቀሪ ጋዜጦችን መሸጥ ሳይችሉ መቅረታቸውን ሁለት ጋዜጣ አዟሪዎች ለዝግጅት ክፍሉ ተናግረዋል፡፡

ከድር ዳዬ የተባለው ጋዜጣ አዟሪ ከላይ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ሱዳን ኢምባሲ አቅራቢያ መንገድ ላይ የተለያዩ አልባሳትንና ቁሳቁሶችን የሚሸጡ ነጋዴዎች በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እየተያዙ በነበረበት ወቅት በአጋጣሚ በስፍራው እንደነበረ ገልጿል፣ ሙባረክ አብደላ የተባለ ጓደኛው ጋዜጣ ከመሸጥ ባሻገር የተለያዩ መጫሚያዎችን መሬት ላይ ዘርግቶ ይሸጥ ስለነበረ በወቅቱ ጫማው ተይዞበት ወደ ቀበሌ ሊሄድ ሲል ከድርን ጠርቶት የቀረውን 10 ፍሬ ፍትሕ ጋዜጣን በአደራ እንዲያስቀምጥለት ይጠይቀዋል፡፡

ከድርም የሙባረክን ጋዜጦች ተቀብሎ ከራሱ ጋር በመያዝ መንገድ ሲሻገር ፖሊሶች ወደ እነሱ እንዲመጣ ይጠሩትና የጓደኛውን ጋዜጣ ከተቀበሉት በኋላ እራሱ እየሸጠ የነበረውን 10 ፍሬ ፍትህ ጋዜጣንም ጨምረው በመያዝ ወደ ቀበሌ መሄድ አለብህ ሲሉት ‹‹እኔ ፋንቱ ሱፐርማርኬት አካባቢ ስሸጥ ነበር፡፡ ወደዚህ የመጣሁት በአጋጣሚ ነው፣ ጋዜጣዬን ስጡኝ? የቀሩኝን የምሸጠው ነገ ነው›› በማለት ለያዙት አካሎች ጥያቄ ያቀርባል፡፡

ከያዙት ውስጥም አንደኛው ‹‹ጋዜጣውን መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡ ይሄ ሕገ ወጥ ጋዜጣ ነው፡፡ ምን እንደሚል አታውቅም ወይ? ፍትሕ ማለት ምን ማለት ነው? ውስጡ ምን እንዳለ ታውቃለህ? ፖለቲካ አይደለም ወይ? ፍትሕን ከዛሬ ጀምሮ መሸጥ አትችልም›› አሉኝ የሚለው ነጋዴ፣ ጋዜጣው በእለቱ እንደማይሰጠው ከተነገረው በኋላ ከቀበሌው ከምሽቱ 1 ሰዓት በኋላ መውጣቱን ለፍትሕ በአዘኔታ ገልጿል፡፡ እንዲሁም የቀበሌውን ጥበቃም ጋዜጣውን ሊያስመልሱለት ከቻሉ በሚል ሲጠይቃቸው በቁጣ እንዳባረሩት አስረድቷል፡፡

ሙባረክም በበኩሉ ጋዜጣ አዙሮ ከመሸጥ በተጨማሪ መንገድ ላይ ጫማ እንደሚሸጥ ያመነ ሲሆን፣ ጋዜጣው ከተያዘበት በኋላ ‹‹ጋዜጣውን መሸጥ ተከልክሏል፡፡ ጋዜጣው ሕገ-ወጥ ነው›› ተብያለሁ በማለት ለፍትሕ ተናግሯል፡፡

ጋዜጣ አዟሪዎቹ ላነሱት ቅሬታ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ የወረዳ 04 አስተዳደር ጽ/ቤት የፍትሕ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑትን ወ/ት መብርሃት ገ/ሚካኤልን ቢሯቸው በመሄድ አነጋግረናቸው ነበር፡፡

‹‹በወቅቱ በቦታው ስለነበርኩ ጥያቄው መምጣቱ በጣም ጥሩ ነው›› በማለት ምላሻቸውን የጀመሩት ኃላፊዋ ‹‹ሳር ቤት አካባቢ በከፊል የእኛ ነው፡፡ በእግረኛ መንገድ ላይ የተለያዩ ሸቀጦችን የሚሸጡ ሕገ-ወጥ ነጋዴዎች አሉ፡፡ በጊዜው ፍትህ ጋዜጣም መንገድ ላይ ተበትኖ ነበር ያገኘነው፡፡ የእኛ ጥያቄ ከጋዜጣው ጋር አይደለም፡፡ መንግስት ለእግረኛ ብሎ ባዘጋጀው መንገድ እግረኞች መሄድ አለባቸው፡፡ በቦታው ሕገ- ወጥ ንግድ ማካሄድ ስለማይቻል በወቅቱ የነበረውን ማንኛውንም ነገር ሰብስበን ወደ ቀበሌያችን አምጥተናል›› ብለዋል፡፡

በዕለቱ ቦታው ላይ እሳቸውን ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከተው የቀበሌ አካል፣ እንዲሁም የፖሊስና የወጣት ሊግ አባላት እንደነበሩ የጠቆሙት ወ/ት መብርሃት፣ ‹‹ጋዜጣው በሕገ-ወጥ ንግድ ቦታ ላይ ቢያዝም ፍትሕ ጋዜጣ ውስጡ ምንድን ነው ያለው? የሚለውን የምናውቀው ነገር የለም›› በማለት ለፍትሕ ገልፀዋል፡፡

ነገር ግን ቀበሌ ውስጥ ከገባን በኋላ የነበርነው አካላት ስለጉዳዩ እየተነጋገርን በነበረበት ወቅት ‹‹ጋዜጣው ተከልክሏል›› የሚል ነገር ቀርቦ እንደነበረ ያስታወሱት ኃላፊዋ፣ ጉዳዩን ለማጣራት ወደ ጉፋ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ በመደወል ኃላፊዋን ማነጋገራቸውን ተናግረዋል፡፡

የጉፋ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ኃላፊም የላፍቶ ክ/ከተማ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ኃላፊን ጠይቀው ‹‹ጋዜጣው ሕጋዊ ነው፣ ማዞር ይቻላል፡፡ መጽሔቶች እየተሸጡ ስለሆነ ጋዜጣውም ይሸጣል፣ ችግር የለውም›› የሚል ምላሽ አግኝቻለሁ ብለዋል - ወ/ት መብርሃት፡፡

ከዚያም በጉዳዩ ላይ እስከ ምሽቱ 1፡30 ሰዓት ድረስ ከተወያዩበት በኋላ አዟሪዎቹ ጋዜጣውን ሰኞ ዕለት መጥተው እንዲወስዱ እንደነገሯቸው፣ ሌሎች የተያዙ ዕቃዎች ሕገ-ወጥ በመሆናቸውና ሻጮችም ከዚህ ቀደም መሰል ሪከርድ ስለነበረባቸው ንብረቶቻቸው እስከአሁን ድረስ እንዳልተሰጣቸው፣ እንዲሁም በሕገ-ወጥ ንግድ ላይ ድጋሚ ቢገኙ 500 ብር እንደሚያስከፍሏቸው በማስፈረም የተያዙትን ሰዎች እንደለቀቋቸው ኃላፊዋ አስረድተዋል፡፡

## መኢአድ በሰሜን ጐንደር የሚገኙ ሁለት አመራሮቹ የደረሱበት አለማወቁን ገለፀ

### -አንደኛው በፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ታስሮ ይገኛል

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በሰሜን ጐንደር ወረዳዎች የሚገኙ አራት የፖለቲካ አመራሮቹ ግንቦት 23 እና 24/2004 ዓ.ም. በፖሊስ በሀይል ተወስደው የደረሱበት እንደማይታወቅ እና ሌላ አባልና አመራሩ በፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ጣቢያ እንደሚገኙ ፓርቲው ማረጋገጡን ለፍትሕ ገልጿል፡፡

አቶ መለስ አሸሬ የጭልጋ ወረዳ መኢአድ ም/ቤት ሰብሳቢ ግንቦት 23 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ከመኖሪያ ቤታቸው ከ10 በላይ በታጠቁ የፌዴራል ፖሊሶች በሀይል ተወስደው የደረሱበት አለመታወቁ ተገልጿል፡፡

አቶ ስለሺ ጥጋቤ የጃናሞራ ወረዳ የመኢአድ ም/ቤት ሰብሳቢ ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ከመኖሪያ ቤታቸው ደባርቅ ከ10 በላይ በሆኑ የታጠቁ የፌዴራል ፖሊሶች በሀይል ተወስደው ለሁለት ቀናት የደረሱበት ሳይታወቅ ቀርቶ ነበር፡፡ ሆኖም ከግንቦት 25/2004 ዓ.ም. ጀምሮ በአዲስ አበባ ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ጣቢያ እንደሚገኙ ትክክለኛ መረጃ ማግኘታቸውን የፓርቲው ዋና ፀሐፊ የሆኑት አቶ ተስፋዬ ታሪኩ ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡ አያይዘውም ‹‹ለአቶ ስለሺ ምግብና አልባሳት ማቀበል እንጂ በአካል አግኝተን ማነጋገር አልቻልንም፡፡ ፖሊስ በምርመራ ላይ እንደሚገኝ ገልፆልናል›› ብለዋል፡፡

አቶ ታድሎ ተፈራ የሰሜን ጐንደር መኢአድ ጽ/ቤት የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ሲሆኑ ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡00 ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ከመኖሪያ ቤታቸው ጐንደር ከተማ በሀይል ተወስደው የደረሱበት አልታወቀም፡፡

አቶ ካሳሁን አክሊሉ የተባሉ የበክረ-ፅዮን በወቅን ከተማ የፓርቲው አደራጅም ከሚኖሩበት ከተማ በየጊዜው ያለማቋረጥ እንደሚደበደቡ፣ እንደሚታሰሩ፣ እንደሚዘረፉ፣ ቤታቸው እንደሚበረበር እና ሀብት ንብረታቸው እንደሚቀማ ምንጮች ለፍትሕ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በአለሳ ጣቁሳ ወረዳ የቀድሞ የመኢአድ ፓርቲ አባል ነበሩ የተባሉት አቶ አይችሉም አያልም ባለፈው ወር ዘመድ ለመጠየቅ በሚል ምክንያት አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ዘመዳቸው የሆኑት አቶ አብርሃም ጌጡ ጊዜያዊ ስራ ካስጀመሯቸው በኋላ ባሳለፍነው ሳምንት ሰኞ ዕለት ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ላይ በፌዴራል ፖሊሶች ተይዘው ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ጣቢያ ታስረው እንደሚገኙ ተጠቁሟል፡፡

‹‹አይችሉም ተከራይቼ ከምኖርበት መኖሪያ ቤት አብሮኝ መኖር ጀምሮ ነበር፡፡ በዕለቱም ምሳ ለመብላት ወደ ቤት እያመራ እያለ ዘጠኝ ፌዴራል ፖሊሶች ይዘውት የእኔን ቤት ሰብረው በመግባት የተለያዩ መጽሐፍቶቼንና የፓርቲ ፕሮግራሞችን በመያዝ ወደ ማዕከላዊ ይዘውት ሄደዋል›› ያሉት አቶ አብርሃም፣ ስንቅ ከማቀበል ውጪ ተጠርጣሪ ዘመዳቸውን በአካል ማግኘትና ማነጋገር እንዳልቻሉ ለፍትሕ አስረድተዋል፡፡

ጉዳዩንም ለማጣራት ወደ ሰሜን ጎንደር ዞን ፖሊስ መምሪያ በተደጋጋሚ ስልክ ደውለን ነበር፡፡ ስልኩን በማንሳት ያነጋገሩን የመረጃ ባለሙያም ዝርዝር ጉዳዩን ካደመጡን በኋላ ወደተጠቀሱት ወረዳዎች ደውለው ያለውን ትክክለኛ መረጃ አጣርቼ እደውላለሁ ቢሉም በድጋሚ ልናገኛቸው አልቻልንም፡፡

## ከስራ የታገዱ መምህራን የይቅርታ ደብዳቤ እንዲያስገቡ መጠየቃቸውን ገለፁ

በወርሃ መጋቢት ከመምህራን የደመወዝ እርከን ማስተካከያ ጋር ተያይዞ በተነሳው ተቃውሞ ከስራቸው የታገዱ መምህራን የይቅርታ ደብዳቤ እንዲያስገቡ ተጠየቁ፡፡

በ05/10/2004 ዓ.ም. ማክሰኞ ዕለት በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ተደውሎ የይቅርታ ማመልከቻ ደብዳቤ ክፍለ ከተማና ትምህርት ቢሮን ጨምሮ በየደረጃው ላሉ የትምህርት ጽ/ቤቶች ካስገቡ ወደ ስራ የሚመለሱበት ሁኔታ እንደሚታይ በየካ ክ/ከተማ መምህራን ማህበር በኩል እንደተገለጸላቸው የኮከበ ፅባህ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ት/ቤት መምህር የነበሩት አቶ ታሪኩ መኮንን ለፍትሕ ገልፀዋል፡፡

መምህሩ አያይዘውም ‹‹የሚያስተዳድሩን ባዕድ ቅኝ ገዢዎች አይደሉም ወንድሞቻችን ናቸው፡፡ ህሊናችንን ሸጠን ለጉልበተኛ እጅ መስጠትን ሊያለማምዱን አይገባም›› ካሉ በኋላ ‹‹የይቅርታ ጠይቁ ውትወታቸውን ወደ ጐን ትተው ከስራ ከታገድን ጀምሮ ለ3 ወራት ያልከፈሉንን ደመወዝ ከካሳ ጋር ከፍለው ወደ ስራችን በመመለስ ስህተታቸውን ቢያርሙ ይሻላቸዋል›› ብለዋል፡፡

ስለጉዳዩ ያነጋገርናቸው የየካ ክ/ከተማ መምህራን ማህበር ሰብሳቢ አቶ ሀብቱ አብርሃ የይቅርታ ደብዳቤ አስገቡ መባላቸው እውነት መሆኑን ገልፀው ‹‹መምህራኑ ወደ ስራ ገበታቸው በሚመለሱበት ሁኔታ ላይ እየሰራን ነው›› በማለት ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡

## በማረሚያ ቤት የሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ከትናንት ጀምሮ የረሃብ አድማ እያደረጉ እንደሚገኙ ተገለፀ

በአዲስ አበባ በሚገኙት በቃሊቲ እና በቂሊንጦ ማረሚያ ቤት የሚገኙ ቁጥራቸው በርከት ያሉ የፖለቲካ እስረኞች ‹‹እስር ቤቶች የማሰቃያ ሥፍራ መሆናቸው ያብቃ›› በሚል ከትናንት ጀምሮ ለሦስት ቀናት የሚቆይ የረሃብ አድማ በማድረግ ላይ እንደሚገኙ የፍትሕ ምንጮች ገለፁ፡፡

በእነአንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ሆነው የፍርድ ሂደታቸውን ከሚከታተሉት ተጠርጣሪዎች መካከል የሁለት እስረኛ ቤተሰቦች በትናንትናው ዕለት የወሰዱላቸውን ምግብ ‹‹በረሀብ አድማ ላይ ነን›› በሚል ምክንያት እንዳልተቀበሏቸው ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡

‹‹በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ በተለመደው መንገድ ተፈትሸን፣ እንደተለመደው ምግብ ልንሰጥ ሄደን ነበር›› ያሉት የአንደኛው እስረኛ ባለቤት ‹‹በማረሚያ ቤቱ ላይ ጥያቄ ስላለን ጥያቄያችን እስኪመለስ ድረስ ምግብ አንበላም፡፡›› ሲል ባለቤቴ መለሰልኝ በማለት አስረድተዋል፡፡ ‹‹ቤተሰብ ደክሞ ሰርቶ ያመጣውን ምግብ ለምን አትወስዱም?›› በማለት በእስረኞች መጠየቂያ ቦታ ላይ የነበሩ ፖሊሶች ለእስረኞቹ ጥያቄ አቅርበው እንደነበረ የእስረኛው ባለቤት ገልፀዋል፡፡

እስረኛው ባለቤታቸውም ‹‹ስለጉዳዩ ቤተሰቤን አስረድቻለሁ›› የሚል መልስ መስጠቱንና ጠዋት ማረሚያ ቤቱ ያዘጋጀላቸውን ቁርስም እንዳልተመገቡ መስማታቸውን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት የእስረኛው ባለቤት አስረድተዋል፡፡ የሌላኛው እስረኛ እናትም ልጃቸው በነገራቸው ነገር ተደናግጠው እንደነበረ የፍትህ ምንጮች ጠቁመዋል፡፡

እስረኞቹ ከሚያነሷቸው ጥያቄዎች መካከልም የሙያም ሆነ የቀለም ትምህርት እንዲማሩ አለመፈቀዱን፣ የሚፈልጉትን መጽሐፍ ማንበብ አለመቻላቸውን፣ የሚፅፏቸው ፅሁፎች መኻታቸው በድንገት ተበርብሮ መወሰዱን፣ ለመጎብኘት የሚፈቀድላቸው የጥየቃ ፕሮግራም ከጥቂት ሰዎች ጋርና በጣም ለአጭር ጊዜ ነው የሚሉት ይገኙበታል፡፡

እየተደረገ ነው ስለተባለው የረሃብ አድማ ለማጣራት ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ ብንደውልም ስልካቸው ሊነሳ ባለመቻሉ የማረሚያ ቤቱን ምላሽ ከዚህ ዜና ጋር ልናስተናግድ አልቻልንም፡፡

## በትላንትናው ምሽት መገናኛ አካባቢ ከሕገ-ወጥ ንግድ ጋር በተያያዘ ነጋዴዎችና ፖሊሶች ተጋጩ

### - የአንድ ሰው ሕይወት አልፏል ተባለ

በየካ ክ/ከተማ በቀድሞ ቀበሌ 16 መገናኛ ታክሲ ተራ በሚባለው አካባቢ መንግስት ሕገወጥ በሚላቸው የመንገድ ላይ ነጋዴዎችና ፖሊሶች መካከል በትናንትናው ምሽት በተፈጠረ ግጭት የአንድ ሰው ሕይወት ማለፉን የአይን እማኞች ለፍትሕ ገለፁ፡፡

የታክሲና የእግረኛ ግርግር በማይለየው በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ አስተዳደር የፍትሕ፣ የህግ ጉዳዮች፣ የትምህርት፣ የጤና ክትትል ግንባታ ጽ/ቤት አካባቢ ትናንት አመሻሽ 1፡30 ሰዓት ገደማ በተፈጠረው ግርግር፣ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ሲጮሁና ሕፃናት ሲያለቅሱ እንደነበረ በወቅቱ በስፍራው የነበሩ ሰዎች ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡

ሕገ-ወጥ በሚባሉት ነጋዴዎችና በፖሊሶቹ መካከል በተፈጠረው ግጭት ተኩስ መሰማቱን፣ እንዲሁም ወደ ፖሊሶች ድንጋይ መወርወሩን ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ አንድ ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ ላይ በስፍራው የደረሰው የፍትህ ዘጋቢ እንደተመለከተው ከመገናኛ ወደ 22 መስመር በሚወስደው መንገድ መኪኖች በቀጥታ ማለፍ እንጂ መቆም አይችሉም ነበር፡፡ በስፍራው ቁጥራቸው በጣም የበዙ የፌዴራል ፖሊሶች አካባቢውን ከብበው የነበሩ ሲሆን በፖሊስ መኪኖች ላይ ተይዘው የተጫኑ ወጣቶችን መመልከት ችሏል፡፡

ስለተከሰተው ጉዳይ በስፍራው የነበሩትን የፌዴራል ፖሊስ ኃላፊዎችን የፍትህ ዘጋቢ ለማነጋገር ሞክሮ የነበረ ቢሆንም የፖሊስ ኃላፊዎቹ በአካባቢው ምንም አለመፈጠሩን ደጋግመው በመግለጽ ‹‹ምንም የምናውቀው ነገር የለም›› በማለት ለማስተባበል ሞክረዋል፡፡

## በሀዋሳ ከተማ ጉዳይ ላይ የቀረበው ሰነድ ተቃውሞ እንደገጠመው ተገለጸ

ባለፈው አርብ የደቡብ ክልል የሴክተር መስሪያ ቤት ሀላፊዎችና የደኢሕዴን አባላት በሀዋሳ ከተማ ጉዳይ ላይ ተሰብስበው ‹‹የሜትሮፖሊታን ከተማችንን እንዴት እንምራው?›› በማለት ያቀረቡት ሰነድ ተቃውሞ እንደገጠመው የፍትሕ ምንጮች ገልጸዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው አቶ ብርሃኑ ለታም የተባሉ የከተማው የኢኮኖሚና ልማት ጽ/ቤት ሀላፊ ‹‹በእርግጥም አጀንዳው በአባላት ደረጃ ለውይይት ቀርቦ ነበር፡፡ ብዙዎቹም ተገቢ አይደለም በማለት ጥያቄ አንስተዋል፡፡ ይሄን በውይይት መፍታት ሲገባቸው ግማሹ ያልተባለውን እያለ ቅስቀሳ ሲያካሂድ ሰው ወደ ሌላ ችግር እንዳይገባ ብለናል፡፡ ድርጅቱም አቅጣጫ እስከሚያስቀምጥ ድረስ ለጊዜው ውይይቱን አቋርጠነዋል›› በማለት ገልፀዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የደኢህዴን የከተማው ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ሳሙኤል ሴባ ስለሰነዱና የተቃውሞ ሰልፍ ሊወጡ የተዘጋጁ የብሄረሰቡ ተወላጆች አሉ ስለሚባለው ጉዳይ ከፍትህ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ከከፍተኛ አመራር ጀምሮ በየደረጃው እስከ አባላት ድረስ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ውይይቱ ገና አላለቀም፡፡ አሁን ወደ መንግስት ስራ ተመልሰናል፡፡ ስለሰልፉም የሰማነው ነገር የለም፤ ጉዳዩም ሰልፍ የሚያስወጣ አይደለም›› በማለት ስብሰባ ላይ በመሆናቸው ከዚህ በላይ ምንም ሊሉ እንደማይችሉ ተናግረዋል፡፡ የሀዋሳ ከንቲባ ለሆኑት አቶ ዮናስም ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርበንላቸው ‹‹ጉዳዩ የሚመለከተው የክልሉ ምክትል መስተዳደር የሆኑትን አቶ አለማየሁ ነው፡፡ እሳቸውን ጠይቁ›› በማለት ስለጉዳዩ ማብራሪያ ለመስጠት እንደሚቸገሩ ገልፀዋል፡፡

## የአቶ ኦልባና ሌሊሳን መደብደብ ማረሚያ ቤቱ አላውቅም አለ

በሽብርተኝነት ወንጀል ተከሰው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመከላከያ ምስክሮቻቸውን እያሰሙ ያሉት የኦህኮ/መድረክ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ኦልባና ሌሊሳ በእስር ቤት ውስጥ ድብደባ እንደተፈፀመባቸው የፍትህ ምንጮች ገለፁ፡፡

በሽብርተኝነት ወንጀል ተከሰው በእስር ቤት በሚገኙ የፖለቲካ እስረኞች ላይ እንዲህ አይነት ድብድብ ሲደርስ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን፤ ይህንን ድብደባ ተከትሎ በፖለቲካው ምክንያት የታሰሩ ግለሰቦች ከፍተኛ ስጋት ላይ እንደሆኑ እነዚሁ ምንጮች ጨምረው ገልፀዋል፡፡

አቶ ኦልባና ላይ ደረሰ የተባለውን ድብደባ አስመልክቶ የማረሚያ ቤቱን አስተዳደር የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አዲስ ጴጥሮስን ፍትህ በስልክ ብታነጋግራቸውም ‹‹እኔ ስለዚህ ጉዳይ የሰማሁት ነገር የለም፤ ነገር ግን እንደዚህ አይነት ድርጊት ይፈፀማል ብዬ አላምንም፡፡ ከተፈፀመም የወሰድነውን እርምጃ እናሳውቃለን፡፡ ...ስለጉዳዩ አጣርተን እንገልጽላችኋለን›› ቢሉም በድጋሚ ስንደውልላቸው ስልካቸውን ለማንሳት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡

## ቅ/ስላሴ ቤተክርስቲያን ቅርስ ፈላጊውን ማገዷን ገለፀች

ባለፈው ሳምንት በወጣችው ፍትሕ ጋዜጣ ላይ ‹‹የቅርስ ግኝት ባለቤትነቴን ለማጥፋት እና የገዳሙን ታሪክ ለመቀየር የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ነው›› በሚል አቤቱታ ያቀረቡት አቶ ቃሲም አለሙ ጽርሐ አርያም ቅ/ስላሴ ቤተክርስቲያን በቃለ ጉባኤ ማገዷን አስተዳዳሪው ለፍትህ ገለፁ፡፡

ግለሰቡም የቪሲዲ ሽያጭ ገቢ የተደረገበት ሠነድ እንዲያቀርቡ፣ ከሌለ ግን በቤተክርስቲያኗ ስም እንዳይጠቀሙ ማገዷን የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ ሊቀ ህሩያን ኤፍሬም ጥላሁን ለፍትሕ አስታውቀዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ‹‹የኢንተርኔት ባንኪንግ›› አገልግሎት መስጠት ሊጀምር ነው

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ‹‹የኢንተርኔት ባንኪንግ›› አገልግሎት ለመስጠት ቅድመ ዝግጅቱን ሙሉ ለሙሉ ማጠናቀቁን አስታወቀ፡፡ ባንኩ አዲሱን ዘመናዊ አገልግሎት አስመልክቶ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ተጠባባቂ ም/ፕሬዝዳንት የሆኑት አቶ ሰለሞን መንገሻ እንዳሉት ‹‹ኢንተርኔት ባንኪንግ ደንበኞች ከቢሮአቸው ወይም ከቤታቸው ወይም ካሉበት የትኛውም ቦታ ሆነው ሂሳባቸውን ማንቀሳቀስ የሚያስችላቸው ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ነው›› በማለት ገልፀዋል፡፡

# ተስፋ የቆረጡና የተረገጡ ህዝቦች እነማንናቸው?

**ት.ኢሳ 18፥2**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በታላቁ መንፈሳዊ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ ስማቸው ከተገለፁ ሀገሮች መካከል በቀዳሚነት ትጠቀሳለች፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ከ53 ጊዜ በላይ ስሟ የተጠቀሰ ሲሆን ከእነዚህም መካከል አብዛኞቹ ንግርቶች የኢትዮጵያን ቅዱስ ምድርነት፣ የምድሪቱን ለምለምነት፣ የህዝቦቿን ኃያልነት፣ የታላቁ የግዮን /አባይ/ ወንዝ መገኛና መፍለቂያ መሆኗን የሚጠቅሱ ናቸው፡፡

ከዚህ በተፃራሪ በመፅሀፉ ውስጥ ስለህዝቦቿ ተስፋ መቁረጥና ድህነት የተነገሩ ትንቢቶችም አይጠፉም፡፡ ለዛሬም የፅሁፋችን መነሻ የሆነው ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ በምዕራፍ 18 ስለኢትዮጵያ የተነገረ በማለት የተናገረውን ትንቢት ነው፡፡ የትንቢቱ ሙሉ ቃል እንዲህ ይላል፡፡

‹‹በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ሳለች ክንፍ ያላቸው መርከቦች ላሉባት ምድር ወዮላት፡፡ መልክተኞችን በባህር ላይ ደብዳቤዎችንም በውሃ ላይ ይልካል፤ ፈጣኖች መልእክተኞች ወደ ረጅምና ወደ ባእድ ወደ ክፉም ህዝብ ይሔዳሉና፡፡ ተስፋ የቆረጡና የተረጋገጡ ህዝቦች እነማናቸው›› ት.ኢሳ. ም.18 ቁ.1-3

ይህ የትንቢቱ ሙሉ ቃል ለኢትዮጵያውያን የተነገረ ነው፡፡ ወቅታዊውን የሀገራችን ሁኔታ መለስ ብለን ስንመለከት እውነትም ተስፋ የቆረጡና የተረገጡ ህዝቦች እነማናቸው? የሚለውን ጥያቄ እንድንጠይቅ እንገደዳለን፡፡

አንድ ዜጋ ህዝብ በሀገሩ የመኖር ዋስትናው ካልተረጋገጠ፣ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብቱ ካልተጠበቀ፣ በኑሮ ደረጃው መሻሻልን ካላገኘ የሚተማመንበትና ተስፋ የሚያደርግበት መልካም አስተዳደር አገዛዙ ሊፈጥርለት ካልቻለ፣ ሠብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን የሚያገኘው በዜግነቱ ሳይሆን በብሔር ማንነቱ፣ በፖለቲካ አስተሳሰቡ፣ በሚናገረው ቋንቋ ብቻ ከሆነ፣ የምዕመኑ ጠባቂ የሚባሉ የሃይማኖት አባቶቹ ከአማኙ ህዝብ ችግርና እልቂት ይልቅ የገዢዎችን ድምጽ ብቻ የሚሰሙና የሚያስተጋቡ ከሆነ፣ ህዝብ በሀገሩ ላይ ተስፋ ለመቁረጥ ይገደዳል፡፡ የህዝብ ይህ ተስፋ መቁረጥ ዞሮ ዞሮ በሀገር ላይ የሚያመጣው ቀውስ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

ዛሬም በሀገራችን ኢትዮጵያ የህዝባችንን ተስፋ መቁረጥና በሀገሩ ላይ ተስፋ ማጣት በምሳሌዎች መመልከት እንችላለን፡፡ ነቢዩ ኢሳያስ ስለኢትዮጵያውያን ባህሪ በትንቢቱ ሲገልፅ ‹‹ፈጣኖች መልእክተኞች ወደ ረዥምና ወደ ባእድ ወደ ክፉም ህዝብ ይሔዳሉ›› ይላል፡፡ በእውነትም የኢትዮጵያውያን ባህሪ በነቢዩ ኢሳያስ ሲገለፅ ለምን ፈጣኖችና መልእክተኞች ተባሉ? ብለን ብንጠይቅ የተለያዩ አንድምታ ያላቸው ትርጓሜዎችን እናገኛለን፡፡ ኢትዮጵያውያን ወደሀገራቸው የሚመጡ እንግዶችን ለመቀበል ፈጣኖች ናቸው፤ አንድም ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸውና ለነፃነታቸው መስዋእት ለመሆን ፈጣኖች ናቸውና አንድም ኢትዮጵያውያን የስነ ህንፃ፣ የስነ ጥበብ ስልጣኔዎችን ለመጀመር ቀደምት ነበሩና ፈጣኖች ሲል ኢሳያስ ገልጿቸዋል፡፡

ታዲያ እነዚህ ህዝቦች በአሁኑ ጊዜ በባዕዳን አገር አሠቃቂ ድርጊቶች ሊፈፀሙባቸው እንደሚችሉ ብሎም ያለምንም ጥቅም ህይወታቸውን ሊያጡ እንደሚችሉ እያወቁ እንኳን በትንቢት እንደተነገረው ወደ ክፉ ህዝብና ሀገር ዘንድ ይሔዳሉ፡፡ ዛሬ ከኢትዮጵያ ወደ አረብና ሌሎች ምዕራባውያን ሀገራት ለመሠደድ በየእለቱ በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን የኢሚግሬሽንና የኤምባሲዎችን ቅፅር ደጅ ሲጠኑ ይውላሉ፡፡ በአቋራጭ መንገድ ለመውጣት እየሞከረ የሚያልቀውን ትውልድ ባህር ይቁጠረው፡፡ ይህ ሁሉ እየሆነ መንግስት ችግሩን የሚፈታው በፓናል ውይይትና በቶክሾው ይመስል ተደጋጋሚ ስብስባዎችን በማዘጋጀት መፍትሄ ለማስገኘት እየታተረ የሚገኝ ቢመስልም አሁንም ከገጠር እየፈለሱ ኢሚግሬሽኑን ደጅ የሚጠኑ ሴቶችም ሆኑ በህገ ወጥ ደላሎች ከሀገር የሚወጡ ዜጎች ቁጥር ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አላየንም፡፡ በሀገሪቱ የሚገኙ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ቢሆኑም ከወረቀት መግለጫ በዘለለ የተሻለ የመፍትሔ ኃሳብ ሲያስቀምጡ አልተስተዋለም፡፡

ተስፋ የቆረጠ ህዝብ በህገወጥም ይሁን በህጋዊ ደላሎች በኩል የስደት ጉዞውን ቀጥሏል፡፡ ይህ ጉዞው መንገድ ውስጥ የሚያስቀረው እንዳለ ሁሉ ካሰበበት የሚደርስ ወገንም አይታጣም፡፡ ነገር ግን ባረፈበት አገርም ቢሆን አሁንም ተስፋ መቁረጡን የሚያባብስ እንጂ ሊያስረሳው የሚችል መፅናኛ አያገኝም፡፡ ከሌሎች አገራት ዜጎች በተለየ ኢትዮጵያውያን በአረብ ሀገራት ብዙ ስቃይና እንግልት ይደርስባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያን በሀገራቸው ቆንስላ ጽ/ቤት ፊት ለፊት እንደ እንስሳ ይጐተታሉ፣ ከፎቅ ላይ ይወረወራሉ፡፡ የፈላ ውሃ ይደፋባቸዋል፡፡ በተስፋ መቁረጥ ከአገር እንደወጡ የሚቆረቆርላቸው መንግስትና ወገን ሳያገኙ፣ ተስፋቸው ሳይለመልም፣ የሀገራቸውና የቤተሰባቸው ናፍቆት እንዳንገላታቸው በሰው ሀገር ፍፃሚያቸው ይሆናል፡፡ እነዚህ ናቸው ተስፋ የቆረጡ የኢትዮጵያ ህዝቦች የተባሉት፡፡ ምሬቱ የባሰባቸውም እዚሁ አገራቸው ላይ በአደባባይ ራሳቸውን በእሳት ይለበልባሉ፣ በሽራፊ ገመድ አንገታቸውን ያንጠላጥላሉ፤ የተስፋው ቃል እስኪደርስ ሁሉም ይሆን ዘንድ ግድ ነው

ኢትዮጵያውያን መሰደድ ብቻም ሳይሆን መረገጥ እጣ ፈንታቸው ሆኗል፡፡ መረገጥ ማለት ከእግር በታች መሆን የሚሉትን ፍቺዎች ይይዛል፡፡ በኢትዮጵያ ብዙ አይነት ምሳሌዎችን ማንሳት እንችላለን፡፡ ህዝቡ ራሱ ግብር እያወጣ ደሞዝ በሚከፍላቸው ፖሊሶች ያለፍርድ በተልካሻ ምክንያት ይደበደባል፣ ይጐተታል፣ ይንገላታል፡፡ መምህራን መብቶቻቸውን ለማስከበር እንቅስቃሴ ሲያደርጉ በሀገራቸው መሪዎች ‹‹ብቃት የለሽ፣ ነውጠኛ›› ወዘተ የሚል ቅፅል ስም እየተሰጣቸው ከስራ መባረርና መታገድ እጣ ፋንታቸው ሆኗል፡፡ ህዝቡ የመዘዋወር መብቱ ተገፎ ‹‹ወደ ክልልህ›› ሂድ በሚል ትእዛዝ ከመኖሪያ ቀዬው ይፈናቀላል፡፡ የሃይማኖት አባቶች ስለመንጋው መበተን ተቆርቋሪ ከመሆንና ለመሰብሰብ የእረኝነቱን ሚና ከመጫወት ይልቅ ስደተኛውን በቤተ እምነቱ እንዳይጠለልና እንዳያርፍ ያባርሩታል፡፡ ገዢዎቹም በመፅሀፍ ‹‹የሾላውን ብረት ብትረግጥ አንተኑ ይጐዳሀል›› የሚለውን ቃል ችላ ብለው ህዝቡን በተስፋ መቁረጥና በመረገጥ ውስጥ እንዲቆይ ትተውታል፡፡ ይህ ነው የተረገጠው ኢትዮጵያዊው ህዝብ፡፡

ነቢዩ ኢሳያስ ከተስፋ መቁረጡ በኋላ የተስፋውን ቃልም ምን እንደሆነ ከላይ በተጠቀሰው ምዕራፍ ላይ ተናግሯል፡፡ ይህ የተስፋው ቃል ለመፈፀሙ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ሊፈፀም የሚችለው ግን ኢትዮጵያውያን ከተስፋ መቁረጥ ይልቅ ተስፋ ማድረግን ገንዘብ ስናደርግና እርስ በርሳችን ተዋደን በአንድነት ስለሀገራችን ሰላምና አንድነት አጥብቀን ስናዝን፣ መሪዎች የህዝቦቻቸውን ለቅሶ፣ ሀዘንና ጩኸት ማዳመጥ ብሎም ምላሽ መስጠት ሲችሉ፣ የሃይማኖት አባቶች የፈጣሪን ቃል ብቻ ተከትለው መንጋውን ሲጠብቁና የእግዚአብሔር የተስፋው ቃል እንደሚፈፀም ነቢዩ ኢሳያስ በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 7 ተናግሮታል፡፡ የተስፋውም ቃል ይህ ነው፡፡

‹‹በዚያ ዘመን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ከተዋረደና ከደከመ ህዝብ ከዛሬ እስከ ዘላለም ታላቅ ከሆነ ወገን ተስፋ ከሚያደርግና ከሚረገጥ በሀገሩ ወንዝ ዳር ከሚኖር ህዝብ ዘንድ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ስም በተጠራበት በደብረ ፅዮን እጅ መንሻ ይቀርባል፡፡›› ኢሳ 18፥7

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

